[1]ጊዜው ልክ ከፋሲካ በዓል በፊት ነበረ፤
ኢየሱስም ይህን ዓለም ትቶ ወደ አብ የሚሄድበት ጊዜ ዮሐ 13፥1-5
እንደ ደረሰ ዐወቀ። በዓለም የነበሩትን፣ የራሱ
የሆኑትን ወደዳቸው፤ በፍጹም ፍቅሩም ወደዳቸው።[ሰ]
[2]እራትም ቀርቦ ሳለ፣ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ዲያብሎስ የስምዖንን ልጅ
የአስቆሮቱን ይሁዳ ልብ አነሣሥቶ ነበር። [3]ኢየሱስም፣ አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ
ሥር እንዳደረገለት፣ ከእግዚአብሔር እንደ ተላከና ወደ እግዚአብሔርም እንደሚመለስ
ዐውቆ፣ [4]ከእራት ተነሣ፤ መጐናጸፊያውን አስቀመጠ፤ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ።
[5]ከዚያም በመታጠቢያው ውሃ ጨምሮ የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ በታጠቀው
ፎጣ ያብስ ጀመር።

*[ሰ]1 ወይም እስከ መጨረሻው*

ዮሐንስ ብዙ ነገሮችን በመጥቀስ ለዚህ ሁኔታ ሥነ መለኮታዊ መድረክ ይከፍታል። መጀመሪያ (ቍ. 1)፣ የፋሲካው በዓል በመቃረብ ላይ ነው። ይህ ኢየሱስ ሊያከናውን ለመጣው ነገር ሁሉ ተምሳሌት ነው። የመጨረሻው ትእይንት መጀመሪያ ነው። ሁለተኛ (ቍ. 1-2)፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በጣም ይወዳቸዋል፣ ለ«ተሻለ» ፍጻሜ። ምንም እንኳን የአስቆሮቱ ይሁዳን ይህን ፍቅር ለመካድ አቅዶ ልቡን ለሰይጣን ቢሰጥም ንጽጽሩ በጣም ትልቅ ነው። ሦስተኛ (ቍ. 3)፣ ኢየሱስ ሁሉን ተቆጣጥሯል። እዚህ አደጋም ሆነ ሽሽት የለም። ኢየሱስ ያልማል፣ ያቅዳል፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ የሚሄድበትን የእግዚአብሔርን ፍቃድም ይፈጽማል።

ደቀ መዛሙርቱ በየራሳቸው የወደፊት ተስፋ ሳሉና የፋሲካ ምግብ እየታደለ ሳለ ኢየሱስ የማስመሰል ጠባይ ሳይታይበት ከገበታ ተነሥቶ ፎጣ ታጠቀ። አንድ ባሪያ እንደሚያገለድመው ዐይነት ልብስ ከመሆን በቀር ሌላ የተለየ ልብስ የለበሰ አይመስልም (ከቍ. 12፤ 19፥23-24፤ ከፊል 2፥7 ጋር ያነ)። ይህን በማድረግ የተናቀውን



የሐዋርያቱን እግር የማጠብ ሥራ አከናወነ። ደነገጡ! ሰዎች ወደ ቤት በሚገቡበት ጊዜ ምግብ ከመብላታቸው በፊት እግራቸውን ማጠቡ የበታች አገልጋይ ተግባር ነበር። እግርን መታጠብ እንግዶች የአስተናጋጁን ምንጣፍ ከማቆሸሽ ያድናቸዋል። ደቀ መዛሙርቱ ግን ስለ ራሳቸው ክብር ሲከራከሩ ይህን ሳይፈጽሙ ቀሩ። ቢያንስ ከመካከላቸው አንዱ የኢየሱስን እግር ለማጠብ መነሣት ነበረበት። ስለ ክብር መቀመጫ ሲከራከሩ ሳለ ነው ኢየሱስ ይህን የተዋረደ ተግባር ለማከናወን የተነሣው። እነርሱ ለእርሱ ማድረግ የሚገባቸውን ተግባር ኢየሱስ ለእነርሱ መፈጸሙን ሲገነዘቡ፣ ዐሥራ ሁለቱ የቱን ያህል ያፍሩ ይሆን?

[6]ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፤ ጴጥሮስም፣
ዮሐ 13፥6-11 «ጌታ ሆይ፤ አንተ እግሬን ታጥባለህ?» አለው።
[7]ኢየሱስም መለሰ፣ «የማደርገውን አሁን አታውቅም፤
በኋላ ግን ታስተውላለህ» አለው።
[8]ጴጥሮስም፣ «የለም፤ እግሬን ከቶ አታጥብም» አለው።
ኢየሱስም፣ «ካላጠብሁህማ ከእኔ ጋር ዕድል ፈንታ የለህም» አለው።
[9]ስምዖን ጴጥሮስም፣ «ጌታ ሆይ፤ እንግዲያውስ እግሬን ብቻ ሳይሆን
እጄንም ራሴንም እጠበኝ» አለው።
[10]ኢየሱስም፣ «ገላውን የታጠበ ሰው የሚያስፈልገው እግሩን ብቻ መታጠብ
ነው፤ የቀረው አካሉ ግን ንጹሕ ነው። ሁላችሁም ባትሆኑ፣ እናንተ ንጹሐን ናችሁ»
አለው። [11]«ሁላችሁም ንጹሐን አይደላችሁም» ያለው አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደ
ሆነ ያውቅ ስለ ነበር ነው።

ጴጥሮስ አጥብቆ ተቃወመ። ከዚያም ዐለፈ (በቀጥታም ሆነ በተምሳሌታዊ መንገድ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም)። «እግሬን ከቶ አታጥብም» *[eis ton aiona]* በማለት ኢየሱስ ለማከናወን የተነሣበትን ይተው ዘንድ ተናገረ። ኢየሱስም፣ «ካላጠብሁህማ ከእኔ ጋር ዕድል

ፈንታ የለህም» አለው:: ስለዚህ ጴጥሮስ ወደ ተለየ ሐሳብ አመራና ሁለንተናውን ይታጠብ ዘንድ ጠየቀ:: ትንሹ ነገር ጥሩ ከሆነ ብዙው ከትንሹ በላይ ውብ መሆን እንዳለበት ያውቃል:: ሆኖም ታጥቦ ስለ መጣ አሁን መታጠብ የሚያስፈልገው እግሩን ብቻ ነው:: ጴጥሮስ ራሱንና (ወይም ፊቱን) እጁን ይታጠብ ዘንድ ማውሳቱ አስፈላጊ ነው:: በባህል ረገድ ሲታይ እጅ ሥልጣንና ኀይልን ይወክላል፤ ራስና ፊት ደግሞ ሥልጣንና ክብርን ይወክላሉ:: በሌላ አገላለጽ ጴጥሮስ ያስረክብ የነበረው የተዋረደውን እግሩን[28] ብቻ ሳይሆን የከበሩ አካሉንም ነበር::

ኢየሱስ ስለ ውሃና የአካል ክፍል ብቻ እየተናገረ አይደለም:: ይህ የውስጣዊ መንጻት ትእምርት ነው:: በእነርሱ ዘንድ እንደ ፍልስጥኤማውያን ቆሻሻ በቀላሉ የማይወገድ ሥሥት አለ:: ዮሐንስ ጣልቃ ገብ በሆነ አስተያየት ይሁዳ ምን ለማድረግ እንዳቀደ ኢየሱስ በደንብ እንደሚያውቅ ይገልጻል:: እነዚህ ቃሎች በአስቆሮቱ ይሁዳ ውስጥ ዘልቀው መግባት አለባቸው:: የጌታ የፍቅር እጅ በርኅራኄ ስሜት ሲነካው፣ የእግር አጠባው ምን እንዳሳደረበት ማንም ያሰላስል ዘንድ ሳይገደድ አይቀርም::

ዮሐ 13፥12-17

[12]እግራቸውን አጥቦ ካበቃ በኋላም ልብሱን
ለብሶ በቦታው ተቀመጠ፤ እንዲህ አላቸው፤
«ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? [13]እናንተ፣ *መምህር
ጌታ* ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፤ እንደምትሉኝ እንዲሁ
ነኝና:: [14]እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፣
እናንተም እንደዚሁ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል:: [15]እኔ
እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላችኋለሁ:: [16]እውነት
እላችኋለሁ፤ አገልጋይ ከጌታው፣ መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም:: [17]እንግዲህ
እነዚህን ነገሮች ዐውቃችሁ ብትፈጽሙ ትባረካላችሁ::

[28] G. S. Shae, "Why Feet, Hands and Head?" *BT* 48/2 (1997): 221-228.



ትምህርቱ ግልጽ ነው:: አስተማሪው ኢየሱስ ነው:: ተማሪዎቹም ከእርሱ የላቁ አይደሉም:: ስለዚህ እንዲህ ዝቅ ባለ ደረጃ የሚያገለግል ከሆነ፣ ደቀ መዛሙርቱም እንደዚሁ ለመፈጸም መዘጋጀት አለባቸው:: እግርን የማጠብ ባህል በመጀመሪያው ምእት ዓመት እንዳስገኘው ያለ ባህላዊ ፋይዳ በዚህ ጊዜ አያስገኝልንም:: እግር ማጠብ ዝቅ የማለት ምልክትና ውብ የሃይማኖት ተግባር ቢሆንም፣ በሐዋርያት ላይ የነበረውን ያህል በዚህ ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ ተግባራዊ ፋይዳ የለውም:: ኢየሱስ የሚጠራን ለአንድ ዐይነት ድርጊት ሳይሆን፣ በልዩ ልዩ መንገድ ለሚገለጽ የልብ ዝንባሌ ነው:: በእኛ ዘመን ቆሻሻን አውጥቶ መድፋት፣ የመታጠቢያ ቤትን ማጽዳት ወይም የሕፃን የሽንት ጨርቅን መለወጥ ማለት ሊሆን ይችላል:: «እግር ማጠብ» እያንዳንዱ ሰው ከኩራት የተነሣ ሊሠራው የማይፈልገውን ሥራ ማከናወን ነው::[29] ይህ ከወደቀው ደመነፍሳችን ጋር የሚጣረስ ቢሆንም እንኳ፣ በዚህ ዐይነት መንገድ ለሚኖሩት በረከት እንደሚሰጣቸው ኢየሱስ ተስፋ ሰጥቶአል (ቊ 20)::

ዮሐ 13፥18-20

[18]«ስለ ሁላችሁ መናገሬ አይደለም፤
የመረጥኋቸውን ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን፣ *እንጀራዬን
አብሮኝ የቈረሰ ተረከዙን አነሣብኝ* የሚለው የመጽሐፍ
ቃል እንዲፈጸም ነው::

[29] ይሁን እንጂ A. Edgington, "Foot Washing as an Ordinance," *GTJ* 6.2 (1985): 425-434 በሚለው ላይ ሥርዐት ሆኖ መፈጸም እንዳለበት በመግለጽ ሐተታ ያቀርባል:: ዮሐ 13፥1-17 እና በ1ጢሞ 5፥10 ውስጥ የሚገኘው እግር የመታጠብ ሥርዐትን ሦስት መስፈርቶች ያሟላል ይላል:- (1) በባሕርዩ ሥርዐታዊ የሆነውን አካላዊ ክንዋኔ፤ (2) በአዲስ ኪዳን ላይ በግልጽ ትምህርት ሆኖ የቀረበውን የመንፈሳዊ እውነታ ትእምርታዊ ውክልና፤ (3) በዘላቂነት ይከናወን ዘንድ በክርስቶስ ወይም በሐዋርያቱ የተሰጠ ትእዛዝ:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሦስቱም አንድ ደረጃ ላይ ሲደርሱ አጠያያቂ ይሆናሉ::

19«ሲፈጸም እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ ዘንድ፣ ይህ ከመሆኑ በፊት አሁን
ነገርኋችሁ:: 20እውነት እላችኋለሁ፤ እኔ የላክሁትን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔን
የተቀበለም የላከኝን ይቀበላል::»

ይሁዳ መዝሙር 41÷9ን እንዲፈጽም (ከዘካ 11÷7-14፤ ከመዝ 69÷25፤ 109÷8፤ ከሐሥ 1÷20 ጋር ያነጻ) አስቀድሞ ተወስኖበታል:: በግልጽ እንደሚታወቀው እግዚአብሔር የወደፊቱን ከወዲሁ በማየት፣ ይሁዳ ወደፊት ምን እንደሚሠራ አይቶ ይሁዳ ከመወለዱ በፊት (1ጴጥ 1÷2) ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ አሰፈረው:: ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር ይሁዳን ለጥፋት አስቀድሞ ወስኗል ማለት አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰናቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ::[30] ያከናውኑት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ከወሰነላቸው ተግባር በቀር ከኢየሱስና ከይሁዳ ሌላ አንዳቸውም ለድነት ወይም ለጥፋት አልተወሰኑም:: ያለጥርጥር ሥራውን ያከናውናሉ:: የእግዚአብሔርን መንገድ ወይም የራሳቸውን መንገድ ተከትለው ሊያከናውኑት ይችላሉ:: ለምሳሌ እስራኤላውያን ይሄዱ ዘንድ ፈርዖን ሊፈቅድ ነበር:: በራስ መንገድ ለመሥራት መረጠ፤ እግዚአብሔርም አስገደደው:: የዮናስ ታሪክም ተመሳሳይ ነገር ይገልጻል:: በእግዚአብሔር ሉዐላዊነትና በሰው ነጻ ፈቃድ መካከል ላለው ተቃራኒ የሚመስል መንገድ መፍትሄ መስጠት ባንችልም የአስቆሮቱ ይሁዳ

[30] አብርሃም (ነህ 9÷7)፤ ያዕቆብና ዔሳው (ከዘፍ 25÷19 ጋር ያነ፤ ሚል 1÷2-3፤ ከሮሜ 9÷10-13፤ ፈርዖን (ዘፀ 9÷16፤ ሮሜ 9÷17)፤ ሳኦልና ዳዊት (1ሳሙ 16÷1-14)፤ ኢሳይያስ (1ነገ 13÷1-3)፤ ቂሮስ (ኢሳ 41÷25፤ 44÷28፤ 45÷1-13፤ ከ2ዜና 36÷22 ጋር ያነጻ)፤ መጥምቁ ዮሐንስ (ሚል 4÷6፤ ኢሳ 40÷3፤ ከሉቃ 1÷17 ጋር ያነ)፤ ኢየሱስ (ኢሳ 42÷1፤ ማቴ 12÷18፤ ሉቃ 9÷35፤ ሐሥ 2÷23፤ 4÷28)፤ ያስቆሮቱ (መዝ 41÷9፤ 69÷25፤ 109÷8፤ ማር 14÷10፤ ሐሥ 1÷20)፤ ሐዋርያት (ሉቃ 6÷13፤ ዮሐ 6÷70፤ 15÷16)፤ ጳውሎስ (ሐሥ 9÷15፤ 13÷2፤ ሮሜ 1÷1፤ ገላ 1÷15፤ ኤፌ 3÷7)፤ ሩፎን (ሮሜ 16÷13)፤ ኤርምያስ (ኤር÷5)::



ኢየሱስን አሳልፎ መስጠትን መምረጡን እናምናለን፤ ለፈጸመው ድርጊትም በግሉ ይጠየቅበታል::

ይህ ነገረ መለኮታው ግምት ማራኪ ይሁን እንጂ የኢየሱስን ቃል ዋና ሐሳብ አላገኘውም:: የይሁዳን ክሕደት አስቀድሞ ተናገረ፤ ይኸውም ነገሩ ከተፈጸመ በኋላ ታማኝ ተከታዮቹ ኢየሱስ በእርግጥ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን እንዲያውቁ ነው:: ይህ አሸናፊ መሲሕ ሆኖ ከመታየት ይልቅ በሌላ መልኩ በታየበት ለእነዚያ ጽልመታዊ የሞቱ ቀናት ወሳኝ ይሆናል:: ይህ ብቻ ሳይሆ ዕርገቱን ተከትለው በመጡት ቀናት ይህ አስቀድሞ የተነገረ (ትንቢት) ከኢየሱስ ጋር ስፍራ እንደሚኖራቸው አስቀድሞ የተወሰነላቸውን ዕጣ ፈንታ ለማስታወስ ያገለግላል:: ሐዋርያትን የሚቀበሉ ኢየሱስን ይቀበላሉ፤ ኢየሱስን የሚቀበሉም እግዚአብሔር አብን ይቀበላሉ::

**§ 146**
**አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደሆነ መግለጹ**
**(ማቴ 26÷21-25፤ ማር 14÷18-21፤ ሉቃ 22÷21-23፤ ዮሐ 13÷21-30)**

(ዮሐ13)21ይህን ካለ በኋላም (በማዕድ ላይ
ሳሉም[ማር]) ኢየሱስ በመንፈሱ ታወከ፣ «ከእናንተ አንዱ
(አብሮኝ የሚበላው እርሱ) እኔን አሳልፎ ይሰጣል» ሲል
በግልጽ ተናገረ::
22ደቀ መዛሙርቱም ማንን ማለቱ እንደሆነ
ግራ ተጋብተው እርስ በርሳቸው ተያዩ::

(ማቴ26)22እነርሱም እጅግ አዝነው፣ በተራ በተራ፣ «ጌታ ሆይ፤ እኔ እሆን
ይሆን?» አሉት::
23እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «አሳልፎ የሚሰጠኝ ከወጭቱ ውስጥ
አብሮኝ ያጠቀሰው ነው፤ 24የሰው ልጅ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈው ይሄዳል፤ ነገር ግን
የሰውን ልጅ አሳልፎ የሚሰጠው ሰው ወዮለት፤ ለዚያ ሰው ሳይወለድ ቢቀር ይሻለው
ነበር::»
25አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳም፣ «መምህር ሆይ፤ እኔ እሆንን?» አለው::
እርሱም፣ «አንተ አልህ» አለው::

የፋሲካ ምግብ እየተበላ ሳለ ኢየሱስ እየተጨነቀ መጣና ቋጥሮ ያቆየውን ነገር አፈነዳው:- ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል! ኢየሱስ አልፎ እንደሚሰጥ ከዚህ ቀደም ትንቢት ተናግሮአል (ክፍል 88፤ ማቴ 17÷22፤ ማር 9÷31፤ ሉቃ 9÷44፤ እና ክፍ 125ሀ፤ ማቴ 20÷18፤ ማር 10÷33):: አሁን ግን ድርጊቱ ቅርብ በሆነው ወዳጁ እንደሚፈጸም ተናገረ:: እርሱ (ሀ) ከኢየሱስ ጋር በመመገብ ላይ ነው (ማር 14÷28)፤ (ለ) ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ነው (ማር 14÷20)፤ ደግሞም (ሐ) በራሱ በመምህሩ እጅ ቊራሽ እንጀራ ይሰጠዋል (ዮሐ 13÷26):: እንዲህ ባለው ምሥራቃዊ ባህል በአንድ የማዕድ ኅብረት አብሮ የተካፈለን ሰው አሳልፎ መስጠት የክሕደት ክሕደት ነው::

ደቀ መዛሙርቱ ደንግጠዋል፤ አዝነዋል፤ ግራ ተጋብተዋል፤ በመጠኑም ቢሆን ኀፍረት ውስጥ ገብተዋል፤ (*አፓሪአ - aporeo* [«ግራ ተጋብተው»] የሚለው ቃል እንደሚያመለክተው ማለት ነው):: ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ስለ ማን እንደሚናገር ለመገመት ጥረት አደረጉ:: ይሁን እንጂ ሁሉንም ሲቃኙ ከራሳቸው በቀር እገሌ ሊሆን ይችላል ማለት አልቻሉም ነበር:: በኀ በሆነ ጥርጣሬ ውስጥ ገብተው «ጌታ ሆይ፤ እኔ እሆን ይሆን?» በማለት ተራ በተራ ጠየቁ:: ርግጥ ነው ሁሉም የተጠቀሙት ሐረግ አሉታዊ መልስን የሚያሰጠውን ነው:: ይሁዳ እንኳ ያንኑ መሥመር ተከትሎ፣ «እኔ እሆንን?» ሲል ጠየቀ:: እንዲህ የጠየቀበት ምክንያት ራሱን ላለማጋጥ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ኢየሱስን፣ «ጌታ» ብሎ አልጠራም፤ «ረቢ» ብሎ ጠራው እንጂ:: ግብዝነቱ ወሰን አልነበረውም:: ኢየሱስ በቀጥታ «አንተ አልህ» አለው (ከማቴ 26÷64 ጋር ያነ):: ይህ ዕጥር ምጥን ያለ ንግግር በሁለቱ ብቻ ተወስኖ የቀረ ይመስላል:: ዐሥራ አንዱ የሰሙት ቢሆንም፣ ከይሁዳ በቀር ማንም በማይገነዘበው መልክ ስለ ተናገረ የኢየሱስ ንግግር አሻሚ ነው::



ኢየሱስና ይሁዳ ጉዳዩን ቢያውቁትም (ከዮሐ 13÷10:11:18-19 ጋር ያነ)፣ ዐሥራ አንዱ አሁንም ግራ እንደ ተጋቡ ናቸው::

በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ኢየሱስ በሰው እጅ ዐልፎ እንዲሰጥ አስቀድሞ ተወስኖበታል (ከዘካ 11÷7-14፤ ከመዝ 41÷9 ጋር ያነ):: ቢሆንም ይሁዳ ለድርጊቱ ይጠየቅበታል:: የሐዋርያነት ሹመቱ ይሻራል (መዝ 69÷25፤ 109÷8፤ ሐሥ 1÷20)፤ አሠቃቂ ሞት ይሞታል (ማቴ 27÷3-10፤ ሐሥ 1÷18-19)፤ ተገቢውን የቅጣት ቦታም ያገኛል:: ርግጥ ነው ሁሉም ነገር ከተፈጸመ በኋላ የጥፋት ልጅ የሆነው (ዮሐ 12÷12) የአስቆሮቱ ይሁዳ ምነው ባልተወለድሁ ይላል::

[23]እነርሱም ከመካከላቸው ይህን የሚያደርግ ማን ሊሆን እንደሚችል እርስ በርሳቸው ይጠያየቁ ጀመር:: **ሉቃ 22÷23**

**ዮሐ 13÷23-26 ከማር 14÷20 ጋር**

[23]ከእነርሱ አንዱ፣ ኢየሱስ ይወደው የነበረ
ደቀ መዝሙር ወደ ኢየሱስ ደረት ተጠግቶ ተቀምጦ
ነበር:: [24]ስምዖን ጴጥሮስም ይህን ደቀ መዝሙር
በምልክት ጠቅሶ፣ «ማንን ማለቱ እንደሆነ ጠይቀው»
አለው::
[25]እርሱም ወደ ኢየሱስ ደረት ደገፍ ብሎ፣ «ጌታ ሆይ፤ ማን ይሆን?» ብሎ
ጠየቀው::
[26]ኢየሱስም («ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ[ማር]») ይህን ቊራሽ እንጀራ ከወጭቱ
አጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው» አለው፤ ከዚያም ቊራሹን እንጀራ አጥቅሶ ለስምዖን
ልጅ ለአስቆሮቱ ይሁዳ ሰጠው::

ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን መጠየቅና እርስ በርስ መጠያየቃቸውን ቀጠሉ:: ከማዕድ ገበታው ባሻገር የሚገኘው ጴጥሮስ «ተወዳጅ የሆነውን ሐዋርያ» ዮሐንስን (ዮሐ 19÷26፤ 20÷2፤ 21÷7:20)

በጥቅሻ [ኒዎ - *neuo*] ቀሰቀሰው:: ኢየሱስ ማንን ማለቱ እንደ ሆነ ዮሐንስ በግል ይጠይቀው ዘንድ ጴጥሮስ ፈለገ:: የመቀመጫው አደረጃጀት የተራራቀ እንዳልነበር ኤደርሼም (Edersheim) ይገልጻል (II:494):: በገበታው ሦስት አቅጣጫ ትራሶች እንዴት እንደ ተቀመጡና ምግብም በስተ መጨረሻ ባለው ባዶ ስፍራ ይሰጥ እንደ ነበር ይገልጻል:: የምግብ ገበታው ወደ መሬት በጣም ዝቅ ብሎ ተዘርግቶ ስለ ነበር በግራ ጐናቸው ትራሱን የተደገፉት ሁሉ በገበታው ዙሪያ ተቀምጠው ነበር:: የክብር ተጋባዦቹ በግራ ቀኙ ሆነው እንግዳ ተቀባዩ (የቤቱ ባለቤት) በምግብ ገበታው በአንድ ወገን ይገኛል:: ዝቅተኛው ስፍራ በሌላኛው የገበታው ጫፍ ላይ የሚገኘው ቦታ ነበር:: ዮሐንስ ከኢየሱስ ፊት ለፊት ደገፍ ብሎ ተቀምጦአል፤ ዮሐንስ 13÷23-25:: ከእርሱ በስተጀርባ ኤደርሼም እጅግ የተከበረ ቦታ በማለት ያመለከተው ሲሆን ይሁዳ የተቀመጠበት ቦታ መሆን አለበት:: እንደሚታወቀው ይሁዳና ኢየሱስ የግል ጨዋታ (ንግግር) የነበራቸው ይመስላል (ማቴ 26÷25):: ኢየሱስ ቍራሽ እንጀራ ለመስጠት ከሚያስችለው ቅርብ ቦታ ሳይቀመጥ አልቀረም (ዮሐ 13÷26-27):: ማን ነው ከሁሉ የሚልቀው የሚለውን ክርክር ይሁዳ አሸንፎአል:: ወይም የእርሱን ፍቅር ለማግኘት ሲል ኢየሱስ በዚህ «የክብር መቀመጣ» ላይ እንዲቀመጥ ሳያደርግ አልቀረም:: በሌላ በኩል ግን በምግብ ገበታው ከሚገኙት ዝቅተኛ መቀመጫዎች ውስጥ ጴጥሮስ አንዱን መርጦ በመቀመጡ ራሱን አዋርዶአል:: ምናልባት ከእግር መታጠብ በኋላ ይህን ድርጊት ወዲያውኑ ሳይፈጽም አልቀረም::

ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ ደረት ተጠግቶ፣ «ጌታ ሆይ፤ ማን ነው?» በማለት በቀጥታ ጠየቀው:: ኢየሱስ ምልክት ሰጠው:: ቍራሽ እንጀራ ከወጡ (ከተዳመጠ ፍራፍሬ፣ ከውሃና ከሆምጣጤ የተሠራ ነው) ጋር አጣቅሶ ለከሐዲው ይሰጠዋል:: ይህ ድርጊት የጥብቅ ወዳጅነት ምልክት



ነው (ከሩት 2÷14 ጋር ያነ):: ቀደም ሲል ኢየሱስ አሳልፎ የሚሰጠው ሰው ከእርሱ ጋር ከአንድ ወጭት እንደሚያጣቅስ ተናግሮአል:: ይሁን እንጂ ምሽቱ ሲገባደድ ይህ ዐሥራ ሁለቱንም ሊገልጽ የሚችል ነው:: «ከወጭቱ ማጣቀስ» «አብሮ ከመቍረስ» ጋር አንድ ነበር:: ይህኛው ምልክት ግን ይበልጥ ግልጽና ይበልጥ ፈጣን ነው:: ቍራሽ እንጀራ ወስዶ ወጭቱ ውስጥ አጠቀሰና ለይሁዳ ሰጠው::

**ዮሐ 13÷27-30**

[27]ይሁዳም ቍራሹን እንጀራ እንደ ተቀበለ
ወዲያው ሰይጣን ገባበት::
ኢየሱስም፣ «የምታደርገውን ቶሎ አድርግ» አለው፤ [28]ይሁን እንጂ ኢየሱስ
ለምን እንዲህ እንዳለው ማንም አላወቀም ነበር:: [29]ይሁዳ ገንዘብ ያዥ ስለ ነበረ፣
አንዳንዶቹ ለበዓሉ የሚያስፈልግ ነገር እንዲገዛ ወይም ለድኾች እንዲሰጥ ኢየሱስ
የተናገረው መሰላቸው:: [30]ይሁዳም ያን ቍራሽ እንጀራ እንደ ተቀበለ ወጥቶ ሄደ፤
ሌሊትም ነበረ::

ቍራሽ እንጀራው ወደ አፉ ሲገባ ሰይጣን ወደ ይሁዳ ልብ ገባ:: ኢየሱስ ሥራውን እንዲያፋጥን አዘዘው፤ ይህንኑም ሌሎቹ ሐዋርያት የገንዘብ ያዥ ተግባር ነው ብለው ተረጐሙት:: ክፍሉን ትቶ ሲሄድ ምናልባት ከጴጥሮስና ከዮሐንስ በቀር ሌሎቹ ሐዋርያት ስለ ይሁዳ ግራ እንደተጋቡ ነበሩ:: ይሁዳ ራሱም በጭለማ ውስጥ ነው፤ በጭለማ ያለውም ከሌሊቱ ግርዶሽ የተነሣ ሳይሆን፣ ከሰይጣናዊ የአታላይነቱ ሽፋንና ክሕደቱ የተነሣ ነበር:: «ሌሊትም ነበር» የሚለው የዮሐንስ ዕጥር ምጥን ያለው ሐሳብ የይሁዳ የመጨረሻ ሕይወት ተገቢ ገለጻ ነው:: ጉዳዩ ለጴጥሮስና ለይሁዳ እንዲሁም ለኢየሱስ ግልጽ ሆኖአልና ይሁዳ በፍጥነት መፈጸም አለበት:: አጋጣሚው ጥሩ ሆኖ ሳለ መፈጸም አለበት::

**§ 147**
**ስለ ጴጥሮስ ክሕደት የተነገረ ትንቢት**
**(ማቴ 26፥31-35፤ ማር 14፥27-31፤ ሉቃ 22፥31-38፤ ዮሐ 13፥31-38)**

የጊዜና የሁኔታው ቅደም ተከተል በሁለት ምክንያቶች አስቸጋሪ ነው:: በመጀመሪያ ዮሐንስ የጌታን እራት ለመጻፍ አልመረጠም (ክፍል 148)፤ በግልጽ እንደሚታየው በተመሳሳዮቹ ወንጌላትና ራሱም በዮሐንስ 6፥53-54 ላይ ባመለከተው በመርካት በቂ ነው ብሎ ሳያስብ አልቀረም:: ሁለተኛ ማቴዎስና ማርቆስ የጴጥሮስን ክሕደት ያሰፈሩት ያን ቤት ለቆ ከሄደና ወደ ጌቴሴማኒ ካቀና በኋላ ነበር (ከክፍል 152 ጋር ያነ):: ይሁን እንጂ ዮሐንስ ይህን ሐሳብ ያሰፈረው ገና ቤት ውስጥ እያሉ ኢየሱስ የደኅና ሁኑ ንግግሩን ከማድረጉ በፊት ነበር (ዮሐ 14፥17):: በዚህ ላይ ማቴዎስንና ማርቆስን እንዲሁ ዐልፈን ዮሐንስ በመከተል ከቶማስና (Thomas) ከጋንደርይ (Gundry) ጋር እንስማማለን:: ዮሐንስ እኮ ሩብ የሚሆነውን መጽሐፉን ያዋለው ለዚህ ለአንድ ምሽት ነው:: ይሁን እንጂ ጴጥሮስ እንደሚክድ የተነገረው ትነቢት የጌታን እራት ይቀድማል ከሚለው ጋር አንስማማም (ክፍል 148):: ከዚህ ላይ የተመሳሳዮቹን ሦስት ወንጌላት ቅደም ተከተል የምናፋልስበት ምክንያት የለም:: ስለዚህ ሁለት ነገሮችን እናከናወናለን:: በመጀመሪያ የዮሐንስን የጊዜና የሁኔታ ቅደም ተከተል ለመከተል ማቴዎስ 26፥30ንና ማርቆስ 14፥26ን ከዐውዳቸው አውጥተን ከክፍል 152 ጋር እንመድባቸዋለን:: ሁለተኛ ከክፍል 147 *በፊት* በክፍል 148 ላይ ማብራሪያ በመስጠት የቶማስንና የጋንደርይን ሥምረት እንደ ገና እናስተካክላለን:: እዚህ ላይ ጥንቃቄ መደረግ አለበት:: ለጊዜና ለሂደት ቅደም ተከተል ስንል ጽሑፎችን ማለዋወጥ በምንጀምርበት ጊዜ በየወንጌላቱ ላለው ዐውድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፤ አለዚያ የአራቱን ወንጌላት ሙሉ ሥዕል ለማግኘት ጥረት ስናደርግ የእያንዳንዱን ለዛ እናጣለን::



**§ 148**
**የጌታ እራት**
**(ማቴ 26፥26-29፤ ማር 14፥22-25፤ ሉቃ 22፥17-20፤ 1ቆሮ 11፥23-26**

ይህን ቅዱስ ሥርዓት አራት ድምፆች ዘግበውታል:: ማቴዎስና ማርቆስ አንድ ዐይነት አቀራረብ አላቸው፤ ሉቃስና ጳውሎስ ግን በጎላ መልኩ ይደራረባሉ:: እዚያ ባንገኝም እንኳ እያንዳንዱ ክርስቲያን በየግሉ የመሳተፍ መብት አለው::[31] ከዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ጀምሮ እስካሁን የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ሞቱን በሥርዐት በመግለጽና በማስታወስ ላይ ናት:: በሚገርም ሁኔታ ይህ አከባበር በመለኮታዊ ኀይል ወደ ቀደመው ዘመን መልሶ በመውሰድ በሚከተሉት ተከታታይ ሁኔታዎች ውስጥ እንድናልፍ ያስችለናል:- በጴጥሮስ ክሕደትና በኢየሱስ ሞት፤ በትንሣኤ ሐሤትና በጴጥሮስ ተስፋ ወደ ቦታው መመለስ:: ይህ የጌታ እራት ነው፤ የክርስቲያንም

[31] B.B. Thurston, "'Do This': A Study on the Institution of the Lord's Supper," *RestQ* 30 (1998): 207-217 በሚለው ላይ በቅዱስ ቊርባን ውስጥ ዋናው ቁም ነገር የሚገኘው ከሚቀርቡት ነገሮች ላይ ሳይሆን፣ ከአፈጻጸሙ ላይ ነው በማለት ሐሳብ ታቀርባለች:: በሌላ አነጋገር፣ ይህ የቤዛነት ዳግመኛ ትዕይንታዊ አፈጻጸም ነው:: ከዚህም በላይ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ የጌታን ሞት ስለሚያውጅ ወንጌላዊ እሳቤ አለው:: N.A. Beck, "The Last Supper as an Efficacious Symbolic Act," *JBL* 89 (1970): 192-198" በሚለው ላይ የጌታ እራት በመጀመሪያ ሥርዐታዊ ሆኖ የመመሥረቱ ጉዳይ እንደ ተተወነ ምሳሌ ነው በማለት ሐሳብ ያቀርባል:: የብሉይ ኪዳን ነቢያት በተውኔታዊ አጉልቶ ማሳያ እንዳስተማሩ ሁሉ ኢየሱስም በቅዱስ ቊርባን ሥርዐት አማካይነት እንዲሁ አደረገ:: B. Cooke ኢየሱስ አንድ እርምጃ ርቆ በመንዝ በሥርዐቱ ላይ መገኘቱ እርሱ ኪዳናዊ መካከለኛ ሆኖ እስከ ቀጠለ ድረስ አስፈላጊ ነው በማለት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን አመለካከት ይደግፋል:: በሌላ አባባል፣ ዳግም የምንፈጽመው ትእምርት አይደለም፤ ኢየሱስ የሚሳተፍበት ሥርዐት እንጂ፤ (ከB. Cooke, "Synoptic Presentation of the Eucharist as Covenant Sacrifice" *TS* 21 [1960]:1-44 ጋር ያነ)::

ክብረ በዓል ነው፤ ቤተ ክርስቲያን አካሉን ስትበላ፣ አካሉ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኅብረትን አገኘ::[32]

ሉቃ 22÷17-18

17ጽዋውን ተቀብሎ ካመሰገነ በኋላ እንዲህ
አላቸው፤ «እንካችሁ፤ ሁላችሁ ከዚህ ተካፈሉ፤
18እላችኋለሁና፤ ከአሁን ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት
እስከትመጣ ድረስ ከዚህ ወይን ፍሬ አልጠጣም::»

ማቴ 26÷26-29፤
ከሉቃ 22÷19-20፤
ከማር 14÷23፤
ከ1ቆሮ 11÷24 ጋር

26እየበሉ ሳሉ፣ ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ
ባረከ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ በመስጠት፣
«እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው (ይህ ስለ እናንተ
የሚሰጥ ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት[ሉቃ])
አላቸው::

27(እንደዚሁም ከእራት በኋላ[ሉቃ]) ጽዋውን አንሥቶ አመሰገነ፤ ለደቀ
መዛሙርቱም በመስጠት እንዲህ አላቸው «ሁላችሁም ከዚህ ጠጡ (ለመታሰቢያዬም
አድርጉት[1ቆር]) (ሁሉም ከዚያ ጠጡ[ማር])::

[32] አሳዛኝ ነገር ነው፤ ቅዱስ ቍርባን የክርክር መነሻ ሆኖ ይገኛል:: አሳዛኙም ሐቅ *በፎክስ* - *Foxe's Book of Martyrs* መጽሐፍ ላይ ተዘክሮ እንደሚገኘው በብዙ መቶኛ የሚቈጠሩ ክርስቲያኖች በጌታ እራት ልዩነት የተነሣ በሌሎች አማኞች ተገድለዋል:: በዚህ ግልጽ መታሰቢያ የተነሣ የጌታን ቤተ ክርስቲያን የለያዩአት ልዩ ልዩ ክርክሮች ከዐሥር አያንሱም:- (1) ወይን ነው ወይስ የወይን ጭማቂ? (2) የቦካ ነው ወይስ ያልቦካ ቂጣ? (3) በየስንት ጊዜ መቅረብ አለበት? (4) ምሳሌ ነው ወይስ ሥርዐት:- ዘይቤ፣ ውሳጤ፣ ወይስ አብሮነታዊ ውሳጤ? (5) የሚቀርቡትን ነገሮች ጸልዮ የሚሰጥ ቄስ፣ ጳጳስ ወይስ ሽማግሌ? (6) የደም ማስተሰርያን ቋሚ ለማድረግ ምሳሌዎቹ አስፈላጊ ናቸውን? (አንዳንዶች አንድ አማኝ በጌታ እራት ላይ በተወሰነ እሑድ ሳይሳተፍ በዚያው ሳምንት ውስጥ ሕይወቱ ካለፈ ደኅንነቱ አሥጊ ይሆናል ብለው ያስባሉ):: (7) አንድ ጽዋ ነው ወይስ ብዙ? (8) ሌሎች ምሳሌዎች (ለምሳሌ፣ በምሥራቅ አገሮች የሩዝ ቂጣ) ምትክ ሊሆኑ ይችላሉን? (9) የአንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም የአንድ ሰበካ ጉባኤ አባል ያልሆኑት ሊሳተፉ ይችላሉን? ወይም ያልተጠመቁ ልጆች፣ ደግሞም አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ሊሳተፉ ይችላሉን? (10) ይህ ምን ተብሎ ይጠራ:- ቅዱስ ቍርባን? የጌታ እራት ወይስ ኅብረት?



28ስለ ብዙዎች የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው::
29እላችኋለሁ፤ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር በአዲስ መልክ እስከምጠጣበት
እስከዚያ ቀን ድረስ፣ ከእንግዲህ ከዚያ የወይን ፍሬ አልጠጣም::

1ቆሮ 11÷26

26ይህን እንጀራ በምትበሉበት ጊዜ፣ ይህንም
ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ
ሞቱን ትናገራላችሁ::

ኢየሱስ የመጨረሻውን ምግብ ለመብላት ከቅርብ ወዳጆቹ ጋር ተቀምጧል:: በአንድ ላይ መብላት ለአይሁድ የተቀደሰ ተግባር ነበር:: በርግጥም ኤርምያስ (Jeremias) የአይሁድ/የክርስቲያን ምግብን አስመልክቶ አምስት አንድምታዎችን በግልጽ ያመለክታል:-[33] (1) የአይሁድ ምግብ፣ በተሳታፊዎቹ መካከል መተሳሰብን ያሳያል፤ ቤተሰባዊ ዝምድናን ይፋ ማድረግ ነው:: (2) የአይሁድ የምግብ ማዕድ ቅዱስ ነው፤ በባርኮት በኩል የእግዚአብሔር ህልዎት አለና:: ስለ ሰጣቸው ምግብ እግዚአብሔርን ማመስገን ብቻ አልነበረም፤ በማዕዳቸው ይገኝ ዘንድ እየለመኑትም እንጂ:: (3) ከኢየሱስ ጋር በአንድ ማዕድ መብላት ብዙ የአዲሱ ቤተ ሰብ አካል መሆንህ(ሽ)ን ያሳያል:: በተጨማሪም ዝቅተኛና (የተናቁና) የጠፉት ከእርሱ ጋር ይበሉ ዘንድ በልዩ ሁኔታ ተጋብዘው ነበር:: (4) ከኢየሱስ ጋር መብላት የደስታ በዓል ነበር፤ ተሣታፊዎቹ የመንግሥቱን የበዓል አከባበር ይፋ ያደርጋሉ - መቤዠትና የኀጢአት ይቅርታ:: (5) ከኢየሱስ ዕርገት በኋላ የቤተ ክርስቲያን የኅብረት ምግብ ኢየሱስን አስታወሰ:: ከዚህ የተነሣም እነዚህ ምግቦች ቸርነት የማድረግ ዕድልን ለመጠቀም አገልግሎት ላይ ውለው ነበር:: ይህ ሁሉ የኢየሱስ የመጨረሻ እራት ዳራ ነው::

[33] J. Jeremias, "'This is My Body ...'" *ExpT* 83 (1972): 196-203.

ከአይሁድ ምግቦች ሁሉ በያመቱ የሚከበረው የፋሲካ በዓል የተቀደሰ ነው:: በዚህ ዓመት ግን አዲስ አቅጣጫን አግኝቶአል:: የመጀመሪያው ፍጻሜ ላይ የደረሰው በጌታ እራት ነው::[34] ለ1500 ዓመታት ያህል በመጠበቅ ላይ ነበር::

ገበታው ተዘጋጅቶአል:: በፊታችን እንጀራና ወይን እንዲሁም ወጥ የያዘ ወጭት አለ፤ ወጡም ከተጨመቀ ፍሬና ከመራራ ቅጠል የተዘጋጀ ነው:: ጋባዡ የተጠበሰውን የበግ ሥጋ አመጣ:: ከመቀመጣችን በፊት ግን አንድ ወጣት፣ «አባቴ ሆይ፤ ይህ ምን ማለት ነው?» ብሎ ይጠይቃል:: የቤቱ አባወራም የዘፀአትንና የእግዚአብሔር ሕዝብ በክብር ነጻ የወጡበትን ታሪክ ይተርካል:: እስከምናውቀው ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጠቀሰው በላይኛው ክፍል ወጣት አልነበረም:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከዚህ የእራት ግብዣ ደረጃ ላይ

[34] የፋሲካ በዓል ሲከበር ደንቡ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ዘፀ 12፤ ዘሌ 23÷4-8፤ ዘኍ 9÷1-14፤ ዘዳ 16÷1-8 ይመልከቱ፤ እንዲሁም Rabbi D. Cohn-Sherbok, "A Jewish Note on *TO POTERIN TES EULOGIAS*," *NTS* 27 (1980-81): 704-709 እና G.J. Bahı, "The Seder of Passover and the Eucharistic Words," *NovT* 12 (1970): 181-202 ይመልከቱ:: ይሁን እንጂ B.M. Bosker የፋሲካ ምግብ ከ70 ዓ.ም. በኋላና (ከቤተ መቅደሱ መፍረስ በኋላ) በመለወጥ ላይ ይገኝ የነበረን የአይሁድ ፍላጎትንም ለማሟላት ሲባል ከ135 ዓ.ም. በኋላ (ሮም ላይ ከተነሣው ከሁለተኛው ዓመፅ በኋላ) ይበልጥ የተለወጠ መሆኑን ያስገነዝባል ("Was the Last Supper a Passover Seder?" *BR* [Summer, 1987]: 24-33). F.C. Senn ደግሞ ይበልጥኑ ርቆ በመንዝ ከመካከለኛው ዘመን ቀደም ያሉ [illegible]ካ ምግብን የሚያወሱ ጽሑፎች የሉም ይላል:: ስለዚህ አንዳንድ ክርስ[illegible]ችን የሚከነክን ቢሆንም እንኳ፣ የዘመኑ የአየሁድ የፋሲካ ምግብ ሥርዐት ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከተለማመዱት የፋሲካ ምግብ የተለየ ሊሆን ይችላል:: ከዚህም በላይ የጌታ እራት ርጉም የአይሁድ የፋሲካ ምግብ ታሪካዊ ማስታወሻ በቅዱስ ቊርባን ላይ በሚቀርቡት ነገሮች አማካይነት የክርስቶስ የቤዛነት ሥራ ልብ የሚባልበት ማስታወሻ ነው በማለት ሐሳብ ያቀርባል (ከF.C. Senn, "The Lord's Supper, Not the Passover Seder," *Worship* 60 [1986]: 362-368 ጋር ያነ):: M. Cook የጌታ እራት ሥርዐት ከአይሁድ እይታ አንጻር ሲታይ ሚናውን የሳተና ተገቢ ያልሆነ ነው በማለት አይሁድ የፋሲካ በዓልን በማክበር ረገድ ክርስቲያኖችን ማገዝ የለባቸውም በማለት ሽንጡን ገትሮ ይሟገታል:: "Christian Appropriation of Passover: Jewish Responses Then and Now," *LexTQ* 34/1 (1999): 13-40.



ሲዳረስ የመጀመሪያውን የወይን ጽዋ አንሥቶ የዘፀአትን እውነተኛ ትርጉም «ለቤተሰቡ» ሳይገልጽ አይቀርም::

ማቴዎስና ማርቆስ አንድ የወይን ጽዋን ሲያወሱ ሉቃስ ሁለት ጽዋዎችን ያወሳል::[35] በተግባራዊነቱ ሲታይ የፋሲካ እራት አራት ጽዋዎችን የያዘ ሲሆን፤ እያንዳንዳቸው በፀዘአት 6፡6-7ሀ ላይ ያለውን ስንኝ ወክለው ይገኛሉ::

ጽዋ ቊጥር 1:- «*እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከግብፃውያን ቀንበር አወጣችኋለሁ::*»

ጽዋ ቊጥር 2:- «*ለእነርሱ ባሪያ ከመሆን ነጻ አወጣችኋለሁ::*»

ጽዋ ቊጥር 3:- «*በተዘረጋች ክንድና በታላቅ ፍርድ እቤዣችኋለሁ::*»

ጽዋ ቊጥር 4:- «*የራሴ ሕዝብ አደርጋችኋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ ...::*»

G.J. Bahr ትክክል ከሆነ ጽዋ ቊጥር 1 ወደ ላይኛው ክፍል ከመግባታቸው በፊት በዋናው ቤት ውስጥ ይሰጣል::[36] ስለዚህ ሉቃስ የሚያወሳቸው ሁለት ጽዋዎች በሁለቱም አቅጣጫ የተሰጡ የፋሲካ ምግብ ይሆናሉ:: ሁለቱም ጽዋዎች ከብርቱው «የደኅንነት ንግግር» ጋር የተያያዙ ናቸው:: ይህ የጌታ እራት በሥርዐትነት በሚገባ እንዲመሠረት ያደርጋል:: አራተኛው ጽዋ የእግዚአብሔርን ሀልዎት

[35] 'የወይኑ ፍሬ' የሚለው ሐረግ በአይሁድ የጸሎት ሥርዓት 'ወይን ጠጅ' የሚለውን ቃል ለመግለጽ የሚውል ነው:: በእርግጥም የወይን ጭማቂ ብቻ ሳይሆን ውሎ አድሮ የኮመጠጠ ነበር:: ይሁን እንጂ የፓለስታይን ዓይነተኛ ው ወይን ጠጅ ከ2-3 እጅ ውሃ ተጨምሮ ብርዝ እንዲሆን የተደረገ ነበር::

[36] G.J. Bahr, "The Seder of Passover and the Eucharistic Words," *NovT* 12 (1970): 181-202 በሚለው ጽሑፉ የአይሁድን የበዓል ምግብ አስመልክቶ የጥንት አገላለጾችን መሠረት በማድረግ ከፍተኛውን የንጽጽር ደረጃ ተንተርሶ ያቀርባል::

ይወክላል:: ኢየሱስ ለሕማማቱ በመዘጋጀት ላይ ሳለ ከአራተኛው ጽዋ ያልተከፈለ መሆኑ (ማቴ 26፥29፤ ማር 14፥25) Carson ይገመታል:: የመሲሐዊው ግብዣ እስኪደርስ (ሉቃ 22፥16፤ ማቴ 26፥29) ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የእግዚአብሔርን ሀልዎት አያከብርም::

ኢየሱስ ቂጣውን ይዞ የምስጋና ጸሎት ጸለየ (*ኢኳራስት - eucharisteo* «ምስጋና አቅርብ» ከዚህም «ኢዩኳሪስት - Eucharist የሚለውን ቃል እናገኛለን):: ይህ አካሉን ይወክላል:: ከዮሐንስ 6፥53-58 በላቀ መልኩ እዚህ ላይ በጥሬ ትርጉሙ አይታሰብም፤ ግልጽነት የጐደለውም አይደለም::

በእነዚህ ሁለት ግልጽ ነገሮች አማካይነት ይህ ዘፀአት ምን ማለት መሆኑን ኢየሱስ ገለጸ:: (1) የኢየሱስን አካልና ደም የሚወክሉት ቂጣውና ወይኑ በውክልና ወደሚሞተው ሞት ያመለክታሉ (ለምሳሌ ኢሳ 53፤ ማቴ 20፥28):: አሁን ከዐሥራ ሁለት ሰዓት በላይ የራቀ አይደለም:: (2) የኢየሱስ ሞት አዲስ ቃል ኪዳንን ይመሠርታል:: የኤርምያስን 31፥31-34 ቃል በተለይ 34ለን ማለትም:- «በደላቸውን ይቅር እላለሁ፤ ኀጢአታቸውንም መልሼ አላስብም» የሚለውን እናስታውሳለን:: «ደም» እና «ቃል ኪዳን» የሚሉት ሁለት ሐሳቦች በአንድ ላይ በሌላ ቦታ ውለው የሚገኙት ሁለት ጊዜ ብቻ ነው (ዘፀ 24፥8፤ ዘካ 9፥11):: እንዲያውም ዘፀአት 24፥8 ሙሴያዊው ኪዳን ደም በማፍሰስ እንዴት እንደ ተሻሻለ ተናገረ:: በዚህ ሁኔታ በኢየሱስ ዘመን ትውፊትን ሕያው አድርጎ የጠበቀ ሚሽናህ (*Pesahim* 10:16) የፋሲካን ወይን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለውን ቃል ኪዳን የሚያጸና የደም ዘይቤ ነው ብሎ ለመተርጐም በዘፀአት 24፥8 ይጠቀማል (Carson, p. 537):: አዲስ ኪዳንም ደም በማፍሰስ ተሻሽሎ ነበር:: ዕብራውያን 9፥22 ምክንያቱን እንዲህ ይገልጻል፤ «በእርግጥ ከጥቂት ነገሮች በስተቀር ሁሉም ነገር በደም መንጻት እንዳለበት ሕጉ ያ ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና::» (3) «ስለ ብዙዎች ... የሚፈስ» የሚሉት ቃሎች («ብዙዎች» ትርጉሙ «ሁሉ» ማለት ነው) ኢየሱስ ምሳሌ ሆኖ የቀረበበትን (ዮሐ 1፥29) የአያሌ የፋሲካ በግ ደም



መፍሰስን ትውስታ በዐሥራ አንዱ አእምሮ ላይ ያጭራሉ:: ምናልባትም ከኢሳይያስ 53፥12 ጋር ሳያያይዙት አልቀሩም፤ «እስከ ሞት ድረስ ሕይወቱን አሳልፎ በመስጠቱ::»

ኢየሱስ በማድረግ ላይ የነበረው ግልጽ ነው:: መታሰቢያ ያደረገው ሕይወቱን፣ ታምራቱን ወይም ትምህርቱን ሳይሆን፣ ሞቱን ነው! ወደ ምድር የመጣበት ቀዳሚ ዓላማ ለዓለም ኀጢአት ለመሞት ነው:: ስለዚህ የቅዱስ ቍርባን (Eucharist) ዓላማ መስቀሉን ማስታወስ ነው (1ቆሮ 11፥26):: ወደፊት ወደ ኢየሱስ ዳግም ምጽአትም ያመለክታል:: ካርል እንዳለው «ወደፊት እናስታውሳለን::[37] የእግዚአብሔር ሀልዎት ምሳሌ የሆነው የመጨረሻው የወይን ጽዋ፣ የበጉን የሰርግ እራት ፍጻሜ በመጠበቅ ላይ ነው (ማቴ 22፥1-14፤ ራእ 19፥6-9፤ እንዲሁም ኢሳ 25፥6፤ 1ሄኖክ 72፥14፤ ማቴ 8፥11፤ ሉቃ 22፥29-30 ይመ):: ከዚህ *ወደፊት* እና *ወደ ኋላ* ምልከታ በላይ የጌታ እራት ራሳችንን እንድንመረምር ወደ ውስጥ (1ቆሮ 11፥27-32) የክርስቶስን አካል አንድነት እንድናውጅም (1ቆሮ 10፥17፤ 11፥17-19) ወደ ውጭ እንድንመለከት ያደፋፍረናል:: ተራና ዐላፊ ነገሮችን የያዘው እንዲህ ያለው ደካማ መታሰቢያ ጊዜ የሚያደርሰውን ጉዳይ በጽናት መቋቋሙ በእርግጥ አስገራሚ ምስጢር ነው::

**§ 147**
**ስለ ጴጥሮስ ክሕደት ትንቢት መነገሩ**
**(ማቴ 26፥31-35፤ ማር 14፥22-31 ሉቃ 22፥31-38፤ ዮሐ 13፥31-38)[38]**

(ዮሐ13)31 ይሁዳ ከወጣ በኋላ፣ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «አሁን የሰው ልጅ ከበረ፤ በእርሱም እግዚአብሔር ከበረ:: 32 እንግዲህ እግዚአብሔር በእርሱ ከከበረ፣ እግዚአብሔር ልጁን በራሱ ዘንድ ያከብረዋል፤ ወዲያውም ያከብረዋል::[38]

---

[37] W.J. Carl, "Mark 14:22-25," *Int* 39 (1985): 296-301.

[38] እዚህ ላይ ማቴ 26፥30 እና ማር 14፥26 ከክፍል 152 ጋር መታከላቸውን እናስተውላለን:: እነዚህ ቍጥሮች ኢየሱስ የላይኛውን ክፍል ትቶ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ሄደ ይላሉ:: ስለዚህ ማቴዎስና ማርቆስ ይህን ትንቢት ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ድባብ ሲወስዱት፣ ሉቃስና ዮሐንስ ግን እዚያው ይተዉታል:: ሁለቱ ወንጌላውያን ይህን ታሪክ በጊዜና በሂደት ቅደም ተከተል ከማስቀመጥ ይልቅ በሴማ (በዋና ሐሳብ) አንጻር ማስቀመጣቸው

33«ልጆቼ ሆይ፤ ከእናንተ ጋር የምቈየው ለጥቂት ጊዜ ነው፤ እናንተም
ትፈልጉኛላችሁ፤ ለአይሁድ፣ *እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ አትችሉም* እንዳልኋቸው፣
አሁንም ለእናንተ ይህንኑ እላችኋለሁ::

34«አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ
ነው፤ እንግዲህ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ:: 35እርስ
በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ
ያውቃሉ::»

36ስምዖን ጴጥሮስ፣ «ጌታ ሆይ፤ የምትሄደው ወዴት ነው?» አለው::

ኢየሱስም፣ «ወደምሄድበት አሁን ልትከተለኝ አትችልም፤ ኋላ ግን
ትከተለኛለህ» ሲል መለሰለት::

37ጴጥሮስም፤ «ጌታ ሆይ፤ አሁን ልከተልህ የማልችለው ለምንድን ነው፧ ስለ
አንተ ሕይወቴንም ቢሆን አሳልፌ እሰጣለሁ» አለው::

38ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰ፤ «ሕይወትህን በእርግጥ ስለ እኔ አሳልፈህ
ትሰጣለህን፧ እውነት እልሃለሁ፤ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ::»

ይሁዳ የላይኛውን ክፍል ትቶ በመሄድ ላይ ሳለ ዮሐንስ ትረካውን ይቀጥላል፤ ይሁዳ ትቶ ሲሄድ ኢየሱስ፣ «አሁን የሰው ልጅ ከበረ» አለ:: ይህም ኢየሱስን በውዳሴ ከፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በስቅለት፣ በትንሣኤና በዕርገቱ ማክበር ያካትታል (ዮሐ 7፥39፤ 12፥16፡23):: ዓለም ስቅለትን ውድቀት አድርጎ ይመለከተዋል፤ ኢየሱስ ግን የመክበሪያ ሥራው አድርጎ ነው የሚያየው:: ይሁዳ ክፍሉን ለቆ በመሄዱ የመጨረሻው «ማክበር» ሊጀመር ይችላል:: ኢየሱስ ወደ «ክብር» ለሚያደርገው እንቅስቃሴ መስቀል የመጀመሪያው ይሆናል::

---

ችግር አይፈጥርም:: ይሁን እንጂ ቶማስና ጋንደርይ (ገጽ 202፣ ማስታወሻ ለ) ኢየሱስ አንድ ትንቢት ብቻ ሳይሆን ሁለት ትንቢቶች ሳይናገር አይቀርም፤ ይኸውም ሉቃስና ዮሐንስ የመጀመሪያውን ትንቢት ሲጽፉ፣ ማቴዎስና ማርቆስ ሁለተኛውን ትንቢት ጽፈዋል በማለት ሐሳብ ያቀርባሉ:: ይህ እውነት ከሆነ፣ እዚህ ላይ በማቴዎስና በማርቆስ የተሰነዘረው ሐሳብ የላይኛውን ክፍል ለቅቀው በሄዱበት ወቅት መሆን አለበት::



በኢየሱስ ሞት፣ ቀብርና ትንሣኤ እግዚአብሔር ራሱ ከብሮአል:: በእነዚህ ድርጊቶቹ ኢየሱስ ለአብ ታዛዥ መሆኑን አሳይቷል:: ከመጀመሪያ አብ የፈቀደውን ዕቅድ ፈጽሞአል::

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በፍቅር «ልጆቼ ሆይ፤» ይላቸዋል:: በኋላም ዮሐንስ የራሱን መንጋ ለመጥራት በዚህ ቋንቋ ተጠቅሟል (1ዮሐ 2፥1:12:28፤ 3፥7:18፤ 4፥4፤ 5፥21):: ኢየሱስ አይቀሬ ለሆነው መለየቱ ሐዋርያቱን ለማዘጋጀት ጥረት ያደረጋል:: ይህ እንግዳ ነገር አይደለም:: ከስድስት ወር በፊት በዳስ በዓል ላይ ስለዚሁ ጉዳይ አይሁድን አስጠንቅቆአቸዋል (ዮሐ 7፥33፤ 8፥21፤ እንዲሁም 12፥35፤ 14፥19፤ 16፥16-20 ይመ):: ነገር ግን መጥፎ ዜናን መቀበሉ ምንጊዜም ያስቸግራል::

በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ወደ አዲስ ርእሰ ጉዳይ ይኸውም ወደ አዲስ ትእዛዝ ተሸጋገረ:: እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ በሚለው ትእዛዝ አዲስ ነገር የለም:: አሮጌው ሕግ ውስጥ ታቅፎ ይገኝ ነበር (ዘሌ 19፥18):: ከዚህም በላይ ይህን ጨምሮ ከሁሉ የበለጠውን ትእዛዝ ምንነት ኢየሱስ ገልጾአል፤ ቊጥሩንም አብራቶአል (ክፍል 103 እና ክፍል 105):: ኢየሱስ ሰውን በሚወድበት መንገድ ፍጹም አዲስ ነው:: ጳውሎስ ሮሜ 5፥7-8 ውስጥ እንዲህ ይገልጸዋል:- «ለጻድቅ ሰው የሚሞት ማግኘት እጅጉን ያዳግታል፤ ለደግ ሰው ሲል ሊሞት የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል:: ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል::» 1ዮሐንስ 3፥16ም (ምናልባት ዮሐንስ ወንጌል 3፥16 ውስጥ እጅግ የላቀው ትርጓሜ ሳይሆን አይቀርም) እንዲህ ይላል:- «ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ ስለ ሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደ ሆነ በዚህ እናውቃለን፤ እኛም ሕይወታችንን ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል::» በእርግጥም ይህ የአማኞች ሁነኛ መለዮ

ይሆን ዘንድ ኢየሱስ ዐወጀ፤ ይኸውም ራሳቸውን በመካድ ሌሎችን እንዲወዱ ነው::

ጴጥሮስ አሁንም ወዴት የመሄድ ጉዳይ አሳስቦታል:: ከዛሬ ሦስት ዓመት ጀምሮ ኢየሱስን በታማኝነት በመከተል ላይ ነው:: እግዚአብሔር መንግሥት እውን የሚሆንበትን ዕለት ለማክበር ተቃርቦአል:: ያ ዕድል አሁን እንዲያመልጠው አይፈልግም! «ጌታ ሆይ፤ የምትሄደው ወዴት ነው?» በማለት ጠየቀ:: ኢየሱስ ይህን ጥያቄ እንዴት አድርጎ ይመልሰዋል?! ይህን ማስተዋሉ ለጴጥሮስ ከባድ ነገር ነው:: ኢየሱስ ምን ይበል? «እንግዲህ ጴጥሮስ ከስቅላቴ በኋላ ለሁለት ቀናት የመጀመሪያው ማረፊያዬ በሞት ለተለዩት ዐመፀኛ ነፍሳት በምሰብክበት ወህኒ ቤት ይሆናል (1ጴጥ 3÷19-20):: ከዚያም ተመልሼ እመጣና ከእናንተ ጋር አርባ ቀን እቆያለሁ (ሐሥ 1÷3):: ከዚያ በኋላ በነጭ ዙፋን ዳግም ከመምጣቴ በፊት (ራእ 19÷11)፣ በቀኙ ወደምቀመጥበት ወደ አባቴ ዙፋን አርጋለሁ» (ማር 16÷19):: ጴጥሮስ ይህን መረዳት የሚችልበት መንገድ የለም:: ኢየሱስ፣ «ወደምሄድበት አሁን ልትከተለኝ አትችልም» ማለቱ በቂ ነው:: ጴጥሮስ ወደ ሰማዕትነት ኢየሱስን ይከተለዋል:: በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት በ68 ዓ.ም. ኔሮ በስቅላት ገደለው:: ጴጥሮስ ጌታው በሞተበት መንገድ ይሞት ዘንድ የሚገባው ሆኖ አላገኘውም፤ ስለዚህ ተዘቅዝቆ እንዲሰቀል ጠየቀ:: ጥያቄውም ተሟላለት:: ከዚያም ጴጥሮስ ከሌሎች ሰማዕታት ጋር ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ኢየሱስን ተከተለው (ራእ 6÷9-11)::

ማቴ 26÷31-33

[31]ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ «ሁላችሁም በዚህች ሌሊት በእኔ ተሰናከላችሁ ትሄዳላችሁ፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤ «*እረኛውን እመታለሁ፤ የመንጋም በጎች ይበተናሉ*::
[32]ነገር ግን ከተነሣሁ በኋላ ቀድሜአችሁ ወደ ገሊላ እሄዳለሁ::»



[33]ጴጥሮስም መለሰ፣ «ሌሎች በሙሉ ባንተ ምክንያት ቢሰናከሉ እንኳ እኔ በፍጹም አልሰናከልም!» አለው::

ሁሉም ነገር በፍጥነት እየተከናወነ ነው:: ዘመናትን ያስቈጠረው ዕቅድ እያንዳንዱ ጉዳይ በሚያስደንቅ ፍጥነትና ትክክለኛ ነት እየተከናወነ ነው:: እንደ ይሁዳ ዐሥራ አንዱም የሚጫወቱት የየራሳቸው ሚና አላቸው፤ የእነርሱ ሚና ግን እንደ እርሱ የጐላ አይደለም:: በዘካርያስ 13÷7 መሠረት በጌቴሴማኒ ዐሥራ አንዱ ትተውት እንደሚሸሹ ኢየሱስ ተነበየ (ማቴ 26÷56፤ ማር 14÷50):: በዘካርያስ 13÷7 ጽሑፍ ላይ ጉልሕ ልዩነቶች አሉ:: ይኸውም በሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና በአዲስ ኪዳን መካከል ማለት ነው:: የዘካርያስ 13÷7ን የመጀመሪያ ዐውድ ምንነት አስመልክቶም አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ (በኀጢአታቸው የተመቱትን የእስራኤል ገዦች/እረኞች የሚመለከት ይመስላል፤ እነዚህ ገዦች ደግሞ ከኢየሱስ ጋር አይመሳሰሉም):: ሆኖም እነዚህ ችግሮች ትንቢቱን ምስያ አድርጎ በመመልከት የሚፈቱ ይመስላል:: በሌላ አገላለጽ ኢየሱስ የአይሁድ ገዦች ሁሉ ተቃራኒ የሆነ አማናዊ ንጉሥ ነው:: ዐሥራ አንዱ ደግሞ እስራኤልን ይወክላሉ:: እስራኤላውያን ገዥዎቻቸውን ባጡ ጊዜ ተበታተኑ:: እንደዚሁም ሐዋርያት ኢየሱስን ባጡ ጊዜ ተበታተኑ:: የዘካርያስ 13 ዐውዳዊ ዝርዝር ሁሉ የአሁኑን ሁኔታ የሚመለከት አይደለም::

ሳያደርግ አይቀርም ተብሎ ሊታሰብ እንደሚችለው ጴጥሮስ በብርቱ ተቃወመ:: እነዚህ ተታላዮች ቢያፈገፍጉም እንኳ፣ እኔ ግን ታማኝ ሆኜ እጸናለሁ በማት ተናገረ:: የጴጥሮስ እኔ ከቶ አላደርገውም ዐይነት ንግግር በወዳጆቹ ዘንድ ከበሬታን አላስገኘለትም:: ሁሉ ነገር በደረሰ ጊዜ የእርሱ ክሕደት ከሌሎቹ ይልቅ ይበልጥ ጉልሕ ይሆናል::

31 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «ስምዖን፣ ስምዖን ሆይ፤ እነሆ፣ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ 32 እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ።» — ሉቃ 22÷31-33

33 ስምዖንም፣ «ጌታ ሆይ፤ እኔ ከአንተ ጋር ወኅኒ ለመውረድም፣ ለመሞትም ዝግጁ ነኝ» አለው።

30 ኢየሱስም፣ «እውነት እልሃለሁ፤ በዚህች ሌሊት ዶሮ ሁለት[a] ጊዜ ሳይጮኽ፣ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» አለው። — ማር 14÷30-31

31 ጴጥሮስም፣ «ከአንተ ጋር ብሞት እንኳ ከቶ አልክድህም» በማለት ይበልጥ አጽንቶ ተናገረ። ሁሉም ደግሞ እንደዚሁ አሉ።

*[a] 30 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሁለት ጊዜ የሚለው ሐረግ የላቸውም።*

ኢየሱስ የጴጥሮስን የቀድሞ ስም በመጠቀምና ሁለት ጊዜ በዚሁ ስሙ በመጥራት ጴጥሮስ ልብ ብሎ እንዲሰማው አደረገ። በጣም አስፈላጊ ነገርም ነው፤ ጴጥሮስ ኢየሱስ አሁን ሊነግረው የፈለገውን ይሰማ ዘንድ ያስፈልገዋል፤ ይህ ለአሁኑ ብቻ ሳይሆን ለሚመጣው አገልግሎቱም ነው። ሉቃስ፣ «ለመነ» (ቁ. 31) በማለት የተጠቀመው ቃል ሰይጣን የጠየቀውን ማግኘቱን ያመለክታል። በሌላ አነጋገር ጴጥሮስ በጠላት እጅ ሥር ነው። ይህ ትዕይንት ከአስቆሮቱ ይሁዳ ጋር እንዲነጻጸር ታስቦአል። ድርጊታቸው ሙሉ በሙሉ የተለየ ባይሆንም እንኳ፣ ለኢየሱስ የነበራቸው ፍቅር የሰማይንና የምድርን ያህል የተራራቀ ነበር። ስለዚህ ንስሓቸውና የንስሐቸው ውጤቶች በእጅጉ የተራራቁ ናቸው።

ሰይጣን በጴጥሮስ ላይ ያለው ቁጥጥር በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሆነ ነው። ጴጥሮስ እንዲበጠር እንጂ እንዲጠፋ እግዚአብሔር



አይፈቅድም (ዮሐ 10÷29)። ሰይጣን አንድን ግለሰብ ለመጉዳት እንደሚያወጣቸው ሌሎች ዕቅዶች ሁሉ፣ እግዚአብሔር የጴጥሮስን ጉድለት ለማንጻትና ፍጹም ለማድረግ ተጠቀመበት። ስለዚህ ኢየሱስ ስለ ጴጥሮስ ያቀረበውን ጸሎት እግዚአብሔር ሰማ። ጴጥሮስ ቢሳሳትም እንኳ እምነቱ እንጻለ ነበር። እምነቱ ወደ ንስሐ መራው፤ ንስሐውም ወደ ብርታት መራው፤ ብርታቱ ደግሞ ወደ ክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ በመሠራጨት እስከዛሬም እንደ ዘለቀ ነው። ጴጥሮስ ለብዙዎቻችን የይቅርታና የዕርቅ ምሳሌ ሲሆን፣ በእምነት፣ በፍቅርና በጽናት ረገድ ደግሞ እያደር በግል መሻሻል እንደሚኖር የሚያሳይ አርአያችን ነው። በጴጥሮስ በኩል የራሳችንን የእምነት ጉዞ እናያለን።[39]

ነገር ግን ጴጥሮስ አሁንም ይቃወማል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የሚለው ነገር፣ «ኢየሱስ ሆይ፤ ተሳስተሃል!» ነው። ለኢየሱስ እታሰራለሁ፤ ዐልፎ ተርፎም እሞታለሁ አለ። በእርግጥ ፈቃደኛ ነው። የሮማውያንን ጦር በሁለት ሰይፍ ለመቋቋም የተነሣን ሰው (ሉቃ 22÷38-50) ድፍረት (ስሕተትና ግንፍልነት ያለበት ቢሆንም እንኳ) ማን ጥያቄ ውስጥ ያስገባል? እንዲህ ያለ ደቀ መዝሙር ኢየሱስን እንዴት ይክደዋል? ነገሩ በእርግጥ ግልጽ ነው። ታምር የመሥራት ኀይል ላለው መሲሕ ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ነው። ሆኖም ኢየሱስ ሰይፉን እንዲያስገባ በነገረው ጊዜ (ማቴ 26÷52) ጴጥሮስ በእርግጥ የሚያውቃቸውንና የተማመነባቸውን ነገሮች እጁ ውስጥ አስገባ። ለሕይወቱ ለመዋጋት እንጂ፣ ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለም።

የኢየሱስ ትንቢት በይበልጥ ግልጽ እየሆነ መጣ:- ከ12 ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ባለው ወቅት ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ። ፖሊስትና ውስጥ ዶሮ የሚጮኽው ሮማውያን ሦስተኛ ሰዓት ብለው

[39] J. Thompson, "The Odyssey of a Disciple, *RestQ* 23 (1980): 77-81.

በሰየሙት ጊዜ ነው (ከ12 ሰዓት እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት):: ያን ሰዓት፣ «ዶሮ ሲጮኽ» በማለት ሰየሙት:: ጴጥሮስ ይህን አላመነምና ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የራሱ የሆነውን ሰው አምርሮ እንደሚክድ ሁሉ የኢየሱስን ቃል አምርሮ ካደ:: የቀሩት ዐሥሩ ከጴጥሮስ ጋር ሆነው ኢየሱስን ካዱ:: እነርሱም ቢሆኑ ይህን ማመን አልቻሉም! ይሁን እንጂ ብዙ ሳይራቅ የኢየሱስ ትንቢት የቱን ያህል ትክክል እንደ ሆነ ማንም ሳያሳምናቸው ራሳቸው ያምኑታል:: ጴጥሮስ ለሦስተኛ ጊዜ ኢየሱስን በሚክድበት ሰዓት አውራ ዶሮው ለሁለተኛ ጊዜ ይጮኻል፤ በወሳኙ ሰዓት የሁለቱ ዐይኖች ይገጣጠማሉ (ሉቃ 22÷60-61)::

**ሉቃ 22÷35-38**

[35]ከዚያም ኢየሱስ፣ «ያለ ኰረጆ፣ ያለ ከረጢትና ያለ ጫማ በላክኋችሁ ጊዜ የጐደለባችሁ ነገር ነበርን?» ብሎ ጠየቃቸው::

እነርሱም፣ «ምንም አልጐደለብንም» አሉ::

[36]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «አሁን ግን ኰረጆም፣ ከረጢትም ያለው ሰው ይያዝ፣ ሰይፍ የሌለውም ልብሱን ሸጦ ይግዛ:: [37]እላችኋለሁና፣ *ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ* ተብሎ የተጻፈው በእኔ መፈጸም አለበት፤ እስ በኔ የተጻፈው ፍጻሜው በእርግጥ ደርሶአል::»

[38]ደቀ መዛሙርቱም፣ «ጌታ ሆይ፤ እነሆ፤ ሁለት ሰይፎች እዚህ አሉ» አሉት::

እርሱም፣ «ይበቃል» አላቸው::

ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን (ማቴ 10) ሰባ ሁለቱን (ሉቃ 10) ያለትርፍ ገንዘብ ያለ መቀየሪያ ልብስ፣ ወይም ያለ መከላከያ መሣሪያ ላካቸው:: ነገር ግን ጊዜው ተለውጦአል:: እየተነጋገርን ያለነው በሚታወቁ ጐረቤቶች ዘንድ ስለሚዘዋወሩት የቆየ ወንጌላውያን አይደለም:: በመነጋገር ላይ ያለነው ተቃውሞ ባለበት ዳራ ብዙ ጊዜም ጕልሕ ስደት ባለበት ስፍራ ስለሚካሄደው ዐለም አቀፋዊ ምርኮ ነው::



ኢሳይያስ 53÷12 ውስጥ በትንቢት እንደ ተነገረው ኢየሱስ እንደ ወንጀለኛ ተቈጥሮአል::[40] ተከታዮቹም እንደ ዐመፀኞች ይቈጠራሉ:: እነዚህ ተጨማሪ ማሳሰቢያዎች በእነዚህ አዳዲስ ሁኔታዎች ውስጥ በጣም አስፈላጊ ይሆናሉ::

ኢየሱስ እንዲያመጡ የነገራቸው ሰይፎች አንዳንድ አሳሳቢ ሁኔታዎችን አስከትለዋል:: እዚህ ላይ ስለ «ቅዱስ» የመስቀል ጦርነት እየተነጋገርን ነውን? አይደለም! እነዚህ ሰይፎች ለጦርነት (ለወረራ) መዋል እንደሌለባቸው ኢየሱስ ግልጽ አድርጎአል (ከዮሐ 18÷10-11 ጋር ያነ):: እንዲያውም ጴጥሮስ ሰይፉን አውጥቶ ማልኮስን ሲያጠቃ፣ ኢየሱስ ሰይፉን ወደ ሰገባው እንዲያስገባ አዞታል (ማቴ 26÷52):: አስቸጋሪ ነገር ሲያጋጥመን ችግሩን በራሳችን ጕልበት እንድንወጣው እነዚህ ሰይፎች ያመለክታሉን? ሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለው ምሳሌ የሚያሳየው ስለ አለመቀበልና (ከማቴ 5÷39 ጋር ያነ) በሥልጣን ላይ ላሉት ገዦች ስለ መገዛት ነው (ከሮሜ 13÷1-5 ጋር ያነ):: ለምሳሌ ጴጥሮስና ዮሐንስ የቤተ መቅደሱን ጠባቂዎች ያስቆሟቸው ዘንድ ሕዝቡን ማነሣሣት ይችሉ ነበር፤ ነገር ግን ድምፃቸውን አጥፍተው ሹልክ ብሎ መውጣትን ነው የመረጡት (ከሐሥ 4÷1-4 እና 5÷26-27 ጋር ያነ):: ታዲያ እነዚህ ሰይፎች ለምን ያገለግላሉ? አላስፈላጊ ስደትን ሊመልሱ ይችላሉ፤ ረብሻ ሊያነሣሡ የሚችሉትንም ያስገድዳሉ:: ለሽርሽር ቦታና ለማዕድ ቤት አገልግሎት የሚውሉ ስለቶች ሳይሆኑ አይቀሩም:: የገቡበትን መንደር የአካባቢ ጥበቃ ድጋፍ ካላገኙ፣ በዚህ ጊዜ ራሳቸውን መከላከል አለባቸው:: ስለዚህ ይህ ሰይፍ ለጕዞ የሚያስፈልግ ዕቃ ሆኖአል::

[40] ኢሳይያስ ምዕራፍ 53 በሌሎች ስፍራዎች በአዲስ ኪዳን ላይ ስለ መጠቀሱ ከማቴ 8÷17፤ ከዮሐ 12÷38፤ ከሐሥ 8÷32-33፤ ከሮሜ 10÷16፤ ከ1ጴጥ 2÷22 ጋር ያነጻጽሩ::

ደቀ መዛሙርቱ ወዲያውኑ «አብዮታዊ» ንግግር አደረጉ፤ በእጃቸው ላይ ያሉት (በኮሮጆአቸው) ሁለት ሰይፎች ብቻ መሆናቸውን ለኢየሱስ ነገሩት:: ኢየሱስም «ይበቃል» አላቸው::

## አንድ ደርብ ባለው ቤት የተደረገ ንግግር

ይህ የኢየሱስ የስንብት ንግግር ነው::[41] በሚቀጥሉት አራት ምዕራፎች ውስጥ (ዮሐ 14-17) ኢየሱስ ሦስት ወሳኝ እውነቶችን ማስጨበጥ ይኖርበታል:-[42] (1) ሊሄድ ነው (ዮሐ 13፥1:31-33:36፤ 14፥1-4:18:25:27-29፤ 16፥5:11-19:28፤ 17፥11):: (2) ከዓለም ዘንድ ተቃውሞ እያለ ሐዋርያት የኢየሱስን ተልእኮ ይቀጥላሉ (ዮሐ 13፥13-17:20:34-35፤ 14፥12-14:18-21፤ 15፥1-21:27፤ 16፥1-4:23-24፤ 17፥12-22):: (3) መንፈስ ቅዱስ በተልእኮአቸው ያግዛቸዋል (ዮሐ 14፥15-18:26፤ 15፥26-27፤ 16፥6-11:13-14):: ወደፊት ሊያጋጥሙ ከሚችሉ መልካም ዜና (መጥፎ ዜና) መካከል ይህ አንዱ ነው:: ወደፊት ምን ሊያጋጥም እንደሚችል መገመቱ አስቸጋሪ ይሆናል:: ኢየሱስ የሰጣቸው ተስፋዎች ግን ከዚህ ዓለም ውጭ ናቸው!

[41] ይህ በመጀመሪያው ምእት ዓመትና መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታወቅ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ነው (ከያዕቆብ፣ ዘፍ 48-49፤ ከሙሴ፣ ዘዳ 31-34፤ ከኢያሱ፣ ኢሱ 23-24፤ እና ከዳዊት 1ዜና 28-29 ጋር ያነ:: እንደዚሁም ከሉቃ 22፤ ከዮሐ 13-17፤ ከሐሥ 20፥17-38 ንግግሮች ጋር ያነ):: የእነዚህ ንግግሮች ዓላማ የግለሰቡን ሥራና ትምህርት አጠቃሎ ለማቅረብ አስፈላጊ ከሆነም ለሕይወታቸው የሚሆነውን ዐቃቤ እምነት ለማዳበርና የአንድን ሰው ሕይወት አርአያነት አገልግሎት ላይ ለማዋል ነው:: ብዙ ጊዜ አሳሳቢ ጉዳዮች በሆኑ ማኅበረሰባዊ ችግሮች ላይ አጽንዖት ይደረጋል፤ ተተኪዎችም ሥራውን ተረክበው እንዲቀጥሉ ዐደራ ይሰጣቸዋል:: [R.W. Paschal, "Farewell Discourse," in *Dictionary of Jesus and the Gospels,* ed. by Joel B. Green, Scot McKnight, I. Howard Marshal (Downers Grove, IL: InterVarsity, 1992), pp. 229-233.]

[42] G.D. Fee, "John 14:8-17," *Int* 43 (1989): 170-174.



**§ 149**
**ኢየሱስ ወደ አብ ሄደ፤ መንፈስ ቅዱስንም ላከ**
**(ዮሐ 14)**

1«ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ[ኸ]፤
በእኔም ደግሞ እመኑ:: 2በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤
ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም
ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው:: 3ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ
በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ
ልወስዳችሁ ደግመኛ እመጣለሁ:: 4እኔ ወደምሄድበትም
ስፍራ የሚያደርሰውን መንገድ ታውቃላችሁ::»

*[ኸ]1 ወይም እናንተ በእግዚአብሔር ታምናላችሁ*

ይህ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከበላው ምግብ ከሌላው ምግብ የተለየ ነበር:: በመሆኑም የታወከና ጸጥ ያለ ይመስላል:: በፋሲካ በዓል አከባበር ላይ መጥሮ ነገር እያንዣበበ መሆኑን የሚያመለክት ነገር ይታያል፤ «ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል» የሚለውም በአእምሮአቸው ማቃጨሉን ቀጠለ:: ጴጥሮስ ሦስት ጊዜ እንደሚክደው ኢየሱስ ነግሮታል፤ የቀሩት ዐሥሩም በዚህ ረገድ ከእርሱ የተሻሉ አይሆኑም:: ፍርሃት የገባቸው መሆኑ በገሐድ ይታያል:: ስለዚህ ኢየሱስ ልባቸው እንዳይታወክ ነገራቸው::[43] ከሁለት ተጨማሪ ትእዛዞች ጋር[44] ኢየሱስ መፍትሄውን ይሰጣል:- በእግዚአብሔር እመኑ፤ ደግሞም በእኔ እመኑ!

መስቀልና ዕርገት ለደቀ መዛሙርቱ ከባድ እጦት ቢያስከትሉም፣ እምነታቸው በአሁኑ ሥቃይ መካከል በሦስት የክብር እውነታዎች አማካይነት እንዲጸና ይደረጋል:- (1) መንፈስ ቅዱስ

[43] የዚህ ትእዛዛዊ አንቀጽ አገባብ [ሜ - *me* የአሁን ጊዜ ትእዛዝ] አሁን በመሠራት ላይ ያለው መቆም እንዳለበት ያሳያል::

[44] «በእግዚአብሔር እመኑ» የሚለው «አሁንም በእግዚአብሔር እያመናችሁ ነው» የሚለውን ሊመለክት ይችላል:: ሆኖም የአዲሱ መደበኛ ትርጉም (New International Version - NIV) ጽሑፍ ሁለቱንም ትእዛዛዊ አንቀጽ አድርጎ በመተርጐሙ የላቀ እሳቤ ይሰጣል::

በዘላቂነት በእነርሱ ላይ በማደሩ፣ (2) በኢየሱስ መመለስ እና (3) የሰማይ ቤት ተስፋ ይህ ማደሪያ ቦታ ፍልስጥኤማውያን ግቢ ውስጥ በሚገኘው አዳራሽ ዙሪያ ካሉት ክፍሎች አንዱን ይወክላል:: ቤቱ ግዙፍ ቢሆንም ክፍሉ ውብ ሊሆን ይችላል:: የኪንግ ጀምስ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም (KJV) «ማንሽን» "mansion" ሲል፣ በአሁኑ ዘመን ትክክል የሆነ ፅንሰ ሐሳብ ላይሰጥ ይችላል:: የወደፊት ቤታችን ክብር (ሞገስ) የሚገኘው በመጠኑና በክብሩ ሳይሆን በክርስቶስ ሀልዎት ነው::

[5]ቶማስ፣ «ጌታ ሆይ፤ ወዴት እንደምትሄድ ዮሐ 14÷5-7
አናውቅም፤ ታዲያ፣ መንገዱን እንዴት ማወቅ
እንችላለን?» አለው::
[6]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው
ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም:: [7]እኔን ብታውቁኝ ኖሮ
አባቴንም ባወቃችሁት ነበር::[ሠ] ከአሁን ጀምሮ ግን ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁታልም::»

*[ሠ]7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በእርግጥ እኔን ብታውቁ አባቴንም ታውቃላችሁ ይላሉ::*

ቶማስ ኢየሱስን በየትኛውም ቦታ ለመከተል ቈርጦ ተነሥቶአል:: እንዲያውም ቀደም ሲል ኢየሱስ ወደ ይሁዳ በተመለሰ ጊዜ ድርጊታቸው ላይ ሞት ሊያስከትልባቸው ቢችልም እንኳ፣ ተከትለውት ይጓዙ ዘንድ ሌሎችን ደቀ መዛሙርቱ አደፋፍሮአል (ዮሐ 11∃6):: ነገር ግን ኢየሱስ የት እንደሚሄድ ወይም እሄዳለሁ ወዳለበት ቦታ የሚወስደውን መንገድ ካላወቀ ቶማስ ሊከተለው አይችልም:: ስለዚህ ሐዋርያቱ መንገዱን እንደሚያውቁ ኢየሱስ ይፋ ባደረገ ጊዜ ቶማስ ሊያርመው እንደሚገባው ተሰማው::

እግዚአብሔርን «ለማግኘት» ወዴት እንሄዳለን≅ እርሱ የትም የሚገኝ መንፈስ ነው:: እርሱን ለመገናኘት ሲባል የሚጓዙበት የተለየ



ቦታ የለም:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ራሱ በጉልሕ ይገልጣል (ራእ 21÷3):: አሁን እንኳ ኢየሱስ የእግዚአብሔር «መገለጥ» መላእክትና ሽማግሌዎች ዙሪያውን ባሉበት (ራእ 4-5) ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በመመለስ ላይ ነው:: ኢየሱስ አሁን ወደዚያ መጓዝ ሲችል የቀረነው ግን መጠባበቅ ይኖርብናል:: ይሁን እንጂ ራሳችንን የፍርድ ዙፋን ሆኖ በተለወጠው ፊት ቆሞ እናገኘዋለን:: ከዚያ መድረስ ችግር አይደለም፤ ጥያቄው ከዚያ በደረስን ጊዜ የት ነው የምንቆመው የሚለው ነው:: ወደ አብ የሚወስደው መንገድ ሳይሆ ግንኙነት ነው:: በዚያ ቀን በአብ ፊት መቆም የምንችለው በኢየሱስ ብቻ ነው:: ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለውን አንድነት ከገለጸለትና በትንሣኤውና በዕርገቱም ገልጦ ካሳየው በኋላ፣ ቶማስ ጥያቄ አልነበረውም::

የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳይኖር መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው:: ክርስትና ለሰው ሁሉ ክፍት ሲሆን፣ መንግሥተ ሰማይ ግን አይደለም! ከኢየሱስ አንደበት የወጣ እውነት ነው እስካላችሁ ድረስ፣ አርቆ አለማስተዋል ነው፤ ትዕሥት አልባት ነው፤ ወይም ያሻችሁን በሉት:: እርሱ እንዲህ አለ፤ «መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም::» አንድ ሰው ጫካ ውስጥ የጠፋን ወይም በዐውሎ ነፋስ በምትናወጥ መርከብ በመስጠም ላይ ያለን አንድ ልጅ ወደ ጠረፍ ቢመራው ጀግና እንጂ አክራሪ አይባልም:: መለኮትነቱን በትንሣኤው ያረጋገጠው ኢየሱስ ችላ ማለት የሌለብንና ታይቶ የማይታወቀውን ብቻና እውነት ይፋ አድርጎአል::

ይህ ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከሰባቱ «እኔ ነኝ» ስድስተኛው ነው (6÷48፤ 8÷12፤ 10÷9፤ 10÷11፤ 11÷25፤ 15÷1):: ኢየሱስን «መንገዱ» ብሎ የሚጠራው የመጀመሪያ ገለጻ ከመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ስሞች አንዱ ሆነ (ሐሥ 9÷2፤ 19÷9:23፤ 22÷4፤ 24÷22):: ኢየሱስን

የሚገልጹት ሁለተኛውና ሦስተኛው ገለጻዎች (እውነትና ሕይወትም)፣ ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ በሌሎች ብዙ ቦታዎች ይገኛሉ:-

| ኢየሱስ **እውነት** ነው | ኢየሱስ **ሕይወትም** ነው |
|---|---|
| ዮሐ 1፥14:17፤ 5፥33፤ 7፥18፤ 8፥32:40:44-46፤ 18፥23:37-38 | ዮሐ 1፥4፤ 3፥15-16:36፤ 5፥21-26:39-40፤ 6፥40፤ 10፥10:28፤ 17፥2፤ 20፥31 |
| መንፈስ ቅዱስ እውነት ነው (14፥17፤ 15፥26፤ 16፥13) | መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ነው (6፥63) |
| የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው (17፥17) | የእግዚአብሔር ቃል ሕይወት ነው (6፥68) |
| «እውነት እላችኋለሁ» (በዮሐንስ ወንጌል ብቻ 24 ጊዜ) | «ሕይወቴንም . . . አሳልፌ እሰጣለሁ» (10፥11:15-17፤ 15፥13) |
| | ሕይወትን የሚያመለክቱ ሌሎች ማጠቃሻዎች:- እንጀራ (6፥33-35:47-54) ውሃ (4፥14)፣ ብርሃን . . . ነኝ (8፥12) |

**ዮሐ 14፥8-14**

[8]ፊልጶስም፣ «ጌታ ሆይ፤ አብን አሳየንና
ይበቃናል» አለው::
[9]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «አንተ ፊልጶስ!
ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን?
እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ፣ *አብን አሳየን*
ትላለህ? [10]እኔ በአብ እንዳለሁ፣ አብም በእኔ እንዳለ
' ' ምንምን? የምንነግራችሁ ቃል ከራሴ አይደለም፤ ነገር
ነገ ሥራውን
የሚሠራው በእኔ የሚኖረው አብ ነው:: [11]እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ
ስነግራችሁ እመኑኝ፤ ቢሳው ቢቀር ስለ ድንቅ ሥራዎቹ እንኳ እመኑ:: [12]እውነት



እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ ይሠራል፤ እንዲያውም እኔ ወደ
አብ ስለምሄድ፣ ከእነዚህም የሚበልጥ ያደርጋል:: [13]አብ በወልድ እንዲከብር፣ በስሜ
የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ:: [14]ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ፣ እኔ
አደርገዋለሁ::»

ቀጥሎ ፊልጶስ ኢየሱስን ሲጠይቅ እናገኘዋለን::[45] ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ስለ ፊልጶስ በውልብታ መልክ የቀረቡ ሦስት ገለጻዎች አሉ:: በግልጽ እንደሚታወቀው ቀደም ሲል በመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን በመጀመሪያ ኢየሱስን ከተከተሉት መካከል ፊልጶስ አንዱ ነበር (ዮሐ 1፥43-46):: ለኢየሱስ የነበረውን ታማኝነት ሲገልጽ በመጀመሪያ ያደረገው ወደ ናትናኤል ጌታን መምራት ነበር:: ከሁለት ዓመት በኋላ አምስት ሺህ ሰዎችን ስለ መመገብ በተመለከተ፣ እነዚህን ሁሉ እንዴት መመገብ እንደሚቻል ኢየሱስን የጠየቀው ፊልጶስ ነበር (ዮሐ 6፥5-7):: በመጨረሻም ዮሐንስ 12፥21 ውስጥ ኢየሱስን ለማየት የፈለጉ የግሪክ ሰዎች ወደ እርሱ ይወስዳቸው ዘንድ ፊልጶስን ለመኑት::

ፊልጶስ እግዚአብሔርን በገሐድ ለማየት ፈለገ:: እንደ ሕዝቅኤል (1-2) ወይም እንደ ኢሳይያስ (6)፣ እንዲያውም እንደ ሙሴ ያለ (ዘፀ 33፥18-23) ራእይ ለማየት ሳያስብ አልቀረም:: ነገር ግን ኢየሱስ ለፊልጶስ ከሚያስፈልገው ያነሰ፣ ወይም ከራሱ ዝቅ ያለ አልሰጠውም:: ኢየሱስን ማየት አብን ማየት ነው (ዕብ 1፥3):: ይህም የኢየሱስ ትሥጉታዊ ቅርጽ እንደነዚህ የእግዚአብሔር ራእዮች ማራኪ አለመሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ነው:: አሁንም ቢሆን ትሥጉታዊው ቅርጽ ትሥጉት እንዳልሆነው ቅርጹ ማራኪ አልነበረም (ኢሳ 11፥3-5፤

---

[45] J.M. Reese በዮሐንስ 13-16 ላይ ዘላቂ የሆነ በሦስት ምድብ የተከፈለ አካሄድ ያለ መሆኑን ግልጽ ያደርጋል፤ ይኸውም ኢየሱስ አንድ መገለጥን ይሰጣል፤ ኢየሱስ ምን ማለቱ እንደ ሆነ አንድ ደቀ መዝሙር ተያያዥነት የሌላቸውን ጥያቄዎች ያቀርባል፤ ከዚያም ኢየሱስ ያ ሐሳብ ምን ማለት እንደ ሆነ ያብራራል ("Literary Structure of John 13:31-14:31; 16:5-6:16-33," *CBQ* 34 [1972]: 321-331.

ሕዝ 40፥3፤ ዳን 10፥6፤ ራእ 1፥12-16)። ይሁን እንጂ እዚህ ላይ የተፈለገው ማራኪ ራእይ ሳይሆን፣ ትክክለኛ የሆነ የእግዚአብሔር ባሕርይ፣ ዐላማና ሥራ መገለጥ ነው። እነዚህ በቃሉና (ቊ 10) በሥራው (ቊ 11) በኩል በኢየሱስ ትሥጉታዊ አገልግሎት ተወክለው ይገኛሉ፤ ሁለቱ በቀጥታ የመጡት ደግሞ ከአብ ነው (ዮሐ 5፥18-23:36-39፤ 8፥41-42፤ 10፥30-32:37-38፤ 12፥49-50)። ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከዳር እስከ ዳር የኢየሱስ ታምራቶች የእኔነቱ መገለጫዎች ሆነው ቀርበዋል (ዮሐ 9፥31-33፤ 10፥37-38፤ 11፥39-43፤ 20፥30-31፤ ከሐሥ 2፥22፤ ከ2ቆሮ 12፥12 ጋር ያነ)።

ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለው አንድነት የሚያስደንቅ ነው (ዮሐ 1፥8፤ 10፥38፤ 14፥10:20፤ 17፥21)። ይበልጥ አስደናቂ የሆነው ጉዳይ ግን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ያለው ጥብቅ ኅብረት ነው። ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ በፈጸመ ቊጥር፣ አባቱ ዲበ ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ ኀይልን አስታጠቀው። እንዲሁም የኢየሱስን የዐደራ ትእዛዛች ስንፈጽም የአብ ኀይል በእርሱ በኩል ወደ እኛ ይፈሳል። እንዲያውም የደቀ መዛሙርቱ ሥራ ከእርሱ ሥራ የላቀ እንደሚሆን ኢየሱስ ተናግሮአል። እንግዲህ አንዱ የኢየሱስ ተግባር ታምራትን መፈጸም ነበር (ቊ 11)። እዚህ እንደ ሆነው ሁሉ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥም በጸሎትና በተምራት መካከል ጥብቅ ትስስር አለ (ከሐሥ 4፥31፤ 6፥6-7፤ 8፥15፤ 9፥11:40-41፤ 10፥4፤ 11፥5፤ 12፥5፤ 13፥3፤ 16፥25-34፤ 28፥8 ጋር ያነ)። ነገር ግን ኢየሱስ ሐዋርያቱ ከእርሱ የላቀ ሥራ ይሠራሉ ሲል፣ በሐሳቡ ውስጥ የነበረው ታምር ብቻ ነበር ማለት አይደለም። እንግዲያውስ አንድን ሰው ከሞት ከማስነሣት የላቀ ምን ተ፟ምር አለ? ኢየሱስም ከነዚህ ሦስቱን ፈጸመ (የራሱን ሳይጨ፡ምር)፤ «ዐበይት» የሆኑት ሐዋርያት ጴጥሮስና ጳውሎስ እያንዳንዳቸው ከሞት ያስነሡት ሰው አንድ ብቻ ነው (ሐሥ 9፥40-41፤ 20፥10)። ርግጥ ነው የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ታላቅነት የሚታየው በአከናወኑት ታምር ብዛት ወይም ጠባይ ሳይሆን፣ ከሞት



ወደ ሕይወት በመለሱአቸው ሰዎች ብዛትና ባሕርይ (ጠባይ) ልክ ነው። ከማንኛውም ልሳንና ነገድ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት፣ የመልክዐ ምድርነና የጕሣን ገደብ የሚሰብሩ ሰዎች ሥራ እንዴት ታላቅ ነው!

ይህን ታላቅ ሥራ ለመፈጸም ጥያቄው የቱንም ያህል ታላቅ ይሁን ኢየሱስ ጸሎታችንን እንደሚሰማ ቃል ገብቶአል። ይህ አስገራሚ ፍላጎታችን ለማርካት የተሰጠ ተስፋ አይደለም። ጕድኝት ከሆኑት ምንባቦች እንደምናየው ኢየሱስ በሰጠው ተስፋ ላይ ወሰኖች አሉ። በእምነት (ማቴ 21፥22) ከሌሎች አማኞች ጋር በመስማማት (ማቴ 18፥19)፣ በኢየሱስ ስም (ዮሐ 14፥13-16፤ 16፥23-26)፣ እንደ ፈቃዱ (1ዮሐ 5፥14-15)፣ ቃሉን እየታዘዝን (ዮሐ 15፥7፤ 1ዮሐ 3፥22)፣ ደግሞም ለእርሱ ፍሬ እያፈራን (ዮሐ 15፥16) መጠየቅ ይኖርብናል። በራስ ወዳድነት መንፈስ ወይም ትክክል ባልሆነ አነሣሽ ምክንያት የምናቀርበውን ጸሎት ተስፋው አይመለከትም (ማር 10∃35፤ ያዕ 4∃2-3)። እግዚአብሔር እንድንጠይቅ የነገረንን ነገር ስንለምነው ጸሎታችንን በእርግጥ ይሰማል። ስለዚህ ምን መጠየቅ ይኖርብናል? ኢየሱስ ቢያንስ ቢያንስ ሦስት ነገሮችን እንድንጠይቅ ነግሮናል፡- መንፈስ ቅዱስን (ሉቃ 11፥13)፣ በመከሩ የሚሠሩ ሠራተኞችንና (ማቴ 9፥38)፣ ጥበብን (ያዕ 1፥5)። ትልቁ ስሕተታችን በአገባቡ አለመጠየቃችን ወይም ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን መጠየቃችን ሳይሆን፣ ፈጽሞ አለመጠየቃችን ነው (11፥9፤ ኤፌ 3፥20፤ ያዕ 4፥2)።

**ዮሐ 14፥15-21**

[15]«ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ። [16]እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል። [17]እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይችልም። እናንተ ግን፣ አብሬአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን ታውቁታላችሁ።

18ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ:: 19ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ዓለም ከቶ አያየኝም፤ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ:: 20እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፣ እኔም ደግሞ በእናንተ እንዳለሁ በዚያ ቀን ትረዳላችሁ:: 21የሚወደኝ ትእዛዜን ተቀብሎ የሚጠብቅ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ::»

*[0]17 ለንዳንድ የጥንት ቀጆች በውስጣችሁ ለሳለ ደባሉ::*

እንደ እውነቱ ከሆነ ክርስቲያን ማለት ኢየሱስን የሚወድ ሰው ማለት ነው:: ሃይማኖታዊ ልምምዶችን፣ መባ መስጠትን፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድን አለባበስንና የመሳሰሉትን ለክርስቶስ ላለን ፍቅር መለኪያ አድርገናቸዋል:: ሃይማኖታዊ መሰጠት ፊተኛ የሆነውን ትእዛዝ የሚፈጽም ቢሆንም እንኳ፣ ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን እንድንወድ ከሚያዘው ሁለተኛ ትእዛዝ አጠገብ አይደርስም:: ኢየሱስ በተናገረው መሠረት ይህ ሁለተኛው ትእዛዝ በፍርድ ቀን ቀዳሚ አጽንዖት ይኖረዋል (ማቴ 25፥31-46):: እንዲያውም እኮ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር መለኪያው ለልጆቹ ያለን ፍቅር ነው::

ለክርስቶስ ያላቸው ፍቅር በመታዘዛቸው ለተቈጠረላቸው ሰዎች እጅግ ውድ የሆነው ስጦታ ማለትም መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቷቸዋል (ሐሥ 5፥32):: አጽናኝ ተብሎአል (ቃል በቃል ጰራቅሊጦስ ሲሆን ለማገዝ ወይም ለማጽናናት የተጋበዘ ማለት ነው):: የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን የማንም ሳይሆን የክርስቲያኖች መብት ነው (ዮሐ 7፥39-40):: ወደ ልባችን (አካላችን) ይገባል (ሮሜ 8፥9-11፤ 1ቆሮ 6፥19)፤ የእግዚአብሔር ርስትም አድርጎ ያትመናል (2ቆሮ 1፥22፤ ኤፌ 1፥13፤ 4፥30):: በእርሱ አማካይነት ተቀድሰናል (ሮሜ 15፥16፤ 2ተሰ 2፥13)፤ ትምህርት ተምረናል (1ቆሮ 2፥10-16፤ ኤፌ 1፥17-18፤ 1ዮሐ 2፥27)፤ ምሪትን አግኝተናል (ሮሜ 8፥14፤ ገላ 5፥18)፤ ተበረታተናልም (ዮሐ 14፥26):: በእርሱ አማካይነት ልጅነትን



አግኝተናል (ተቀብለናል (ሮሜ 12፥6-8፤ 1ቆሮ 12፥7-11፤ ኤፌ 4፥11-13)፤ የእግዚአብሔርን ክብር ፍሬም ተቀብለናል (ገላ 5፥2-23):: እንዴት መጸለይ እንዳለብን በማናውቅበት ወቅት ስለ እኛ ይማልዳል (ሮሜ 8፥26)፤ ተስፋ ስንቈርጥም ያድሰናል (ሐሥ 3፥19 [ከሐሥ 2፥38 ጋር ያነ]፤ ዮሐ 7፥38-39፤ ኢሳ 40፥1-2፤ 41፥17-20፤ 44፥1-5፤ 54፥11-17፤ 55፥1-5፤ ዕብ 4፥1-11):: ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ገለጻ አንድን ክርስቲያን በምስጋና ውዳሴ እንዲጮኽ ያደርገዋል! ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ሊኖር በሚገባው የመንፈስ ቅዱስ አስፈላጊነትና ውበት ላይ ታምራዊ ስጦታዎች ፋክክር እንዳያሳድሩ መጠንቀቅ አለበት::

ደቀ መዛሙርት «ከጥቂት ጊዜ በኋላ» ኢየሱስን ያጡታል (ከዮሐ 7፥33፤ 12፥35፤ 13፥33፤ 16፥16-19 ጋር ያነ):: ይህ ትልቅ ጉዳት ነው:: አስተማሪያቸውን መሪያቸውንና ኀይል የሚያስታጥቃቸውን ያጣሉ:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሲሄድ የሚያጡትን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ይተካላቸዋል:: እንደ እውነቱ ከሆነ የኢየሱስ ቀጣይ ታሪክ የሆነው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ (ሐሥ 1፥1) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ታሪክ የሆነውን ያህል የሐዋርያት ሥራ ታሪክ አይደለም:: የኢየሱስን ያህል ባሕርይና ችሎታ ያለው ሌላው አጋዥ [*አሎን - allon*] ነው:: ዓለም ስለዚህ አስደናቂ ስጦታ (ከሐሥ 2፥6 ጋር ያነ) ምንም እንደማያውቅ ከሐዋርያት ሥራ ግልጽ ነው:: ምክንያቱም ዓለም የሚሠራው በዓለም ሥርዐት መሠረት ነውና:: መንፈስ ቅዱስ የማይከፋፈል ወይም የማይገበይ በመሆኑ በዓለማዊው ሰው ዘንድ አይፈልግም (1ቆሮ 2፥14):: እኛ ግን በአካላችን መንፈስ ቅዱስ በማደሩ በሥላሴ አንድነት እንደምንተባበር ቊ 19-20 ግልጽ ያደርጋሉ:: በእርግጥም የመለከት ባሕርይ ተካፋዮች ነን (2ጴጥ 1፥4)::

ዮሐ 14፥22-27

22ከዚያም የአስቆሮቱ ያልሆነው ይሁዳ፣ «ጌታ
ሆይ፤ ታዲያ፣ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ
የምትገልጠው እንዴት ነው?» አለው።
23ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «የሚወደኝ ቢኖር
ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱ
እንመጣለን፤ ከእርሱም ጋር እንኖራለን። 24የማይወደኝ
ቃሌን አይጠብቅም፤ ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ
የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።
25«አሁን ከእናንተ ጋር እያለሁ ይህን ሁሉ ነግሬአችኋለሁ፤ 26አብ በስሜ
የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል። እኔ
የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል። 27ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን
እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም። ልባችሁ
አይጨነቅ፤ አይፍራም።»

ሦስተኛው ጥያቄ የተነሣው ብዙ ከማይታወቀው ከሌላው ይሁዳ ታዴዎስ (ማቴ 10፥3፤ ማር 3፥18) ወይም ልብድዮስ ከተባለው ነው። አሁንም ስለ ምድራዊ መንግሥት የሚያስብ በመሆኑ ኢየሱስ በአገሪቱ ላሉት ሁሉ ራሱ ለምን እንዳልገለጠ ሊገባው አልቻለም። አንድ ንጉሥ በይፋ የታወቀ መሆንን አይፈልግምን? ይሁዳ የተናገረ መሆኑን ኢየሱስ ልብ አላለም። የእርሱን ጥያቄ በመመለስ ፈንታ ይሁዳ ሳያስተውለው የቀረውን ጉዳይ ደጋግሞ ተናገረ፦

1. ፍቅር የሚገለጸው በመታዘዝ ነው።
2. ኢየሱስን የሚወዱ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ቤት አላቸው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ለቶማስ የገለጸለት ቤት የወደፊት «ሰማያዊ» ቤት ነው። ለይሁዳ በተስፋ የተሰጠው ቤት ግን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የመሆን ምድራዊ ቤት ነው።
3. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በባሕርይ፣ በማንነትና በዓላማ በመሠረቱ አንድ ናቸው።



4. እርሱ ከሄደ በኋላ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን አገልግሎት ይቀጥላል።

የመንፈስ ቅዱስ አንዱ አገልግሎት ሐዋርያዊ አስተምህሮን መመሥረት ነው (ሐሥ 2፥42)። ይህን ፍጻሜ ላይ ለማድረስ ሐዋርያት የኢየሱስን ቃሎችና ሥራ አስመልክቶ (ከዮሐ 16፥13 ጋር ) «መለኮታዊ ትውስታ» ያስፈልጋቸዋል። ከዚህም በላይ ሐዋርያት በተለይ ለመስበክ በሚነሡበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ቃሎችና ሥራዎች ይተረጉምላቸዋል፤ ይተገብርላቸዋልም (ማቴ 10፥19-20)። በመጨረሻም ይህ ሐዋርያዊ አስተምህሮ ለሚመጡት ክርስቲያን ትውልዶች ሲባል፣ በእስትንፋሰ መንፈስ ቅዱስ አማካይነት በጽሑፍ ሰፍሮ ነበር። ካለን ጊዜ አኳያ አሁን ሂደቱን መግለጽ አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳ፣ ሃያ ሰባቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ያን ሐዋርያዊ አስተምህሮ ይዘዋል ብለን በመሠረቱ እናምናለን። ኢየሱስ የተናገረውንና የፈጸመውን ወይም ሐዋርያት ስለ እርሱ ያስተማሩትን ሁሉ ዐቅፈው ባይዙም፣ ኢየሱስ ለራሱ ሙሽራ እስከሚመለስ ድረስ ቤተ ክርስቲያን ህልውና ይኖራት፣ ታድግና ትጸና ዘንድ የሚያስፈልጋት ይኸው ነው።

«ልባችሁ አይጨነቅ፤ አይፍራም» በሚለው ቁጥር 27 ውስጥ፣ ኢየሱስ ወደ ቁጥር አንድ ይመለሳል። የሚመጡት ሁለት ቀናት ለሐዋርያት አስጨናቂዎች ይሆናሉ። ፈታኝ በሆነ ሰዓት ኢየሱስን ትተው ይሸሻሉ፤ ሲመታና ሲሰቀል በሩቅ ሆነው ይታዘባሉ። በኋላ ደግሞ በትንሣኤ ያገኙት ደስታ በዕርገቱ ወቅት ወደ ከፍተኛ ጭንቀት ይለወጣል። ወደፊት የሚጠብቃቸው ጉዞ ወደ ንቀት ወደ ልግጫና ወደ ድብደባ የሚወስድ ሲሆን፣ ከዮሐንስ በቀር ሁሉንም ሰማዕትነት ደረጃ ላይ ያደርሳቸዋል። ያም ሆኖ ኢየሱስ ሰላምን ይሰጣቸዋል። መከራ የሌለበት ሰላም ሳይሆን ከመከራ ጋር ያለ ሰላም ነው። ስጦታው ለእያንዳንዱ አማኝ በቀጣይነት ይተላለፋል። በውስጣችን መንፈስ ቅዱስ ስላለ፣ በእግዚአብሔርም ዘንድ ቤት

እንደሚኖረን ተስፋ ስላለን፣ ደግሞም ክርስቶስ እንደሚመለስ ስለምናምን እነዚህ አጭርና ጊዜያዊ ሥቃዮች (መከራዎች) የሚቻሉ ናቸው፤ ሊያስገኙት ካላቸው ተስፋ አንጻር ሲታዩ ደግሞ አስደሳች ናቸው ማለት ይቻላል (ሮሜ 8፥18፥22-23)።

ዮሐ 14፥28-31

[28]«*እሄዳለሁ፤ ተመልሼም ወደ እናንተ
እመጣለሁ* ማለቴን ሰምታችኋል፤ ብትወዱኝስ አብ
ከእኔ ስለሚበልጥ ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር፤
[29]የተናገርሁት ሲፈጸም እንድታምኑ፣ ከመሆኑ በፊት
አሁን ነግሬአችኋለሁ። [30]የዚህ ዓለም ገዥ ስለሚመጣ
ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልነጋገርም።
እርሱም በእኔ ላይ ሥልጣን የለውም፤ [31]ነገር ግን እኔ
አብን እንደምወድ፣ አባቴ ያዘዘኝንም እንደማደርግ
ዓለም እንዲያውቅ ነው።

«ተነሡ፤ ከዚህ እንሂድ።»

ኢየሱስ መሄዱና መመለሱ አይቀሬ መሆኑን ቀደም ሲል ሁለት ጊዜ ገልጾአል (14፥2-3፡18-19)። ወደ «መኖሪያ ስፍራው» በመመለሱ ደቀ መዛሙርቱ መደሰት ነበረባቸው። በራሳቸው በደረሰው እርሱን የማጣት ችግር የተነሣ ባስገኘው ድል ሐሤት ማድረግ አልቻሉም። ኢየሱስ ስለሚናገረው ነገር የሚውቅ መሆኑን እርግጠኞች እንዲሆኑ እንጂ ከእርሱ ጋር ሐሤት እንዲያደርጉ ይህን አይነግራቸውም።[46]

የሰይጣን ድንገተኛና ከባድ ጥቃት የቀረው ጥቂት ጊዜ ብቻ ነው። የአስቆሮቱ ይሁዳን ይማርካል፤ ጴጥሮስንና ሌሎቹን ሐዋርያት

[46] Tenney (ገጽ 149 ላይ) እንዲህ ይላል፤ «በዚህ ወንጌል ውስጥ ዳር እስከ ዳር ባለው ክፍል ማመን የቱን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ አጽንዖት ተሰጥቶታል (ዮሐ 1፥50፤ 3፥12፡15፤ 4፥21፡41፤ 5፥24፡44፡46፤ 6፥29፡35፡47፡64፤ 7፥38፤ 8፥24፡45፤ 9፥35፤ 10፥38፤ 11፥25፡40፤ 12፥37፡44፤ 13፥19፤ 14፥1፡11፤ 16፥31፤ 17፥20፤ 20፥27)።»



ያሸንፋል፤ በኢየሱስ አካል ላይም ያሰበው የሚሳካለት **ይመስላል።** በጣም መጥፎ መስሎ ቢታይም እንኳ፣ እውነቱ ግን ሰይጣን በኢየሱስ ላይ አንዳች ኀይል የለውም። በምድረ በዳ ሊፈትነው አልቻለም ነበር፤ በመስቀል ላይም ሊያሸንፈው አይችልም፤ ወይም በመቃብር ውስጥ ሊያስቀረው አልቻለም ነበር። ሰይጣን በኢየሱስ ላይ ተጽዕኖ ማሳደር አይችልም፤ በኢየሱስ ላይ ክስ ማቅረብም አይችልም። ኢየሱስ ይሞታል፤ የሚሞተው ግን በሰይጣን ኀይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

ይህን ካለ በኋላ አሁን የመሄጃው ጊዜ ደርሶአል። ነገር ግን በዚህ በላይኛው ክፍል ንግግር ላይ ሦስት ምዕራፍ ሙሉ ገና የቀረ ነገር አለ! የቀሩት ሦስት ምዕራፎች በዐሥር ደቂቃ ውስጥ ተነበው ያልቃሉ። ይህ ኢየሱስ የተናገረው ንግግር ዕጥርታ ቢሆንም እንኳ፣ በቀጣይነት የቀረበውን ንግግር እየተመለከትን አይደለንም። ከእራት በኋላ ዕቃቸውን እያጸዱና እየሰበሰቡ ሳለ፣ በምሽቱ ከመውጣታቸው በፊት መደረቢያቸውን እየለበሱም ሳለ ኢየሱስ ንግግሩን እንደ ቀጠለ ነበር። ወደ ቄድሮን ሸለቆ ለመሄድ (ዮሐ 18፥1) በኢየሩሳሌም አውራ ጐዳና ሲጓዙ ንግግሩን ይቀጥላል። በአትክልት ስፍራው ብቻውን ከመጸለዩ በፊት ይህን ሁሉ ለማከናወን በቂ ጊዜ ይኖረዋል።

**§ 150ሀ**
**የወይን ግንዱና ቅርንጫፎቹ**
**(ዮሐ 15፥1-17)**

ይህ ምዕራፍ በሦስት ምድብ ሊከፈል ይችላል፡- (ሀ) ከኢየሱስ ጋር አንድነት (የወይን ግንዱ ምስያ)፣ ቍ 1-8፤ (ለ) ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት፣ ቍ 9-17፤ እና (ሐ) ከዓለም ዘንድ ተቃውሞ፣ ቍ 18-27። ከኢየሱስ ጋር ያለን አንድነት ከሌሎች አማኞች ጋር ላለን አንድነትና ከዓለም ዘንድ ለሚደርስብን ተቃውሞ ምክንያት (መሠረት) ነው።

ይህ የመግቢያ አንቀጽ በፖለስቲና የዕርሻ ልምድ ላይ በመመሥረት የቀረበ ምስያ ነው:: የተለቀመ ወይን ጥሬ ገንዘብ ከሚያስገኙ ዐበይት መኸሮች አንዱ ነበር:: ስለዚህ ከወይኑ የተገኘው ትምህርት ለዐሥራ አንዱ የታወቀና ግልጽ ይሆናል:: እንዲህ ያለውን ምስያ ስንተረጉም በጊዜና በባህል የተራራቅን እንደ መሆናችን መጠን ዐበይት በሆኑት ክፍሎች (አካሎቹ) ላይ ማተኰር ይኖርብናል:: ይኸውም በወይኑ፣ በቅርንጫፎቹና በአትክልተኛው ላይ ነው:: የወይኑ የሥራ ድርሻ ቅርንጫፎቹ ፍሬ ያስገኙ ዘንድ ለእነርሱ አስፈላጊውን «ጭማቂ» መስጠት ነው (ቍ 4:5:7):: የቅርንጫፉ የሥራ ድርሻም በእርሱ አማካይነት ፍሬ ከሚያፈራበት ማለትም ከወይኑ ጋር ተጠብና መኖር ነው (ቍ 4:5:8):: የአትክልተኛው የሥራ ድርሻ ደግሞ (ቃል በቃል «ገበሬ») ፍሬ የማያፈሩትን ቅርንጫፎች መቍረጥ፣ ፍሬያማ የሆኑትን ደግሞ ቅርንጫፎች መግረዝ (ማስተካከል) ነው (ቍ 1-2:6):: ይህ ጉዳይ የይሁዳን ክሕደት ተከትሎ የመጣ ስለሆነ፣ ምስያው ለዐሥራ ሁለቱ ብርቱ የሆነ አንድምታ አለው::

ይህ ምንባብ ለዐሥራ አንዱ ሐዋርያት እውነተኛ ማስጠንቀቂያ ነው:: እነርሱም ሆኑ ወደ እምነት የመለሰሏቸው ወገኖች «ፍሬ አልባ» እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል:: ቀደም ሲል አማኙ ዋስትና እንደሚኖረው ተስፋ የሰጠ በመሆኑ (ዮሐ 10፥28)፣ የኢየሱስን ማስጠንቀቂያ ዝቅ በማድረግ የሚቀርብ ማናቸውም ዐይነት ትርጓሜ አሳሳችና ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው:: ጳውሎስም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የዕርሻ ምስያ አቅርቧል (ሮሜ 11፥11-24):: በእምነት የተቀደሱት ቅርንጫፎች ወደ አለማመን የሚያሽቆለቁሉ ከሆነ (ሮሜ 11፥20-22)



እነርሱም ተቈርጠው ይጣሉ ይሆናል::[47] ክርስቲያኖች ይህን የኢየሱስ ማስጠንቀቂያ በብርቱ ማጤን ይኖርባቸዋል::

**ዮሐ 15፥1-8**

1«እውነተኛው የወይን ተክል እኔ ነኝ፤
አትክልተኛውም አባቴ ነው:: 2እርሱም በእኔ ያለውን፣
የማያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ ቈርጦ ይጥለዋል፤ ፍሬ
የሚያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ ግን የበለጠ እንዲያፈራ ይገርዘዋል::[ǁ] 3ከነገርኋችሁ ቃል
የተነሣ እናንተ አሁን ንጹሐን ናችሁ:: 4በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእናንተ እኖራለሁ፤
እናንተም በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ ልታፈሩ አትችሉም::
5«እኔ የወይን ተክል ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ:: ማንም በእኔ
ቢኖር እኔም በእርሱ ብኖር፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፤ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ
አትችሉምና:: 6በእኔ የማይኖር ተጥሎ እንደሚደርቅ ቅርንጫፍ ነው፤ እንዲህ ያሉት
ቅርንጫፎች ተለቅመው ወደ እሳት ይጣላሉ፤ ይቃጠላሉም:: 7በእኔ ብትኖሩ ቃሉቼም
በእናንተ ቢኖሩ፣ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ለምኑ፤ ይሰጣችኋልም:: 8ብዙ
ፍሬ በማፍራት ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን ብትገልጡ በዚህ አባቴ ይከብራል::

*ǁ2 ይገርዘዋል የሚለው የግሪኩ ቃል ያጠራዋል የሚል ትርጉም አለው::*

የወይን ተክል እስራኤልን የሚያመለክት የታወቀ ትእምርት ነበር (መዝ 80፥8-9:14፤ ኢሳ 5፥1-7፤ ሕዝ 17፥8):: እንዲያውም መቃባውያን በ150 ዓ.ቅ.ክ. አካባቢ ሕዝብነታቸውን እንዲወክል በማድረግ በሳንቲሞቻቸው ላይ ቀርጸውት ነበር:: ታላቁ ሄሮድስም በ19 ዓ.ቅ.ክ. የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ በሠራ ጊዜ ወደ ቅዱስ ስፍራ

---

[47] R.A. Peterson, "The Perseverance of the Saints," *Pres* 17/2 (1991): 95-112 በሚለው ላይ የተቈረጡት ቅርንጫፎች ከቶ አማኞች አልነበሩም፤ ይኸውም በርግጥ በክርስቶስ አልነበሩም ማለት ነው ብሎ ይከራከራል (ከቍ 2 ጋር ያነ):: በክርስቶስ አምናለሁ የሚል ሰው ግን ፍሬ የማያፈራ ወይም በክርስቶስ የማይጸና ከሆነ፣ ከቶ እውነተኛ አማኝ አልነበረም ማለት ነው:: ይሁን እንጂ ከዚህ ላይ በካልቪኒዝምና በአርሚኒያኒዝም መካከል ያለው ልዩነት የቃላት ክርክር እንጂ ሌላ አይደለም::

በሚወስደው በር ላይ ከወርቅ የተሠራ የወይን ተክል በመግቢያው በር ዙሪያ እንዲታይ በማድረግ አስቀርጾ ነበር። ይህ ሁሉ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ለሚሥልላቸው ብርቱ ሥዕል የላቀ ጉልሕነትን ይሰጠዋል። በዚህ ጊዜ የቀረበው የጌታ እራት (ቅዱስ ቊርባን) ከወይኑ ተክል ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከሚያስታውሱበትና ጥሞና ከሚገቡበት ትርጒም ሰጭ መንገዶች አንዱ ይሆናል።

ወይኑ መገረዙ አስፈላጊ ነበር። የወይን ፍሬ የሚያድገው ከአዲስ ቅርንጫፍ ላይ እንጂ በዕንጨቱ ግንድ ላይ አልነበረም። ስለዚህ በያመቱ ይቈረጥ ነበር፤ ይኸውም የወይኑ ተክል ያለውን ኀይል ጥቅም በሌለው ዕንጨት ሳይሆን በማደግ ላይ ባለው ፍሬ ላይ እንዲያውል ነበር። አንዳንዶቹ ግንዶች ታላላቅ የወይን ተክሎችን ሊያወጡ ይችላሉ፤ የወይኑ ተክሎች ፍሬ አላስገኙም። እነዚህ ቅርንጫፎች ሙሉ በሙሉ ተቈርጠው እንደ ዕንጨት ተከመሩ። ያለመታደል ሆነና ይህ «ዕንጨት» መጥፎ ዐይነት በመሆኑ እንደ ደመና ከመንደድ በቀር ሌላ ጥቅም የለውም።

እግዚአብሔር እንደ መልካም አትክልተኛ በአትክልት ስፍራው «ጥቅም የሌለው» ዛፍ እንዲኖር አይፈቅድም። በውጭ ሲታዩ ክርስቲያኖች የሚመስሉ፣ ግን ፍሬ የማያፈሩ ይቈረጣሉ። «ቈርጦ ይጥለዋል» እና «እሳት» የተባሉት ቃላት ቅንጅት ፍርዱ ምን እንደሚመስል ሥዕላዊ በሆነ መልክ በሚገባ ያሳያሉ (ማቴ 3፥10፤ 7፥19፤ ራእ 10፥14-15)።[48] «ንጹሐን» የሚለው ቃል ዮሐንስ 13፥10ን

[48] J.C. Dillow, "Abiding Is Remaining in Fellowship: Another Look at John 15:1-6," *BibSac* 147 (1990): 44-53 ላይ በኢየሱስ ያሉ ቅርንጫፎች (ቊ 2) በእርግጥ ክርስቲያኖች ናቸው በማለት አሳማኝ በሆነ መልክ ይከራከራል። በእንዲያውም ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ «በእኔ» የሚለው 16ቱ እያንዳንዱ አገባብ ከኢየሱስ ወይም ከአብ ጋር ያለውን ጥብቅ ኅብረት ያመለክታል። ይሁን እንጂ ከወይኑ ተክሉ መለየት የሚመለክተው መኮነንን ሳይሆን፣ ለቦዘነ ልጅ የሚሰጠውን ጊዜያዊ ቅጣት ነው ይላል። በማከልም ቊ 2 ውስጥ ኤርዮ - *airo* ከክርስቶስ መለየትን አያመለክትም፤ ፍሬ ለማፍራት



ያስታውሰናል፤ «ሁላችሁም ባትሆኑ፣ እናንተ ንጹሐን ናችሁ። ይሁዳ አሁንም ከጀርባ ያንጃብባል።

ፍሬ የሚያፈሩት እንኳ ሥቃይ ባለው ግን አስፈላጊ በሆነው የግርዛት ሂደት ውስጥ ማለፍ ይኖርባቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ግርዛት እውን የሚሆነው አንድ ክርስቲያን ይቋቋም ዘንድ በሚደርስበት ፈተና ውስጥ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ማንጻት ብሎ የሚጠራው ይህ ግርዛት እውን የሚሆነው፣ በእርሱ ቃል በኩል መሆኑን ቊጥር 3 ግልጽ ያደርጋል። የኢየሱስ ቃል ለሐዋርያት የተነገረው በቃል ነው፤ ለእኛ ግን ተጽፎልናል። ውጤቱ ያው ነው። የኢየሱስ ቃል በሕይወታችን ፍሬ የማያፈራውን ሁሉ ቈርጦ ይጥለዋል (ከዕብ 4፥12 ጋር ያነ)።

አንድ ጥያቄ ይቀራል፤ «በኢየሱስ እንዴት እንኖራለን?» ሁለት ክፍል ያለው መልስ ቊጥር 7 ውስጥ ተጽፎአል። ከኢየሱስ ቃል ጋር እንጣበቃለን፤ እንጸልያለንም። ይህ ከመተግበሩ ይልቅ ቢናገሩት የሚቀል ቢሆንም፣ ፅንሰ ሐሳቡ በጣም ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት፣ በቃል በመያዝ፣ በመስበክና በማስተማር አእምሮአችንን በክርስቶስ ቃል እንሞላለን። ልመናችንን ወደ እግዚአብሔር በታማኝነት በማቅረብ ከግንዱ ጋር ለመጣበቅ የሚያበቃን እምነትና ጽናት ተሰጥቶናል (በቊጥር 7 ውስጥ የተሰጠውን ትንታኔ ለማስተዋል ከ14፥13፤ በገጽ 401 ላይ § 149 ጋር ያነ)።

ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ ውስጥ ሦስተኛ ደረጃን ያክላል፤ ይኸውም የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ማክበር ነው (1ዮሐ 2፥3-6:27፤ 5፥1-4)። ከክርስቶስ ጋር ለመጣበቅ ሌሎች መንገዶች

የሚታገሉትን ለማንሣት ያለውን የእግዚአብሔር ክብካቤ እንጂ ይላል። ሆኖም ይህ ትርጓሜ ከምስያ ቋንቋም ሆነ (ከማቴ 3፥12፤ 5፥22፤ 18፥8-9፤ 25፥41፤ ከ2ተሰ 1፥7-8፤ ከራእ 20፥15 ጋር ያነ) ከታሪካዊ ዳራው ጋር አይገጣጠምም (አይስማማም)።

ቢኖሩም፣ ለመንፈሳዊ ጽናታችን እነዚህ ሦስቱ ከእግዚአብሔር የተሰጡ ዋና ዋና ምግቦች ናቸው:: ስለዚህ በዚህ ዐውድ ውስጥ፣ «እምነት፣» «ፍቅር፣» እና «መታዘዝ» የተባሉት ቃላት ተግባራዊ የሆኑ ተመሳሳዮች ናቸው::

ከክርስቶስ ጋር በመጣበቅ ፍሬ እናፈራለን:: ቅጽበታዊ አይደለም፤ ግን አይቀሬ ነው:: በእኛ በኩል ጥረት የሚጠይቅ ቢሆንም እንኳ፣ እውነተኛ ደቀ መዛሙርቱ የሆኑ ሁሉ ፍሬያማ ስለ መሆናቸው ጥርጥር የለውም:: ከወይን ግንድ ጋር የተጣበቁት ቅርንጫፎች ፍሬያማ እንደ ሆኑ ሁሉ (የወይን ፍሬ እንደሚሰጡ ሁሉ) ከክርስቶስ ጋር የተጣበቁ ክርስቲያኖችም ፍሬ ያፈራሉ:: ፍሬ ሲባልም ክርስቲያናዊ ጠባይን (ገላ 5÷22)፣ የጽድቅ አኗኗርንና የቸርነት ሥራን (ኤፌ 5÷9)፣ አማኝ ማፍራትን (ሮሜ 1÷13)፣ ለእግዚአብሔር ውዳሴ ማቅረብን ያካትታል (ዕብ 13÷15)፣ (ከማቴ 7÷16-20፤ 12÷23፤ 13÷8:23፤ ከሮሜ 7÷4፤ ከ2ቆሮ 9÷10፤ ከኤፌ 5÷9፤ ከቈላ 1÷6፤ ከዕብ 12÷11፤ ከያዕ 3÷18 ጋር ያነ)::

[9]«አብ እንደ ወደደኝ ሁሉ እኔም
ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ:: [10]እኔ የአባቴን ትእዛዝ
ጠብቄ በፍቅሩ እንደምኖር፣ እናንተም ትእዛዜን
ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ:: [11]ደስታዬ በእናንተ
እንዲሆንና ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን ይህን ነግሬአችኋለሁ:: [12]ትእዛዜ ይህች ናት፤
እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ:: [13]ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን
አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም፤ [14]የማዛችሁን ብትፈጽሙ
ወዳጆቼ ናችሁ:: [15]ከእንግዲህ አገልጋዮች አልላችሁም፤ አገልጋይ ጌታው የሚሠራውን
አያውቅምና፤ ነገር ግን ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ስለ ገለጽሁላችሁ ወዳጆች
ብያችኋለሁ:: [16]እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ እንድትሄዱና ፍሬ

ዮሐ 15÷9-17



እንድታፈሩ ፍሬያችሁም እንዲኖር ሾምኋችሁ:: ስለዚህም አብ በስሜ የምትለምኑትን
ሁሉ ይሰጣችኋል:: [17]እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ትእዛዜ ይህች ናት::

የክርስትና ቍልፍ ቃል ፍቅር ሳይሆን አይቀርም:: የምንናገረው እንዲሁ ስለ ስሜታዊነት አይደለም፤ ለሌላው ሲባል ራስን አሳልፎ ስለ መስጠት ጉዳይ እንጂ:: ክርስቲያኖች የሚታወቁበት መለዮ ነው (ዮሐ 13÷34-35)፤ ወንድሞቻችንን የማንወድ ከሆን፣ እግዚአብሔርን ላለመውደዳችን እርግጠኛ ምልክት ነው (ዮሐ 4÷20-21):: እርግጥ ኢየሱስ ፍጹም የሆነ የፍቅር ምሳሌ ነው፤ እርሱን እንከተለው ዘንድ ታዘናል:: ፍቅሩ በሁለት ነገሮች ተለይቶ ይታወቅ ነበር:- (1) እግዚአብሔርን በፍጹም በመታዘዙ (ቍ 10)፣ እና (2) ሕይወቱን አሳልፎ በመስጠት (ቍ 13)::

የኢየሱስን ፍቅር ለመከተል በብርቱ ጥረት የምናደርግ ከሆን፣ ሁለት ነገሮችን ማድረግ አለብን:: በመጀመሪያ ትእዛዞችን በመፈጸም መታዘዝ አለብን:: ይህ ማለት ግን የሰጠውን ትእዛዝ ሁሉ ያለ እንከን እንፈጽማለን ማለት አይደለም:: ቢሆንም እርስ በርስ እንድንዋደድ በሰጠን ቀዳሚ ትእዛዝ ላይ ግድየለሾች ልንሆን አንችልም (ከ13፤34 ጋር ያነ):: ይህም በሰባኪዎች መካከልና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማይረባ ነገር የሚካሄድን ንትርክና ውድድር አሳፋሪ የሆነ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ጥሰት ያደርገዋል:: ሁለተኛ ሕይወታችንን ለሌሎች አሳልፈን እንሰጣለን (1ዮሐ 3÷16):: ብዙዎቻችን ሕይወታችንን በተለይ ለኢየሱስና ለቤተ ሰባችን አሳልፈን እንሰጣለን እንላለን፤ ይህ የሩቅ እውነት መሆኑን እናውቃለንና:: ኢየሱስ እንደ ሞተው ዐይነት እንሞት ዘንድ ግን አልተጠራንም::[49] ይልቁንስ እርሱ

[49] ቍጥር ዐሥራ ሦስት ውስጥ «ስለ» በሚለው መስተዋድድ አማካይነት፣ «በሌላ ሰው እግር በመግባት» ወይም «ምትክ በመሆን» የሚለው የተተኪነት ሞት ሳይታሰብ አልቀረም::

እንደኖረው እንኖር ዘንድ ተጠርተናል (1ዮሐ 3፥17)። ይህም ብድር የሚከፍሉት የሌላቸው ሕመምተኞች የሕክምና ወጭ መሸፈንን፣ መበለቶችን መጠየቅን፣ ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆችን ልጅ አድርጎ ማሳደግን፣ በጉዞ ላይ ወይም በፈተና ላይ ላሉት መጠለያ መስጠትን ያካትታል። በእርግጥም ለሌሎች መኖር ለእነርሱ ከመሞት ይልቅ አስቸጋሪ ነው።

ይህ ዐይነቱ ራስን አሳልፎ የመስጠት ፍቅር የሚገኘው ዋጋ በመክፈል ነው። ሽልማትንም ይዞ ይመጣል። ኢየሱስ የፍቅር ትእዛዙን ለሚያከብሩ ሁሉ ሦስት ተስፋዎች አድርጎ ሰጥቶአል፦ (1) በኢየሱስ ሐሤት ይሞላሉ (ቊ 11)። ኢየሱስ ወደ መስቀል በሚያመራበት ጊዜ በፍንደቃ ላይ ነበር ብላችሁ አታስቡም።፤ ሆኖም በጥልቅ እርካታና ሰላም ተሞልቶአል። በአባቱ ዐቢይ ፈቃድ ውስጥ እንደሚገኝና በቅርቡም ከእርሱ ጐን እንደሚሆን ያውቃል። ይህ ሽልማትም ዋጋ ሊከፈልበት ይገባል። (2) ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱ ጌታ ብቻ ሳይሆን ወዳጃቸውም ነው (ቊ 14-15)። ጥልቅ ስሜቱንና ዕቅዱን አካፍሎአቸዋል። ይህ ዐይነቱ ግልጽነት የወዳጅነት መገለጫ ባሕርይ ነው። ኢየሱስ ያዘዘውን ስንፈጽም እኛም የወዳጆቹ አባላት እንሆናለን። ጥልቅ፣ የፍቅር ሀብት ያለበት እንዲሁም ሙሉ የሆነ ኅብረት ከኢየሱስ ጋር ይኖረናል። ሽልማቱም ዋጋ ሊከፈልበት ይገባል። (3) ኢየሱስ ጸሎታችንን ይሰማል (ቊ 16ለ፣ ከቊ 7 እና ከ14፥13 ጋር ያነ)። የመላው ዓለም ፈጣሪ ያደምጠናል። አሁንም ቢሆን ሽልማቱ ዋጋ ሊከፈልበት ይገባል።

አለዚያ እንዲህ ያለውን ሽልማት በማግኘታችን በራሳችን ላይ ትምክህት ያድርብናል፤ ቊ 16 ውስጥ በኃጢታችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሣ መሆኑን ልብ እንል ዘንድ ተነግሮናል። አስቀድሞ የጠራን እርሱ ነው (ዮሐ 6፥44)። በእምነታችን ጸንተን እንድንኖር የሚያደርገን እርሱ ነው (ዮሐ 10፥28)። ፍሬ እንድናፈራ በኀይል



የሚያስታጥቀን እርሱ ነው (ዮሐ 15፥5)። በኃጢታችን (ቸርነታችን) ሁሉና ፍሬያችንም ሁሉ ድንቅ የሆነው የእግዚአብሔር ጸጋ ምስክር ነው (ዮሐ 15፥8)!

**§ 150ለ**
**ከዓለም ዘንድ ተቃውሞ**
**(ዮሐ 15፥18-16፥4)**

18«ዓለም ቢጠላችሁ፣ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ። 19ከዓለም ብትሆኑ ኖሮ፣ ዓለም የራሱ እንደሆኑት አድርጎ በወደዳችሁ ነበር፤ ከዓለም ለይቼ ስለ መረጥኋችሁ የዓለም አይደላችሁም፤ ዓለም የሚጠላችሁም ስለዚህ ነው።»

ከኢየሱስ ጋር ኅብረት (ቊ 1-8) ወደ ሦስት ነገሮች ማምራቱ አይቀሬ ነው፦ (1) ፍሬ ማፍራት (ቊ 2:4:5:8)፤ ሰዎችን መውደድ (ቊ 9-17) እና (3) ስደት (ቊ 18-25፤ ከማር 13፥9፤ ከሉቃ 21፥12 ጋር ያነ)። ፍሬ የማፍራቱን ሐሳብ እንወደዋለን። ሌሎችን የመውደድ ኀላፊነትንም እንወጣለን። ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ኅብረት እስካለን ድረስ የማይቀር ጉዳይ ቢሆንም እንኳ ስደትን እንጠላለን። ኢየሱስን የምትከተል ከሆንክ ትሰደዳለህ። በጣም ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው። ከኢየሱስ ጋር ከተባበርህ ዓለም እርሱን ባስተናገደው መልኩ አንተንም ያስተናግድሃል (ከ13፥16፤ 15፥20 ጋር ያነ)። በአንጻሩ ግን ከዓለም ጋር ከተባበርክ «የእኛ ወገን» ተብለህ ትስተናገዳለህ። ሐዋርያት በኢየሱስ የተመረጡ ሰዎች ነበሩ።[50] በእርግጥም ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር የመረጣቸውና ከዓለም የወጡ ነበሩ። ስለዚህ ስደት ይደርስብን ይሆናል ብለን ልናስብ እንችላለን።

---

50 «መረጥኋችሁ» የሚለው ቃል በተለይ ሐዋርያትን ይመለከታል (ከሉቃ 6፥13፤ ከዮሐ 6፥70፤ 13፥18፤ 15፥16፤ ከሐሥ 1፥2:24፤ 9፥15፤ 22፥14)።ነገር ግን አያሌ ማጣቀሻዎች እግዚአብሔር አስቀድሞ ክርስቲያኖችን የመረጠ መሆኑንም ይገልጻሉ (ሮሜ 8፥29-30፤ 11፥5፤ ኤፌ 1፥4-5፤ 1፥11፤ 2ተሰ 2፥13፤ 1ጴጥ 1፥2፤ 2፥9፤ ራእ 17፥14። «ያ የምርጫ ሂደት» እንዴት እውን እንደሚሆን ማቴዎስ 22፥14ን ይመልከቱ።

ይህ እውነት ከሆነ ታዲያ ቤተ ክርስቲያን (የአሜሪካ) ለምን ስደት አልደረሰባትም? ቢያንስ ቢያንስ ሦስት ፋይዳ ያላቸው መልሶች አሉ:: በመጀመሪያ ስደት አካላዊ ብቻ አለመሆኑን ኢየሱስ ገልጾአል (ማቴ 5፥11-12)፤ ነገር ግን ስም ማጥፋትን፣ ማላገጥን፣ መናቅን ወይም ውግዘትን ሊያካትት ይችላል:: አሜሪካን ውስጥ ጥቂት ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት ቢደበደቡም፣ ቤተ ክርስቲያንም ኢየሱስን በመከተሏ ብዙ ጊዜ የስድብ ናዳ ደርሶባታል:: በቴሌቪዥን በሚቀርብ አዝናኝ ተውኔትና በፍርድ ቤት እንዲሁም ምክር ቤት ውስጥ ዓለም በክርስቶስ ላይ ያላት ብርቱ ጥላቻ ቤተ ክርስቲያንም ይደርስባታል:: በሌላ በኩል ግን ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ በዓለም ስልት ራሷን በማሞካሸት ጨውና ብርሃን ከመሆን ባሕርይዋ የተነሣ የሚደርስባትን ውጊያ በማስወገድ ከስደት ታመልጣለች:: በግልጽ ቋንቋ ሲገለጽም ቤተ ክርስቲያን ሐሞተቢስ ሆናለች:: «ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት፣ ስለሚመጣውም ፍርድ» (ሐሥ 24፥25) በመስበክ ፈንታ ማኅበረሰባዊ ወንጌልን ትሰብካለች፤ ሰዎችን ስለ ኀጢአታቸው በመገዳደር ፈንታ አሉ የተባሉ ክበቦች አባል በመሆን ትተባበራለች::

ሦስተኛ፣ ዐበይት ከሆኑት የስደት መንሥኤዎች አንዱ በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ላይ የጽድቅ ሕይወት የሚያሳድረው የበደለኛነት ስሜት ነው:: ጻድቅ ምንም ነገር ሳይናገር ኀጢአተኛን ይኮንናል:: ንጽሕናው በክፉ ሰው አካሄድ ላይ ይመሰክርበታል:: እንዲህ ያለን (ያለችን) ሰው ምሳሌነቱ(ቷ)ን መከተል ያስፈልጋል፤ ወይም መወገድ አለበ/ባ/ት:: አለመታደል ሆነና ብዙ ጊዜ ሁለተኛውን መፈጸሙ ቀላል ነው:: ይብስ አለመታደል የሆነው ደግሞ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች በመታዘብ ላይ ያለውን ዓለም የሚያስቆጣ ዐይነት የጽድቅ ሕይወት የሌላቸው የመሆኑ ሐቅ ነው:: ሕይወታቸው የርሱ አስተናጋጅ የሆኑ ን ሰይጣን አያሸብርም፤ ወይም የዓለም ሰው የሆነውን አይከስም:: የማይቻል ነው ባይባልም እንኳ፣ በብዙ ክርስቲያኖችና



ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች መካከል ልዩነት ማየቱ አስቸጋሪ ነው:: ኢየሱስ ቍ 19 ውስጥ እንደገናም በ1 ዮሐንስ 4፥4-6 ላይ የሚያተኩረው በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው:: ዓለም «የራሱ የሆነውን» በመለየት (በማወቅ) ረገድ ባለሙያ (ጥበበኛ) ነው:: ዓለም ክርስቲያንን ከሌላው ለይቶ ማየት ካልቻለ፣ ኢየሱስም ለይቶ አያየው ይሆናል (ማቴ 10፥32-33)::

ዮሐ 15፥20-25

[20]«'አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም' ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስታውሱ:: እኔን ለሳደውኝ ከሆነ፣ እናንተንም ያሳድዷችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው ከሆነም ቃላችሁን ይጠብቃሉ:: [21]የላከኝን ስለማያውቁ፣ በስሜ ምክንያት ይህን ያደርጉባችኋል:: [22]መጥቼ ባልነገራቸው ኖሮ ኀጢአት ባልሆነባቸው ነበር፤ አሁን ግን ለኀጢአታቸው የሚሰጡት ምክንያት የላቸውም:: [23]እኔን የሚጠላ፣ አባቴንም ይጠላል:: [24]ሌላ ሰው ያላደረገውን በመካከላቸው ባላደርግ ኖሮ፣ ኀጢአት ባልሆነባቸው ነበር፤ አሁን ግን እነዚህን ታምራት አይተዋል፤ ሆኖም እኔንም አባቴንም ጠልተዋል:: [25]ይህም፣ 'ያለ ምክንያት ጠሉኝ' ተብሎ በሕጋቸው የተጻፈው ቃል እንዲፈጸም ነው::»

ስደት ከቶ አያስደስትም፤ ይሁን እንጂ ተቀባይነት ያለው እንዲሆን የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉ:: በመጀመሪያ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳሳሰባቸው ሁሉ እኛ ከመሰደዳችን በፊት እርሱ ተሰዶአል (ቍ 20):: በሚቀጥሉት ሃያ አራት ሰዓታት በኢየሱስ ላይ የሚደርሰው እኛ ከምናልፍበት ተመክሮ ሁሉ እጅግ የከፋ ነው:: እርሱ ያለፈበት በመሆኑ በሥቃያችን ሊራራልን ይችላል:: ሥቃያችን በእርግጥ ይገባዋል:: ከዚህም በላይ ሥቃዩን እንደ ተጋራን ሁሉ ሥልጣኑንና (ፊል 3፥10-11) እርስቱን (ሮሜ 8፥17) እንጋራለን:: ሁለተኛ በመጨረሻው ጉዞ ሽልማት አለ:: አሁን እንኳ ዓለም የሌለው ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነትና የኀጢአት ይቅርታ አለን (ቍ 21-25):: ኢየሱስ በመምጣት ላይ ነው፤ ከእርሱም ጋር ፍርድ እየመጣ

ነው (በዚህ ምንባብ ላይ እንደሚታየው ማለት ነው):: በዚያ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነትና ያገኘነው የኀጢአት ይቅርታ ይበልጥኑ ጣፋጭ ይሆናል፤ ዓለም እነዚህን አለማግኘቱ ደግሞ ይበልጥኑ ዘግናኝ ይሆናል:: ሦስተኛ፣ የአሁኑ ሥቃያችን በሕይወታችን መልካም ጠባይንና ጽድቅን ያሳድጋል (2ቆሮ 4÷17-18፤ ፊል 3÷10፤ ያዕ 1÷2-4፤ 1ጴጥ 4÷12-16):: ስደት ብዙ ጊዜ የሚመጣው ከፍተኛ ሽክምን አስከትሎ ነው:: ነገር ግን ከእርሱ የምናተርፈውና በእርሱም አማይነት የምንሆነው ዋጋ ሊከፈልበት ይገባል (ሮሜ 8÷18)::

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ «በሌላው በኩል» ያለው አማራጫችን የተሻለ አይደለም:: ክርስቶስን በመተው ከስደት የምናመልጥ ብንሆን ብርቱ መዘዞች ይከተላሉ:- (1) እግዚአብሔርን አለማወቃችን ብቻ ሳይሆን፣ እርሱን እንደጠላን እንቀራለን:: እግዚአብሔርን የምንጠላው ለእርሱ ውድ የሆነውን ነገር በመተዋችን ነው (ቊ 21-23):: ከዚህም የተነሣ በአስፈሪ ፍርድ ውስጥ እንወድቃለን:: (2) የኀጢአት በደል አለብን (ቊ 22-24):: ይህም የሥጋ ምኞትን የማርካት ወይም ከራስ ወዳድነት የሚመነጭ ምኞት ብቻ ሳይሆን ልጁን የመካድ በደል (ኀጢአት) ነው:: ያለማመንም ኀጢአት:: እንዲህ ያለው ኀጢአት ብርቱ ቅጣት ያዘለ ነው:: (3) ምክንያትም ሆነ መከላከያ የለንም (ቊ 22-24):: ይህ በሦስት መንገድ እውነት ነው:: በመጀመሪያ አናውቅም (አላውቅም) እንዳንል ኢየሱስ እውነቱን ነግሮናል (ቊ 22):: ሁለተኛ እውነቱን ታይተው በማይታወቁ ታምራት አረጋግጦአል (ቊ 24፤ ለምሳሌ ማር 2÷12፤ ዮሐ 9÷32):: ሦስተኛ የደረሰበትን ስደት የሚያስከትል ምንም በደል ከቶ አልፈጸመም (ቊ 25):: ይህ ጥቅስ የመዝሙር 35÷19ና የ69÷4 ቃና አለው:: ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ጠላቶቹ የሚደርሱበት ጥቃት በኢየሱስ ላይ ከቀረበው ክስ በእጅጉ የባሰ ነው::



**ዮሐ 15÷26-27**

[26]«እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ፣ ከአብ
የሚወጣው አጽናኝ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ
ስለ እኔ ይመሰክራል:: [27]እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያው
ከእኔ ጋር ስለ ነበራችሁ፣ ትመሰክራላችሁ::»

ወንጌልን መስበክ ዐበይት ከሆኑ የስደት ምክንያቶች አንዱ ነው:: ይህ ሐዋርያት ሥራ ውስጥ በተደጋጋሚ በጉልሕ ተመልክቶአል:: በጴጥሮስና በዮሐንስ (ከሐሥ 4÷1 ጋር ያነ)፣ በዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ላይ (ከሐሥ 5÷17 ጋር ያነ)፣ በእስጢፋኖስ ላይ (ከሐሥ 6÷8 ጋር ያነ)፣ እናም በጳውሎስ ላይ የደረሰ ነው (ከሐሥ 9÷20፤ 13÷6-9:44-45፤ 14÷1-2:19-20 ወዘተ ጋር ያነ)::

እንዲህ ያለው ስደት እንደሚመጣ ኢየሱስ በትንቢት ተናግሮአል (ማቴ 10÷17-20)፤ ያን ተከትሎ ግን ተስፋ መጥቶአል፤ መንፈስ ቅዱስ! ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ሲሰብኩ እርሱ ከጐናቸው ይሆናል:: የመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ሥራ ምንጊዜም ስለ እግዚአብሔር መናገር ነው:: ከማንኛውም የብሉይ ኪዳን ትንቢት ጀርባ ምንጊዜም እርሱ ነበር (2ጴጥ 1÷20-21):: ክርስቲያኖችን ለማስተማር (ዮሐ 14÷26፤ 15÷26፤ 16÷13:15) እና ለመመስከር (ዮሐ 15÷26፤ 1ጢሞ 4÷1፤ ራእ 2÷7) እንደ ቀጠለ ነው:: በተጨማሪም ዓለምን ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል (ዮሐ 16÷8-11):: ዓለምን ለክርስቶስ ለማሸነፍ የምናደርገው ጥረት ከእግዚአብሔር ነጻ የሆነ ወይም እንዳሻችን እንድንኖር የተተውን አይደለም::

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የእኛን ሥራ አይሠራልንም:: ሁላችንም ስለ ኢየሱስ የመመስከር ኀላፊነት አለብን (ሮሜ 10÷10):: ይህ የክርስቶስ ቀዳሚ መልእክተኞች በነበሩት ሐዋርያት በተለይ ተፈጻሚ ነበር:: ይህ ልዩ ሹመት ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመንና (ቊ 27፤

ሐሥ 1÷21-22፤ 4÷19) ከኢየሱስ የአገልገሎት ዘመን መጀመሪያ አንሥቶ የእርሱ ተከታዮች ይሆኑ ዘንድ ግድ አላቸው::

1«ይህን ሁሉ የነገርኋችሁ እንዳትሰናከሉ ነው:: ዮሐ 16÷1-4
2ከምኵራብ ያስወጧችኋል፤ እንዲያውም የሚገድላችሁ
ሁሉ እግዚአብሔርን እንዳገለገለ የሚቈጥርበት ጊዜ ይመጣል:: 3ይህን ሁሉ
የሚያደርጉባችሁ፣ አብን ወይም እኔን ስላላወቁ ነው:: 4አስቀድሜ ይህን የነገርኋችሁ
ጊዜው ሲደርስ እንድታስታውሱ ነው፤ ከእናንተ ጋር ስለ ነበርሁ፣ ይህን ከመጀመሪያው
አልነገርኋችሁም::»

ዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ወደፊት የሚደርስባቸውን ስደት ሳያስተውሉ እንዲቀሩ ኢየሱስ አልፈለገም፤ ለሚደርስባቸው ስደት ይዘጋጁ ዘንድ አስጠነቀቃቸው:: ቀደም ሲል ስለዚሁ ጉዳይ እነርሱን ማስጠንቀቁ አስፈላጊ አልነበረም፤ ምክንያቱም እርሱ አብሯቸው ነበር:: አሁን ግን ትቶአቸው ሊሄድ ስለሆነ አርቀው ያስተውሉ ዘንድ አስፈላጊያቸው ነው:: ብርቱ ጥቃት ይመጣባቸዋል:: ሐዋርያትን የሚያሳድዱ ሁሉ ለእግዚአብሔር እየሠራን ነው ብለው ስለሚያስቡ የሐዋርያቱ መከራ ዕጥፍ ድርብ ይሆናል:: ይህም በተለይ የራሱን፣ «ቅዱስ ጦርነት» ያካሂድ በነበረው በሳውል ዘንድ እውን ሆኖ የሚገኝ ይሆናል (ሐሥ 7÷60-8÷3፤ 9÷1-3፤ 23÷1፤ ገላ 1÷13):: ነገር ግን በመጀመሪያው ምእት ዓመት አይሁድ የፈጸሙት ማሳደድ ይህንኑ የመሰለ ነበር (ከሐሥ 14÷19፤ 17÷5-9:13-14፤ 18÷12፤ 20÷3፤ 21÷27-32፤ 23÷12-16 ጋር ያነ):: በዘጠነኛው ዓመተ ምሕረት አጋማሽ ላይ ክርስቲያኖች በአይሁድ ምኵራቦች ያመልኩ ዘንድ እንዳይፈቀድላቸው ተወሰነ (ከራእ 2÷9፤ 3÷9 ጋር ያነ):: እንዲያውም የገማልያል የልጅ ልጅ የሰንበታቸውን 18ኛ ማሳረጊያ ጸሎት



በማድረግ፣ «ናዝራውያንና (ክርስቲያኖች) መናፍቃን ወዲያውኑ ይገደሉ» የሚለውን ጨመረ::

### § 150ሐ የወደፊቱ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት (ዮሐ 16÷5-15)

5«አንግዲህ ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ ይሁን እንጂ
ከእናንተ፣ 'የምትሄደው የት ነው?' ብሎ የሚጠይቀኝ
የለም:: 6ይህን በመናገሬም ልባችሁ በሐዘን
ተሞልቶአል፤ 7ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፤ መሄዴ
ይበጃችኋል:: እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ ወደ እናንተ
አይመጣም፤ ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ እናንተ
እልካለሁ፤

ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ወዴት እንደሚሄድ አልጠየቁም የሚለው ሐሳብ እውነት አይደለም:: ጴጥሮስ በዚያኑ ምሽት ጠይቆአል (ዮሐ 13÷36):: ቶማስም ከጥቂት ጊዘ በኋላ፣ «ጌታ ሆይ፤ ወዴት እንደምትሄድ አናውቅም፤ ታዲያ፣ መንገዱን እንዴት ማወቅ እንችላለን?» (ዮሐ 14÷5) በማለት ጠይቆአል:: ችግሩ ያልጠየቁ መሆናቸው ሳይሆን ኢየሱስ ንግግሩን ከመጨረሱ በፊት ውይይቱን መተዋቸው ነበር፤ ይህ «የደህና ሁኑ» ንግግር ነው:: ኢየሱስ የት እንደሚሄድ በማጤን ፈንታ በሐዘን ተውጠው ነበር:: ከኢየሱስ ጋር ሐሤት ማድረግና ዕቅዱንም ማጤን ይገባቸው ነበር::

ከኢየሱስ ጋር ሐሤት ማድረግ ብቻ ሳይሆን በራሳቸውም ደስ መሰኘት ነበረባቸው:: ኢየሱስ ሲሄድ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ:: በተለይ እንዲህ ያለው ታላቅ ስንብት ቀላል አይደለም:: መንፈስ ቅዱስ የቱን ያህል ታላቅ ስጦታ መሆኑን ማሰቡ ለሐዋርያቱ ቀላል እንዳልነበር የታወቀ ነው:: ይሁን እንጂ በመስቀል (በመከራ) የተጀመረ ቢሆኑም፣ ከኢየሱስ አንጻር ሲታይ እርሱና ዐሥራ አንዱ በቂ በሆነ መልኩ ለግንዛቤ የሚሆን ጉዳይ አግኝተዋል::

እርሱ ከመሄዱ በፊት መንፈስ ቅዱስ ለምን እንደማይመጣ ኢየሱስ አልገለጠም:: መንግሥተ ሰማይ ሁለቱ የመለኮት አባላት ህልዎት ስለሚያስፈልገው አይደለም! በሁሉ ቦታ የሚገኘው መንፈስ ቅዱስ (መዝ 139፥7-10) በአንድ ጊዜ በሁለቱም ስፍራ ሊገኝ ይችላል፤ ኢየሱስ ሲጠመቅ (ዮሐ 1፥32-33) ወደ ምድር በአካል መልክ መጥቶአል:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የሚመጣበት ሥራ የተመሠረተው፣ እርሱ ሊሄድ ሲል በሚፈጽመው ነገር ነው ብለን እናስባለን:: ኢየሱስ በመስቀል አማካይነት ይህን ዓለም ትቶ ይሄዳል:: መንፈስ ቅዱስ በመውቀስ (8-11)፣ እንደገና በመውለድ (ዮሐ 3፥3-7፤ ቲቶ 3፥5) በመቀደስ (2ተሰ 2፥13፤ ሮሜ 15፥16)፣ በምልጃ (ሮሜ 8፥26)፣ በምሪትና (ሐሥ 16፥6-7)፣ በማበረታታት (ዮሐ 14፥26) ረገድ የመስቀሉን ሥራ ከፍጻሜ ለማድረስ ይመጣል:: የሉቃስ ወንጌል ኢየሱስ ለመፈጸምና ለማስተማር ስለ ጀመረው ጉዳይ ሁሉ ነው (ሐሥ 1፥1):: የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት በተከናወነው መሠረት የኢየሱስን ቃልና ሥራ ይቀጥላል:: እንደ እውነቱ ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የኢየሱስን ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት ለማብራራት፣ ግልጽ ለማድረግና ገቢራዊ ለማድረግ ነው:: ስለዚህ አንድ ሰው ቊ 7ን እንዲህ በማለት በራሱ አገላለጽ ሊያመለክት ይችላል፣ «ሥራዬን ባልሠራ (ይኸውም በመስቀል በኩል በመሄድ) መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ሥራውን መሥራት አይችልም::»

8«በሚመጣበትም ጊዜ ዓለምን ስለ ኀጢአት[ሽ]፣
ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል:: 9ስለ ኀጢአት — ዮሐ 16፥8-11
ሲባል፣ ሰዎች በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ 10ስለ ጽድቅ፣
ወደ አብ ስለምሄድና ከእንግዲህ ስለማታዩኝ ነው፤
11ስለ ፍርድም፣ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት
ነው::»



[ሽ] 8 ወይም የዓለምን ኀጢአት ይገልጣል

መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያን ስላልሆኑት (ቊ 8-11)፣ ስለ ክርስቲያኖችና (ቊ 12-13)፣ ስለ ኢየሱስ (ቊ 14-15) ይሠራል:: ክርስቲያን ያልሆኑትን በተመለከተ ሥራው ስለ ኀጢአት መውቀስ ነው:: ብዙዎች የእርሱን ሥራ አያከብሩም፤ በመጨረሻም ሥራውን በብርቱ ለመቋቋም ጥረት ያደርጋሉ:: የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለሚቃወሙት ወቀሳው በፍርድ ቀን ሕጋዊ ማስረጃ ይሆንባቸዋል:: ንስሐ ለሚገቡ ግን የመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ ወደ መስቀሉ የሚጋብዝ ይሆናል::[51]

ሦስት ነገሮችን አስመልክቶ ይወቅሳል:: በመጀመሪያ ኀጢአትን በተለይም ያለማመንን ኀጢአት አስመልክቶ:: እግዚአብሔር በሥጋ ኀጢአት የሚያዝን ቢሆንም፣ አንድ ሰው ኢየሱስን አልቀበልም በማለቱ ግን በፍጹም ያዝናል፤ እንደ ተናቀም ይቈጥረዋል:: በሚመጣው የፍርድ ቀን ለዚህ በደል የሚሰጥ ምክንያት አይኖርም:: ሁለተኛ ጽድቅን በተመለከተ ነው፤ ይህን ኢየሱስ ወደ አብ ከመመለሱ ጋር አያይዞታል:: ወደ አብ በመመለሱ እንዴት ነው አንድ ያላመነ ሰው ስለ ጽድቅ የሚወቀሰው? የኢየሱስ ሕይወት በትንሣኤውና በዕርገቱ አማካይነት ቅዱስነቱ በመረጋገጡ መሆን አለበት:: እርሱ ጻድቅ ነው (ሐሥ 3፥14-15፤ 2ቆሮ 5፥21፤ 1ጴጥ 3፥18፤ 1ዮሐ 2፥1፤ 3፥7):: ስለዚህ የእኛ ጽድቅ የሚለካበት መመዘኛ ሆኖአል:: እርሱ ጽድቃችን ካልሆነ በቀር (2ቆሮ 5፥21)፣ በጽድቅ ዐይን ለመታየት ተስፋ የለንም:: ድንቅ ጥረታችን እንኳ ደካማ መሆኑን በኢየሱስ በኩል እናያለን::

[51] «ይወቅሳል» የሚለው የግሪክ ቃል [ኤለንኮ - *elencho*] ሰፋ ያለ ትርጉም አለው፤ የሚከተለውን ማለት ሊሆን ይችላል:- (1) «በቃል ምክር መስጠት፣» (2) «ወደ ብርሃን ማጋለጥ፣» (3) ስሕተትን ማጋለጥ ወይም ማስተባበል፣» (4) ወይም «መውቀስና መቅጣት::» ከእነዚህ ብያኔዎች (ገለጻዎች) ውስጥ ለአንድ ለተወሰነ ግለሰብ አገባብ የሆነው የቱ ነው ለማለው ጥያቄ፣ መንፈስ ቅዱስ ለሚያመጣው ወቀሳ ሰውየው በሚሰጠው ምላሽ ላይ የተወሰነ ነው::

ሦስተኛ ፍርድን በተመለከተ፤ ሰይጣን ተሸንፎአል፤ በደለኛም ሆኖአል፤ ተፈርዶበታልም (ሉቃ 10÷18፤ ሮሜ 16÷20፤ ራእ 12÷12፤ 20÷7-10)። በእግዚአብሔር ሉዐላዊ ፈቃድ ለጊዜው እንዲቆይ ተደርጓል። ነገ ማለዳ በዓለም ላይ የመፍረድ ሥልጣን በኢየሱስ ላይ ያርፋል። በዚህ ዋና ሥራ አማካይነት የእግዚአብሔር ፍርድ በሰይጣን ላይ ይፈጸማል። ያኔ ዓለም የራሱ ፍርዶቹ የቱን ያህል የተዛቡ መሆናቸውን ያያል።[52]

[12]«ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን ግን
ልትሸከሙት አትችሉም። [13]የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ዮሐ 16÷12-15
ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። እርሱ ከራሱ
አይናገርም፤ የሚሰማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም
ወደፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ [14]የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ
ያከብረኛል። [15]የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው፤ እንግዲህ 'የእኔ ከሆነው ወስዶ
እንድታውቁ ያደርጋል' ያልኋችሁ ለዚህ ነው።»

ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ምሽት ማስተዋል የማይችሉት ብዙ ነገር አለ፤ ይህ የሆነው ከፊል አእምሮአቸው በሐዘን ስለ ተጠመደ። ከፊሉ ደግሞ አንዳንዶቹ ጉዳዮች በእምነት ሊቀበሏቸው የሚገቡ በመሆናቸው ነው። ይሁን እንጂ ከኢየሱስ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ በሚገባ ማስተዋል ከሚችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። ችግሩ ይህን ለእነርሱ ለማብራራት ኢየሱስ የማይገኝ መሆኑ ነው። መፍትሔው አሁንም ቢሆን የመንፈስ ቅዱስ ህልዎት (መገኘት) ነው (ዮሐ 14÷26፤ 15÷26፤ 16÷7)።

እንዲህ ያለውን መለኮታዊና ግልጽ ምሪት መቀበሉ በተለይ ለሐዋርያት በጣም አስፈላጊ ነበር። ከዚህ ቀደም እንደ ተገለጸው [የ14÷26 ማብራሪያን ይመልከቱ] ሐዋርያት፣ ሐዋርያዊ አስተምህሮን

[52] D.A. Carson, "The Function of the Paraclete in John 16:7-11," *JBL* 98/4 (1979):547-566.



የመመሥረትና ቀኖናዊ ቅዱሳት መጻሕፍትን የመጻፍ ኃላፊነት ይኖራቸዋል። በመሆኑም ተጨባጩ ሥነ መለኮታዊ አስተምህሮ ተስፋ በቀጥታ የተሰጠው በተለይ ለሐዋርያት ነበር። እንዲህ ሲባል ግን መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ክርስቲያኖችን አይመራም፣ አቅጣጫ አይሰጥም፣ ደግሞም አያስተምርም ማለት አይደለም። ዛሬም ይህንኑ በእርግጥ ይፈጽማል! ስለ እምነታችን፣ በእጅ የማይዳሰሰውንና ግላዊ የሆነውን ነገር ተምረናል፤ ይኸውም በግል እግዚአብሔርን ስለ ማወቅ (ዕብ 8÷11)፣ በእርሱ እንዴት መኖር እንደሚቻል (1ዮሐ 2÷27)፣ እርስ በርስም እንዴት መዋደድ ስለሚቻል ነው (1ተሰ 4÷8-9)። መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ የሆነውን ነገር ያስተምራል (1ቆሮ 2÷10-16)። ትምህርቱ በተለይ ስለ ድነት የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው (1ቆሮ 2÷6-9)፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ከተጻፈውም ጋር አይቃረንም (1ቆሮ 4÷6)። «እውነት ሁሉ» (ቊ 13) የሚለው «ለድነት መልእክት የሚስፈልገው እውነት ሁሉ» ተብሎ ግንዛቤ እንዲያገኝ ያስፈልጋል። የዚህ ምንባብ አንዳንድ መርሖች እኛን የሚመለከቱ ቢሆኑም፣ ተስፋው ሙሉ በሙሉ እርግጠኝነት የእኛ ነው ሳንል እንችላለን። በዛሬው ዘመን ተራ ክርስቲያንና በሐዋርያት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። «መንፈስ ነገረኝ» እያሉ በደንታቢስነት የሚመላለሱት (የሚራመዱት) ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያንና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ጉዳት ሳያደርሱ አልቀረም።

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ኢየሱስን ማክበር ነው። አለቦታው የሚገባ አካል አይደለም፤ ራሱንም ከፍ የማድረግ ፍላጎት የለበትም። ኢየሱስ የአብን ፈቃድ ይፈጽም እንደ ነበረ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም የወልድን ፈቃድና ዐላማ ይፈጽማል (ቊ 14-15)። የኢየሱስ ብቸኛ ዐላማ አብን ማክበርና ትእዛዙን መፈጸም እንደ ነበረ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ወልድን ማክበር ይፈልጋል።

**§ 150መ**
**በኢየሱስ ትንሣኤ ወቅት ሐሤት እንደሚኖር የተነገረ ትንቢት (ዮሐ 16፥16-22)**

16«ከጥቂት ጊዜ በኋላ አይታዩኝም፤ ይሁን እንጂ
ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ።»
17ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹ፣ «'ከጥቂት ጊዜ
በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ
ታዩኛላችሁ' እንዲሁም፣ 'ወደ አብ እሰምሄድ' ሲል ምን
ማለቱ ነው» ተባባሉ፤ 18'ጥቂት ጊዜ' ማለቱስ ምን
ይሆን? የሚለውም ነገር አልገባንም» እያሉ ይጠያየቁ
ነበር።

ይህ የተጋረደ ትንቢት ሐዋርያትን ግራ አጋባቸው፤ «ከጥቂት ጊዜ በኋላ» ሲል ምን ያህል ጊዜ ነው? እርሱን ማየት የማይችሉት በምን ምክንያት ነው? መቼና እንዴትስ ነው ተመልሶ የሚመጣው? ከእኛ አንጻር ሲታይ እነዚህን ጥያቄዎች መመለሱ ቀላል ነው። ኢየሱስ በሚቀጥለው ቀን ሊሰቀልና ሦስት ቀን ሙሉ ዋሻ ውስጥ ሊቀበር ነው። ከዚያ በኋላ ይነሣል፤ ወደ አብ ከማረጉ በፊትም ለአርባ ቀን ለሐዋርያት ይገለጣል። በቅርብ ቀንም በግልጽ ያዩታል።

**ዮሐ 16፥19-22**

19ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደ ፈለጉ ባወቀ ጊዜ
እንዲህ አላቸው፤ «እኔ፣ 'ከጥቂት ጊዜ በኋላ ታዩኛ
ላችሁ፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ
አታዩኝም' ስላልኋችሁ፣ ምን ማለቴ እንደ ሆነ እርስ
በርሳችሁ ትጠያየቃላችሁ? 20እውነት እላችኋለሁ፤ እናንተ ታለቅሳላችሁ፤
ታዝናላችሁም፤ ዓለም ግን ሐሤት ያደርጋል፤ ይሁን እንጂ ሐዘናችሁ ወደ ደስታ
ይለወጣል። 21ሴት ቀኗ ደርሶ ስትወልድ ትጨነቃለች፤ ከተገላገለች በኋላ ግን፣ ሰው
ወደ ዓለም ስለ መጣ ጭንቋን ትረሳለች፤ 22ለእናንተም እንደዚሁ አሁን የሐዘን ጊዜ
ነው፤ ሆኖም እንደ ገና ስለማያችሁ ደስ ይላችኋል፤ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ
የለም።»



ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ትንቢት ተደናግጠው ስለ ነበር በምግብ ገበታው ዙሪያ እርስ በርስ ተወያዩበት። ነገር ግን ምን ማለቱ እንደ ሆነ ኢየሱስን እንዳይጠይቁት ፈርተዋል፤ ወይም አፍረዋል። ስለዚሁ ጉዳይ እንደሚወያዩ ኢየሱስ አስተዋለ። የወደፊቱን የሚያውቅ ስለ መሆኑ ጥርጥር ባይኖረንም፣ እነዚህ ሰዎች ለብቻቸው ሰብሰብ ብለው የሚንሾካሾኩትን ለማወቅ መለኮታዊ እይታ የሚያስፈልገው አልነበረም። በመደነቅ ቅላጼ፣ «'ከጥቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም' ስል በዚህ ላይ እየተወያያችሁ ነበርን?» በማለት ጠየቃቸው። እንዳወቀባቸው ተገንዝበዋል፤ ኢየሱስ ላቀረበው ጥያቄ መልሱንም የሚያውቅ መሆኑን ተረዱ።

ኢየሱስ የዚህ ትንቢት የመጀመሪያና ቀዳሚ ፍጻሜ የሆነውን ሞትና ትንሣኤውን በመግለጽ ግራ ከተጋቡበት ሁኔታ ገላገላቸው። በሚሞትበትና በሚቀበርበት ጊዜ የአይሁድ አለቆችና የሮም የግድያ ትእዛዝ ፈጻሚዎች ሐሤት ያደርጋሉ። ሐዋርያት ያለጥርጥር መሪር ሐዘን ውስጥ ይገባሉ (ማር 16፥10፤ ሉቃ 24፥38፤ ዮሐ 20፥11:15)። ይሁን እንጂ ኢየሱስ እሑድ ዕለት ከሞት በሚነሣበት ጊዜ ሐዘናቸው ወደ ደስታ ይለወጣል። ይህን ጉዳይ በምጥ ጣር ምሳሌነት አጉልቶ አሳይቷቸዋል። አንዲት ሴት በምትወልድበት ጊዜ በጣም ትሠቃይ ይሆናል፤ ቢሆንም እንዲህ ያለው ከባድ ሥቃይ ልጁ ከተወለደ በኋላ በሚመጣው ደስታ ወዲያውኑ ይዋጣል።

ከዚህም በላይ ትንሣኤ ለሐዋርያት የማይነቃነቅ ደስታ ሊያመጣላቸው ነው። አያሌ አስከፊ ልግጫዎችን፣ ድብደባዎችንና ሞትን ይጋፈጡ ዘንድ ይጠራሉ። በጉዞአቸውና በፈተናቸው ሁሉ የትንሣኤ ሐሤት ይኖራቸዋል። የትንሣኤ ሐሤት የራሳቸው ትንሣኤና ሽልማት እውን የመሆኑ ተስፋና ዋስትና ነውና። የትንሣኤን አስደናቂነት ከዐይን ምስክሮች ጋር መጋራት ባንችልም ደስታቸውን

ግን እንጋራለን:: በበ30 ዓ.ም. ዐቢይና እውን እንደሆነ ሁሉ ዛሬም እንዲሁ ነው:: ኢየሱስ ከሞት በመነሣቱ እኛም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን፣ አዲስ አካልን፣ የሰማይ ቤትን፣ ከጌታችንና ከአምላካችን ጋር የዘላለም ሕይወትን ተቀብለናል:: እንዲህ ያለው ተስፋ በሕይወት ላይ በሚደርሱ እጅግ ከፍተኛ ችግሮች ውስጥ ደስታችንን ያጸናልናል::

**§ 150ሠ**
**ጸሎት እንደሚመለስና ሰላም እንደሚሆን የተሰጠ ተስፋ**
**(ዮሐ 16÷23-33)**



[23]«በዚያ ቀን ከእኔ ምንም አትለምኑም፤
እውነት እላችኋለሁ፤ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ
ይሰጣችኋል:: [24]እስከ አሁን በስሜ ምንም
አልለመናችሁም፤ ለምኑ ትቀበላላችሁ፤ ደስታችሁም
ሙሉ ይሆናል::
[25]እስከ አሁን የነገርኋችሁ በምሳሌ ቢሆንም
እንኳ፣ ከእንግዲህ ግን ስለ አብ በምሳሌ ሳይሆን በግልጽ
የምናገርበት ጊዜ ይመጣል:: [26]በዚያ ቀን በስሜ ትለም
ናላችሁ፤ ይህም በእናንተ ፋንታ አብን እለምናለሁ ማለቴ አይደለም:: [27]አብ
ወደዳችሁኛና ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ ራሱ ይወዳችኋል::
[28]ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ አሁን ግን ዓለምን ትቼ ወደ አብ
እሄዳለሁ::»

ኢየሱስ «ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላሁ» የሚለውን አነጋገር በማብራራት ሁለተኛውን የትንቢት ፍጻሜ ምንነት ገለጸ:: ኢየሱስ ተወካዩ በሆነው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ ሐዋርያቱ ሲመለስ፣ ኢየሱስን ለጥያቄ አይፈልጉትም:: ይህ ማለት ግን ኢየሱስ ፈቃዱን ይገልጥላቸው ዘንድ (ከሐሥ 1÷24-26 ጋር ያነ) ሐዋርያቱ ጥያቄ አይጠይቁም ማለት አይደለም:: እንዲህ ሲባል፣ መንፈስ ቅዱስ ትውስታቸውን ይመራል፤ በስብከትና ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጻፍ (ዮሐ 14÷26፤ 15÷26፤ 16÷13) ሐዋርያዊ አስተምህሮን ለመመሥረት አስፈላጊ የሆነውን እውነት ሁሉ ያስተምራቸዋል ማለት ነው:: እንዲያውም የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ከኢየሱስ ትምህርት ይልቅ



ግልጽ ይሆናል:: ኢየሱስ ሊመጣ ያለውን ለመግለጥና (ለምሳሌ 15፡1-8፤ 16፡17-21) ኢአማኝያን የማይቀበሉትን ለመደበቅ (ማቴ 13÷10-15) ብዙ ጊዜ ምሳሌያዊ ቋንቋን ተጠቅሞአል:: መንፈስ ቅዱስ ግን ምሳሌያዊ ቋንቋን መጠቀም አያስፈልግውም:: ስለ አብ በግልጽ ይነግራቸዋል (ዕብ 8÷11):: ይህ የጠራ መገለጥ ወደ ላቀ ግልጽ ግንኙነት ይመራል::

ከዚህም በላይ ከአብ ጋር ቀጥታ ግንኙነቶች ስላለን፣ ልመናችንን በቀላሉ ማቅረብ እንችላለን:: ኢየሱስ ለእኛ እንደሚማልደው ዐይነት አይደለም (ቍ 26-27):: እንዲያ አይደለም፤ እኛ በኢየሱስ ስም ልመና በምናቀርብበት ጊዜ አብ ምላሽ እንዲሰጥ ያደርገዋል:: የኢየሱስ ተከታዮች እንደ መሆናችን መጠን የመላለም አምላክ ልመናችንን ይሰማል!

እንግዲህ በኢየሱስ ስም መለመን ልመናው «ይፈጸም ዘንድ» በጸሎት መደምደሚያ ላይ የሚታከል ምትሀታዊ ቀመር አይደለም:: በአይሁዳውያን ዘንድ የአንድ ሰው ስም ባሕርይና ሥልጣኑን ይወክላል:: ስለዚህ በኢየሱስ ስም መለመን ማለት ከእርሱ ጋር ያለንን ወዳጅነት መሠረት በማድረግ ሥልጣኑ ሥር ወደ አብ መቅረብ ነው (ዮሐ 15÷14-15):: ከኢየሱስ ጋር እውነተኛ ኅብረት ካለን፣ ጥያቄያችንም ከባሕርይና ከዓለማዎቹ ጋር ስምም ከሆነ፣ በርግጥ አብ መልስ ይሰጠናል:: እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሐዋርያት አይሁዳውያን አንደ መሆናቸው መጠን እንደ አይሁዳውያን ጸልየዋል:: አሁን ደግሞ እንደ ክርስቲያኖች በኢየሱስ በኩል ይጸልዩ ዘንድ ጥሪ ያቀርብላቸዋል::

**ዮሐ 16÷29-33**

[29]ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አሉ፤
«አሁንም እኮ ያለ ምሳሌ ግልጽ እየተናገርህ ነው::
[30]አሁን ሁሉን ነገር እንደምታውቅና ማንም ሲጠይቅህ
እንደማያስፈልግ ተረድተናል፤ ይህም ከእግዚአብሔር
እንደ ወጣህ እንድናምን አድርጎናል::

[31]ኢየሱስም መለሰ እንዲህ አላቸው፤ «አሁንስ አመናችሁ ማለት ነው?[p] [32]እነሆ፤ ሁላችሁም በየፊናችሁ የምትበታተኑበት ጊዜ ይመጣል፤ ያም ጊዜ አሁን ነው:: እኔንም ብቻዬን ትተዉኛላችሁ፤ ይሁን እንጂ አባቴ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም::

[33]«በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ፣ ይህን ነግሬአችኋለሁ:: በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ::»

*[p]31 ወይም በስተ መጨረሻው አመናችሁ!*

ኢየሱስ ከአብ መጥቻለሁ ወደ እርሱም እመለሳለሁ ባለ ጊዜ በዐሥራ አንዱ ዘንድ ይብላላ ለነበረው ጥያቄ ግልጽ መልስ ሰጠ:: ጥያቄያቸውን ከማቅረባቸው በፊት እርሱ በመገንዘቡ ተገረሙ:: በመልሱም የሰውን ልብ የመረዳት መለኮታዊ ሥልጣኑ አረጋገጡ::

ይህ ግራ ተጋብተው ከነበሩበት ደቀ መዛሙርት የብርሃን ጭላንጭል ቢሆንም የተረዱት ግን ተረድተናል ካሉት በታች ነበር:: በመጀመሪያ ይህ ድርጊት የመንፈስ ቅዱስን መምጣት የሚጠብቅ ሆኖ ሳለ ኢየሱስ ለእነርሱ በግልጽ መናገር የጀመረ መሰላቸው:: ሁለተኛ ማንም ኢየሱስን መጠየቅ የማይፈልግበት ጊዜ የመጣ መሰላቸው (ቍ. 23):: ይህም የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ይጠብቃል:: ይህን የማያፈናፍን ንግግር ለመዝጋት ለደቀ መዛሙርቱ ይህ አመች መንገድ ን አይቀርም:: እስካሁን ያቀረቡት ጥያቄ ሁሉ አቅጣጫውን የሳተ ይመስላል (14÷5:8:22):: ትክክለኛውን ጥያቄ ባለማቅረባቸውም ተገሥጸዋል (16÷5)::

የሐዋርያቱ ግንዛቤ መጠነኛ ቢሆንም ትዝብቱ እንዳለ ሆኖ ኢየሱስ አሞገሳቸው:: ከዚያም ወደ መጀመሪያው ርእስ ጉዳይ በመመለስ የሚበተኑ መሆናቸውን ዳግመኛ አስጠነቀቃቸው (ማቴ



26፥31):: እያንዳንዳቸው ወደየቤታቸው እንደሚበተኑም ነገራቸው:: ይህን ቢፈጽሙ ኖሮ ወደ ገሊላ በሸሹ ነበር:: ከዚያ ይልቅ ኢየሱስ እንዳዘዛቸው ከእርሱ ለመገናኘት ወደ ገሊላ ከመመለሳቸው በፊት (ማቴ 26፥32)፣ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ዐሥር ቀናትን አሳለፉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ወደ ገሊላ በተመለሱ ጊዜ አልተበታተኑም:: ስለዚህ «እያንዳንዳችሁ ወደግሉ መንገድ» በሚለው መተርጐም ይኖርብናል:: ይህም ከሰዓታት በኋላ የጌቴሴማኒን ትዕይንት አጉልቶ ያሳያል::

ኢየሱስ ለሐዋርያቱ ሰላምን ለመስጠት ሲል ስለዚህ ዘግናኝ መበተን ትንቢት ተናገረ:: እንዲህ ያለ ሥቃይ ያለበት ትንቢት እንዴት ሰላም ሊያመጣ ይችላል? ርግጥ በዚያ ወቅት ሰላም አያመጣም፤ ነገሮች ከተረጋጉ በኋላ ግን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ እርሱና አብ አንድ እንደ ሆኑ፣ አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ እንዳለ፣ እነዚህ ንጥር ብለው የቀረቡት ትንቢቶች አጉልተው ያሳያሉ:: ኢየሱስ ያለፈበት ሥቃይ ከእርሱ ቍጥጥር ውጭ ያልነበረ መሆኑን ይህ ያሳያል:: በስቃዩ አማካይነት በእርግጥ አሸናፊ ሆኖአል:: ይህ መተማመኛ ደቀ መዛሙርት ጠላት ከሆነው ዓለም ስደት በሚገጥማቸው ጊዜ ደግፎ ይይዛቸዋል:: ስለዚህ እነዚህ ዘግናኝ ትንቢቶች ለሐዋርያቱ ውሎ አድሮ ታላቅ ሰላምን ያመጣሉ (ዮሐ 14÷27):: በመሆኑም የዚህ አስጨናቂ ነግግር መደምደሚያ፣ «ልባችሁ አይጨነቅ/አይዞአችሁ![53] እኔ ዓለምን አሸንፌአለሁ» ነው::

**§ 151**
**የጌታ ጸሎት**
**ዮሐ 17**

የጌታ ጸሎት ተብሎ የሚታወቀው (ማቴ 6፥9-12፤ ሉቃ 11፥2-4) ደቀ መዛሙርቱ ይጸልዩ ዘንድ ኢየሱስ የሰጣቸው ነው:: ዮሐንስ 17

[53] «ልባችሁ አይጨነቅ»/«አይዞአችሁ» [ታርሴይ - tharsei] የሚለው ግስ ከአንድ ጊዜ በቀር (ማር 10፥49) አገልግሎት ላይ የዋለው በኢየሱስ ብቻ ነው (ማቴ 9፥2:22፤ 14፥27፤ ማር 6፥50፤ ዮሐ 16፥33፤ ሐሥ 23፥11)::

በእርግጥ የኢየሱስ ጸሎት ነው:: ወንጌላቱ አንዳንድ ጊዜ የኢየሱስን ጸሎት አይመዘግቡም (ከማቴ 11፥25-26፤ ከማር 14፥36፤ ከሉቃ 10፥21፤ 23፥34:46፤ ከዮሐ 11፥41 ጋር ያነ):: ከዚህ ላይ በቅዱስ ምድር ላይ እየተራመድን ነው::

በዚህ ጸሎት ኢየሱስ ለራሱ (ቍ. 1-5) ለደቀ መዛሙርቱ (ቍ. 6-19) እና ለወደፊቷ ቤተ ክርስቲያን ጸልየዋል:: ምንም እንኳ («ክብር፣» «የዘላለም ሕይወት» «እመን» «ፍቅር» «ቃል» «ዓለም»::) የሚሉት ቃላት የዮሐንስ ቢሆኑ የኢየሱስን ልብ ይገልጻሉ:: በዚህ የመጨረሻ ጸሎቱ በአብ ክብር ያለውን መጨነቅ (ቍ. 1:4-5)፣ ከአብ ጋር ያለውን ግንኙነት (ቍ. 7-8:10:24-26) የደቀ መዛሙርቱ ድነት (ቍ. 2-3:12) እና የሦስቱን አንድነት (ቍ. 11:21-23) ያሳያል:: ይህ ጸሎት ከፋሲካ ምግብ ጋር የሚስማማ ማጠቃለያና ከኢየሱስ ተሰግዎዊ አገልግሎት[54] እጥርታ/ማጠቃለያ ጋር የሚስማማ ነው::

**ዮሐ 17፥1-5**

[1]ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ፣ ወደ ሰማይ
ቀና ብሎ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ «አባት ሆይ፤ ጊዜው
ደርሶአል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ ልጅህን አክብረው፤
[2]ከአንተ ለተቀበላቸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት
እንዲሰጥ በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥተኸዋልና::
[3]እውነተኛ አምላክ
የሆንኸውን አንተንና የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም
ሕይወት ናት:: [4]የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርሁህ:: [5]እንግዲህ አባት
ሆይ፤ ዓለም ሳይፈጠር ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር በአንተ ዘንድ አክብረኝ::

[54] ከ D.A. Black, "On the Style and Signifecance of John 17," *CTR* 3 (1988): 141-159 ጋር ያነጻጽሩ::



ኢየሱስ ይህን ጸሎት አንድ ደርብ ባለው ቤት ሳለ የጸለየ ይመስላል:: ይሁን እንጂ እርሱና የእርሱ የሆኑት በዚህ ጊዜ ቤቱን ትተው ወደ ቄድሮን ሸለቆ በመጓዝ ላይ ሳይሆኑ አልቀረም (ማቴ 26፥30፤ ዮሐ 18፥1):: ኢየሱስ በአይሁድ የጸሎት አቋቋም መሠረት ጸልዮአል:- ዐይኖቹ ወደ ሰማይ አቅንተው እጆቹም ወደዚያው ሳይዘረጉ አልቀሩም:: «አባት ሆይ» በማለትና «ልጅህን አክብረው» ብሎ ለራሱ በመጸለይ ይጀምራል:: በጨረፍታ ሲያዩት ድርጊቱ ራስ ወዳድነት ይመስላል:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ክብርን የጠየቀው ክብርን ወደ አብ ለመመለስ ነው:: ከዚህም በላይ የኢየሱስ ክብር የሚመጣው በመስቀል በኩል ነው:: «ጊዜው ደርሶአል» (ከ2፥4፤ 7፥8:30፤ 8፥20፤ 12፥23፤ 13፥1 ጋር ያነ) አለ:: ይህ አባባል የመሞቻ ጊዜውን ያመለክታል:: በመታዘዝ ሞት (ቍ. 4)፣ አብን ያከብራል:: በትንሣኤውና በዕርገቱ ደግሞ አብ ኢየሱስን ያከብረዋል:: ይህ ራስ ወዳድነት አይደለም:: በተጨማሪም «አክብር» [ዶክሳዞ - doxazo] የሚለው ቃል «ክብር መስጠት» ወይም «ሞገስ መስጠት» ማለት ነው:: የራስን ባሕርይም ያመለክታል:: በሌላ አነጋገር ኢየሱስ የመጣው አብን ለመወከል ነው (ቍ. 6፤ ከዮሐ 1፥18፤ ከዕብ 1፥3 ጋር ያነ):: ከመቃብር በማስነሣትና በኋላም ወደ መንግሥተ ሰማይ በመውሰድ ያግዘው ዘንድ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔርን ይጠይቃል:: በዚህ ሁኔታ በኢየሱስ ማንነት በኩል የእግዚአብሔር ክብር ለደቀ መዛሙርቱ ይገለጻል::

ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ እንጂ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስተዋወቅ ብቻ አይደለም:: ይህም «ድነት» ብለን የምንጠራው አሠራር ነው:: ባጭሩ ኢየሱስ የዘላለምን ሕይወት ለመስጠት ሥልጣን ያለው ለሁሉ ሳይሆን አብ ለሚሰጠው ብቻ ነው:: ይህ ማለት እግዚአብሔር ሚዛናዊነት በጐደለው መልኩ አንዳንዶችን ይድኑ ዘንድ ይመርጣል፤ ሌሎችን

ደግሞ ይፈርድባቸው ዘንድ ይተዋቸዋል ማለት ነውን? እርግጥ ነው እግዚአብሔር ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እርሱ ሊመጣ አይችልም (ማቴ 24፥22፤ ሮሜ 8፥29-30፤ ኤፌ 1፥5፡11)። ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር አስቀድሞ ውሳኔ በሦስት ነገሮች ላይ (ከሉዐላዊው ፈቃድ በተጨማሪ) የተመሠረተ መሆኑን የሚያሳይ ይመስላል፡- (1) በአስቀድሞ ዐዋቂነቱ (ሮሜ 8፥29፤ 1ጴጥ 1፥2)። እግዚአብሔር አንድ ሰው ከመወለዱ በፊት ልቡን ስለሚያውቅ የአንድ ሰው ዕጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን በትክክል መመዘን ይችላል። (2) በክርስቶስ (ኤፌ 1፥4፡11)፤ በክርስቶስ የሆነ ሰው ሁሉ ይድን ዘንድ አስቀድሞ ተወስኖለታል፤ እርሱን ያልተቀበለ ሁሉ ይጠፋ ዘንድ አስቀድሞ ተወስኖበታል። (3) የሰው አጸፋ (ማቴ 22፥14፤ 2ጴጥ 1፥10)፤ የማቴዎስ 22፥1-14 ምሳሌ ለእግዚአብሔር ጥሪ መልስ የሰጡ ሁሉ ለግብዣው በእርሱ የተመረጡ መሆናቸውን የሚመለክት ነው። በተጨማሪም ቅዱስ ሕይወት በመኖር መመረጣችንን የላቀ ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ እንደምንችል ጴጥሮስ ይናገራል። እግዚአብሔር በሉዐላዊው ሕጉ ኢየሱስን የተቀበሉ ሁሉ ይድኑ ዘንድ አስቀድሞ የተወሰኑ መሆናቸውን፣ ያልተቀበሉት ሁሉ ግን ይጠፉ ዘንድ አስቀድሞ የተወሰኑ መሆናቸውን ይፋ ያደረገ (ያወጀ) ይመስላል። ከዚህም በላይ አንድ ሰው ከመወለዱ በፊት ምን እንደሚመርጥ እግዚአብሔር ያውቃል።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ምርጫ ሚዛናዊነት በጉደለው ወይም በራሱ ፈቃድ ሳይሆን ሰው በሚሰጠው አፀፋ ላይ የሚመሠረት ነው በማለት መደምደም እንችላለን። እርግጥ ነው እግዚአብሔር ሰው ሁሉ ይድን ዘንድ ይፈልጋል (2ጴጥ 3፥9)፣ የኢየሱስ መሥዋዕትነትም ይህን ለመፈጸም ኃይል አለው (1ዮሐ 2፥2)።



የምንነጋገረው ስለ ዘላለማዊ ሕይወት ነው። ይህ የጊዜ ልክ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግንኙነት ነው። የዘላለም ሕይወት ማለት እግዚአብሔርን በግልና ከልብ ማወቅ ነው። የሚታወቀው በረቂቅ አስተንትኖ ሳይሆን በኢየሱስ በኩል ይሆናል። ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የምንችለው በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በኩል ነው። የሚደነቀው ነገር ኢየሱስ የሚናገረው ነገሮቹ እንደ ተፈጸሙ አድርጎ ነው (ቊ 4-5)። እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ ለመፈጸም ቈርጦ የተነሣ በመሆኑ ይህን ማድረግ ይችላል። ኢየሱስ የራሱን ድርሻ ለመፈጸም ቈርጦ በመነሣት፣ እግዚአብሔር የራሱን ድርሻ እንዲፈጽም ይጠይቃል። ይኸውም በትንሣኤና በዕርገቱ እንዲያከብረው ነው (ቊ 5)። ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ምን ዐይነት ክብር እንደ ነበረው መገመት እንጂ ሌላ ማድረግ አንችልም። በእግዚአብሔር መልክ እንደ ነበር እናውቃለን (ዮሐ 1፥1-4፤ ፊል 2፥6፤ ቈላ 1፥15፡19)። ከእግዚአብሔር ጋር ሠራ (ለምሳሌ ዘፍ 1፥26)፤ በእግዚአብሔርነቱ ታየ (ኢሳ 11፥3-5፤ ሕዝ 40፥3፤ ዳን 10፥6)፤ ዳግም በእግዚአብሔርነቱ ይመለካል (ራእ 5)።

**ዮሐ 17፥6-12**

6«ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን
ገለጥሁላቸው። የአንተ ነበሩ ለእኔ ሰጠኸኝ፤ እነርሱም
ቃልህን ጠብቀዋል። 7የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ
አሁን ዐውቀዋል። 8ምክንያቱም የሰጠኸኝን ቃል
ሰጥቻቸው ተቀብለዋል፤ እኔም ከአንተ እንደ ወጣሁ በእርግጥ ዐውቀዋል፤ አንተ
እንደ ላከኸኝም አምነዋል፤ 9እነርሱ የአንተ ስለ ሆኑ እጸልይላቸዋለሁ፤ ለሰጠኸኝና
የአንተ ለሆኑት እንጂ ለዓለም አልጸልይም። 10የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፤ የአንተ
የሆነውም ሁሉ የእኔ ነው፤ በእነርሱም ከብሬአለሁ። 11ከእንግዲህ እኔ በዓለም
አልቈይም፤ እነርሱ ግን በዓለም ውስጥ ናቸው፤ እኔም ወደ አንተ መምጣቴ ነው።
ቅዱስ አባት ሆይ እኛ አንድ እንደ ሆንን፣ እነርሱም አንድ እንዲሆኑ በሰጠኸኝ ስም

ከስቧኂቸው፤ ጠበቅኂቸውም፤ የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ከአንዱ ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም::»

አማኞች ሁሉ ከአብ ለኢየሱስ የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው (ቍ 21):: ከእነዚህ ስጦታዎች መካከል ኢየሱስ ወዳጆቼ የሚላቸው ልዩ ሰዎች ነበሩ:: እነሱን ሐዋርያት አላቸውና ከአብ ጋር የሚደርገውን ንግግር እንዲሰሙ ፈቀደላቸው:: ሐዋርያት ኢየሱስን ከመከተላቸው በፊት የእግዚአብሔር ናቸው (ቍ 6):: እግዚአብሔርን ለመከተል ልባቸውን አዘንብለው ነበር:: እንዲያውም ቢያንስ ግማሾቹ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ነበሩ (ዮሐ 1÷35-51፤ የክፍል 28 ማብራሪያን ይመልከቱ)::

ኢየሱስ የአባቱን ስጦታዎች ወደዳቸው፤ ወይም ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጣቸው:: ይህን ያደረገው በሁለት መንገድ ነው:: በመጀመሪያ ኢየሱስ በአባቱ ቃል ሞላቸው (ቍ 6:8):: በራሱ ለመናገር ወይም ራሱን ለማክበር ፈቃደኛ አልሆነም (ዮሐ 7÷17፤ 8÷28፤ 12÷49):: ሁለተኛ ኢየሱስ በሌላ አካል ሥልጣን የሚሠራ ተወካይ መሆኑን ለተከታዮቹ ግልጽ አደረገ (4÷34፤ 5÷30፤ 6÷38):: በዚህ ጊዜ ሐዋርያት ኢየሱስ አብን የቱን ያህል እንደሚወክለው እየተገነዘቡ መጡ (ቍ 7-8)::

ኢየሱስ አሁን ዓለምን ትቶ ሊሄድ ነው:: ከእንግዲይ በግሉ ደቀ መዛሙርቱን አያስተምርም፤ አይንከባከብም:: ስለዚህ አባቱ ስለ እነርሱ ጣልቃ እንዲገባ ይጠይቀዋል:: ይህ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚያደርገው የምልጃ ሥራው መጀመሪያ ነው (ሮሜ 8÷34፤ ዕብ 7÷25፤ 9÷24፤ 1ዮሐ 2÷1):: ይህ ለማያምኑት እንዲሆን ያልተደረገ (ቍ 9) ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ የተደረገ ስጦታ ነው:: እግዚአብሔር የኢየሱስን ጸሎት በሰማ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስና አብ አንድ ሆነው እንደሚያስቡና እንደሚሠሩ ያለጥርጥር ያውቃሉ::



ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሳለ ዐሥራ ሁለቱን በሚገባ ጠበቃቸው (ተንከባከባቸው):: አሁን ደግሞ አብ ዐሥራ አንዱን በሚገባ እንዲጠብቃቸው ይጠይቃል:: ይሁዳ በትንቢት እንደ ተነገረው ኢየሱስን ትቶ ሄደ (ዮሐ 13÷18፤ መዝ 41÷9፤ 69÷25፤ 109÷6-8):: እንዲህ ላለው ክሕደት «የጥፋት ልጅ» ወይም አመት (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) እንደ ተረጐመው «ለጥፋት የተመደበው» የሚል መጠሪያ ወጣለት:: ይህ ሐረግ የዐመፅ ሰውን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ ውሎአል (2ተሰ 3÷3)::

**ዮሐ 17÷13-19**

[13]«አሁን ወደ አንተ መምጣቴ ነው፤ ነገር ግን
ደስታዬ በእነርሱ ዘንድ የተሟላ እንዲሆን፣ አሁን
በዓለም እያለሁ ይህን እናገራለሁ:: [14]ቃልህን
ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ፣ እነርሱም
ከዓለም ባለመሆናቸው
ዓለም ጠልቶአቸዋል፡ [15]የምለምንህም ከክፉው እንድትጠብቃቸው እንጂ፣ ከዓለም
እንድታወጣቸው አይደለም:: [16]እኔ ከዓለም እንዳልሆንሁ ሁሉ፣ እነርሱም ከዓለም
አይደሉም:: [17]ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው[ዶ]:: [18]አንተ ወደ ዓለም
እንደ ላክኸኝ እኔም ወደ ዓለም ልኬአቸዋለሁ:: [19]እነርሱ በእውነት የተቀደሱ
እንዲሆኑ፣ ራሴን ስለ እነርሱ ቀድሻለሁ::»

*[ዶ]17 በግሪኩ ሀጊያዘ የሚለው ቃል ለሆነ ተግባር መለየት ወይም መቀደስ ማለት ነው፤ ቍ 19 ይመ::*

ለደቀ መዛሙርቱ ይህ የደኅና ሁኑ ንግግር ነው:: ለኢየሱስ ደግሞ ይህ ወደ ቤት መምጫ ነው:: ከረዥምም ሥቃይ በኋላ ከአባቱ ጋር፣ ከራሱ መለኮታዊ ባሕርይ ጋር ሊገናኝ ነው:: ነገር ግን በደስታ ላይ ቢሆንም ስለ ደቀ መዛሙርቱ ሐዘን ተሰምቶታል:: እርሱ ከሄደ በኋላ ከአብ የመጣው ኢየሱስ ወደ አብም በእርግጥ የተመለሰው ኢየሱስ ለእነርሱ ለመማለድ ወደ አብ የተመለሰ መሆኑን እንዲያምኑ

ያስፈልጋል:: እንዲህ ያለው እምነት ደቀ መዛሙርቱ በስደት ውስጥ እያሉ እንኳ ደስታውን ይጋሩ ዘንድ ያበቃቸዋል::

ለክርስቲያን ስደት አይቀሬ ነው (ዮሐ 15፥18-25 ውስጥ ያለውን ማብራሪያ ይመ):: እንደ ዓለም አንኖርም፤ ወይም ድርጊቱን አንደግፍም:: እንደ እውነቱ ከሆነ እኛ የዓለም ጨውና ብርሃን ነን (ማቴ 5፥13-16):: መልእክታችን ያጸናል፤ ያነጻልም፤ ይህ የሚሆነው ግን ያለሥቃይ አይደለም:: የእግዚአብሔር ቃል የማያምነው ዓለም ትዕቢቱን፣ ልበ ደንዳናነቱንና ዘልዛላነቱን እንደ ያዘ ሥጋት ውስጥ ይከተዋል:: በዚህ ምንባብ ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል በክርስቲያኖችና በዓለም መካከል፣ የሚለይ መሣሪያ ነው በማለት ሁለት ጊዜ ቀድሞ የተናገረው ከዚህ የተነሣ ነው:: እርሱ የዚህ ዓለም እንዳልሆነ ሁሉ ክርስቲያኖችም የዚህ ዓለም አለመሆናቸውን ሁለት ጊዜ ሙሉ ገለጸ::

ለስደት ያለው መፍትሄ ዓለምን ትቶ መሄድ ሳይሆን ዓለም ውስጥ ሆኖ መቀደስ ነው:: ኢየሱስ፣ ክርስቲያኖች ሥቃይ እንዳይደርስባቸው አልጸለየም፤ ከክፉ እንድንጠበቅ ጸለየ እንጂ:: ይህ ለአካላችን ሳይሆን ለነፍሳችን የቀረበ ጸሎት ነው:: በአይሁድና በሮም ባለሥልጣናት አማካይነት ሰይጣን በሺህ የሚቈጠሩ ክርስቲያኖችን አሠቃይቶአል፤ ቢሆንም ኢየሱስ የነፍሳችን ጠባቂ ነው::

የክርስቲያን ዓላማ በማንኛውም መንገድ ኢየሱስን መምሰል ነው:: እርሱ እንደ ተሠቃየ ሁሉ እኛም እንሠቃያለን:: በዓለም ተቀድሶ እንደ ነበር (ይኸውም፣ ተለይቶ፣ ልዩ ሆኖ፣ ቅዱስ ሆኖ ማለት ነው) እኛም መቀደስ አለብን::

ዮሐ 17፥20-23

20«የእነርሱን ትምህርት ተቀብለው በእኔ
ለሚያምኑ ጭምር እንጂ ለእነዚህ ብቻ አልጸልይም፤
21ይህም፣ አባት ሆይ፤ አንተ በእኔ፣ እኔም በአንተ
እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን
ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው:: 22እኛ አንድ እንደ ሆንን እነርሱም አንድ
እንዲሆኑ፣ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ:: 23ይህም እኔ በእነርሱ አንተም በእኔ
መሆንህ ነው:: አንተ እንደ ላክኸኝና እኔን በወደድኸኝ መጠን እነርሱንም
ወደድሃቸው ዓለም ያውቅ ዘንድ፣ አንድነታቸው ፍጹም ይሁን::»



እስከዚህ ድረስ ኢየሱስ ለራሱና (ቍ 1-5) ለደቀ መዛሙርቱ ጸልዮአል (ቍ 6-19):: አሁን ደግሞ በሐዋርያቱ ስብከት ክርስቲያኖች ወደሚሆኑት ሐሳቡን መለሰ:: ግድ የተሰኘበት ቀዳሚ ነገር የአማኞች ሁሉ አንድነት ነው:: እርግጥ ነው የተከፋፈለች ቤተ ክርስቲያን ለኢየሱስ ከፍተኛ ሕፍረት ናት:: በሰሜን አሜሪካና በካናዳ ብቻ ከ300 በላይ የተለያ የቤተ እምነት (የዲኖሚኔሽን) ቡድኖች አሉ:: ይህም በቤተ እምነቶች ውስጥ ስም የሌላቸውን ቡድኖች ሳይጨምር ነው:: ኢየሱስ ለቤተ እምነታዊ ስም ወይም ማእከሎች ትኩረት አይሰጥም፤ የሚያውቀው አንድ አካልን ብቻ ነው (ኤፌ 4፥4-6)::

በቤተ ክርስቲያን አጣማሪዎች ወይም በአስተምህሮአዊ መድረክ አማካይነት ድርጅታዊ አንድነትን የሚሹት በየዋህነት ብሩህ ተስፋን የሚናፍቁ ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም::[55] ቤተ እምነቶች የተመሠረቱት በሰው ማንነትና ፍልስፍናዎች ላይ ነው:: አንድ ሰው ለቤተ እምነት ያለውን ታማኝነት ወይም ለአስተምህሮ ሚና ያለውን ታማኝነት ለጌታ ካለው ታማኝነት ጋር ያምታታ ስለሆነ መከፋፈያ መለዮአችንን ወይም

[55] T.E. Pollard, "'That they All Be One' (John 17:21) and the Unity of the Church," *ExpT* 70 (1958-59): 149-150 በሚለው ላይ ኢየሱስ ልብ ብሎ የሚያየው አንድነት ድርጅታዊ ወይም ቤተ እምነታዊ አንድነት አይደለም ይላል:: በኢየሱስና በአባቱ አምሳል የተቀረጸ አንድነት አይደለም፤ በኢየሱስና በአባቱ አምሳል የተቀረጸ አንድነት በመሆኑ (ዮሐንስ 17፥11:21:22-23)፣ በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነት ነው:: ኢየሱስና አባቱ ደግሞ ልዩ ነበሩ:: Pollard ባቀረበው ሐሳብ ውስጥ ይህ ትክክል ነው፤ ኢየሱስ የሚመኘው አንድነት በአንድ ጣራ ሥር በመሆን ድርጅታዊ አንድነት ሳይሆን፣ በመንፈስና በዐላማ የተባበሩ የግለሰቦች አንድነት ነው::

አስተምህሮዊ ልዩነታችንን በቶሎ እንተዋለን ተብሎ አይታሰብም:: ዝም ብሎ ክርስቲያን መሆን «ኢታማኝነት» ይሆናል:: የእግዚአብሔር እውነተኛ ሰዎች የመሆናችን ግልጽ መለዮ የሚያስፈልገን ይመስለናል (ለምሳሌ ካቶሊክ፣ ባፕቲስት፣ ሜቶዲስት፣ ሉትራን፣ ፔንቴኮስታል፣ ወዘተ)::[56]

ጥምረት ከማጽደቅ ጋር አንድ ነው ብለን እስከማመን ድረስ ተደናግረን ነበር:: ይህም ሕይወትን ከሚደግፍ አካሄድ ጋር የምንኀዝ ከሆን፣ ጳጳሱን መቀበል አለብን የሚል ነው:: ወይም በዓለም ዐቀፋዊ የምስጋና ጸሎት የምንካፈል ከሆን ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ መንፈስ ቅዱስ ያላቸው መሆኑን እንክዳለን ማለት ነው:: በምግብ ክምችት ረገድ ከሜቶዲስቶች ጋር የምንተባበር ከሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የሚለውን ሁሉ መቀበል አለብን:: እዚህ ላይ ስለ ሁለት ነገሮች ጥንቃቄ ማድረግ አለብን:: (1) የዳንነው የአስተምህሮአዊ ልዩ ዝርዝሮችን በመከተል ሳይሆን በኢየሱስ ነው:: ድርድር ውስጥ ሊገቡ የማይችሉት ነገሮች ጥቂት ናቸው:- የኢየሱስ የደም ማስተሰርያ፣ ትንሣኤ፣ ክርስቶስ አምላክ መሆኑ ወዘተ:: ብዙ ጊዜ የሚለያዩን ግን ዐበይት ያልሆኑ ነገሮች ናቸው:- የጌታ እራት አቀራረብ፣ የአመራር ዘይቤ፣ ሺህ ዓመታዊ ሥርዐቶች፣ ልብሰ ተክህኖ፣ መዝሙር፣ ወዘተ:: የኢየሱስ አካል አባል ካልሆነ ሰው ጋር የሚኖር ኅብረትን የማንቀበልበት ጊዜ አለ:: ይሁን እንጂ ለራሳችን

[56] D. Bjork በሥላሴ ባሕርይ ላይ በመመሥረት በተልዕኮ ውስጥ የማንኛውም ዐይነት ዐለም ዐቀፋዊ አንድነት አስፈላጊ ነው ይላል፤ ይኸውም ግለሰባዊ መለዮ ሳይጠፋ የዓላማ አንድነት ማለት ነው:: ስለዚህ ክርስቲያን ቡድኖች ከሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር ያላቸውን ልዩነት መሠረት በማድረግ ሳይሆን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያላቸውን ግንኙነት መሠረት በማድረግ ራሳቸውን መግለጽ ይገባቸዋል በማለት ይከራከራል:: እንዲህ የሚከራከረውም በሚከተለው ርእስ ሥር ነው፤ "Toward a Trinitarian Understanding of Mission in Post-Christendom Lands," *Missiology* 27/2 (1999): 231-234.



እዚህ ግባ ለማይባል መድረክ ስንል የክርስቶስን አካል መከፋፈል የለብንም:: (2) ዓለም ዐቀፋዊ የወንጌል ተልእኮ በእጅጉ ጉዳት የደረሰበት በክፍሎች ነው:: ያለንን ሀብት ወደ ጥቃቅን ምድቦች እናከፋፍላለን፤ ከዚያም የሌላውን ድርጅት ጥረት ከንቱ ለማስቀረት ወይም ለመደጋገም እንሞክራለን:: ድርጊቱ በሚሰቀጥጥ ሁኔታ አስቂኝ ነው:: ሌላው ቀርቶ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ታወቁ ቋንቋዎች በመተርጐም፣ በአገራችን የቤተ ሰብንና የሃይማኖትን ፖሊሲ በመወሰን፣ በከተሞቻችን ቤት አልባነትን በማስወገድ እናቶችን በማልበስና መጠለያ በመስጠት የውጭ አገር ተማሪዎችን በወንጌል በመድረስ ወዘተ ጥረቷን ብታስተባብር ኖሮ የዓለምን ረሀብና ሥቃይ በማቃለል ረገድ አያሌ ጉዳይ በፈጸምን ነበር:: ይህ ሁሉ ችላ ተብሎአል፤ ምክንያቱም አንድ ላይ የምንሠራ ከሆነ ሌላው ሰው እኛን ተመሳሳይ ተደራቢ ነገሮችን ያምናሉ ብሎ ይጠረጥራል ብለን ስለምናምን ነው::

በተጨማሪም ድርጅቶች (እንደ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ እምነቶች ያሉት) ከቶ አንድ ሊሆኑ አይችሉም፤ አንድም አንዱ በሌላው ይዋጣል፤ ወይም በተቀናጀ ሀብት አንድ አዲስ ድርጅት ለመፍጠር ሁለቱም የጋራ ማንነታቸውን ያጣሉ:: ድርጅቶች የተመሠረቱት በመሥራች ሰዎች ማንነት ላይ ሲሆን በድርጅቱ ውስጥ ሥልጣን ባላቸው ሰዎች አማካይነት ይቀጥላሉ:: ስለዚህ ቤተ እምነቶች ወደ አንድ የጋራ አካል ይቀላቀሉ ዘንድ መሥራች የሆነው ማንነት መቅረት አለበት:: በአዲሱ ድርጅት እንዳይተኩ በተገባ ተስፋ አማካይነት የሥልጣን ሹመት መቅረት አለበት:: አለመታደል ሆነና ይህ የሚሆን ነገር አይደለም:: ምክንያቱም ባጠቃላይ ሲታይ ኢየሱስ የራሱን ቤተ ክረስቲያን መምራት ይችላል ብለን ባጠቃላይ ሲታይ አናምንም:: የእኛ አጋዥነት ያስፈልገዋል እኮ! በልዩ ልዩ የመንግሥት ጉጥ ውስጥ

አንዳንድ ዕውቅ ሰዎች ኀላፊነትን ቢይዙ የላቀ ሥራ ሊሠራ እኮ ይችላል!

በዚህ ሁኔታ በእነዚህ አሳፋሪና አመንማኝ ቤተ እምነታዊ ክፍፍሎች ተጠምደን እንገኛለን:: የኢየሱስ ጸሎት አልተመለሰም ማለት ነውን? ቤተ ክርስቲያን በእርግጥ አንድ አይደለችምን? «ቤተ ክርስቲያን» ስንል ቤተ እምነቶች ማለት ከሆነ ጸሎቱ አልተመለሰም፤ የኢየሱስ ጸሎት ሊመለስም አይችልም ነበር:: ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን ምንነት «መንግሥት» በሚለውና መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው አገላለጽ የምንጠቀም ከሆነ ጸሎቱ በእርግጥ ተመልሶአል:: በየትኛውም ወገን የሚገኙት እውነተኛ ክርስቲያኖች በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት ናቸው:: ቤተ እምነቶች በቅን ሐሳብ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማደራጀትና ለማቀናጀት ጥረት ቢያደርጉም ሰዋዊ ጥረታችን ፍሬ ቢስ ሆኖ ተገኝቶአል:: እንዲህ ሲባል ግን የተደራጁ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ ፍሬ አልባ ናቸው ወይም መተው (መቅረት) አለባቸው ማለት አይደለም:: ይህም ወሎ አድሮ ወደ አዲስ ቤተ እምነቶች ይመራል! ሆኖም ይህን ማለት ነው:- (1) ክርስቲያኖች በግልና (ተቀጥረው በሚሠሩበት ድርጅት፣ በጉርብትና፣ በትምህርት ቤት) በሕዝባዊ መድረኮች ውስጥ (በትእይንቶች፣ በልዩ ልዩ ጽሑፎች በኩሩሴድስ) እርስ በርስ መቀባበልና በአንድነት መሥራት ያስፈልጋቸዋል:: ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ለመዋጋት የምንነሣሣው እውነተኛውን ጠላት ማየት ሳንችል ስንቀር ብቻ ነው:: (2) ለእግዚአብሔር ቃልና ለትክክለኛ አስተምህሮ ያለንን መሰጠት ሳናጣ ለድኅነት እጅግ አስፈላጊ የሆነው አስተምህሮ የቱ እንደ ሆነና እንዳልሆነ ግልጽ እንዲሆንልን ያስፈልጋል:: በእነርሱ የተነሣ ሳንለያይ (ሮሜ 14÷1-8) ስለ ያዝነው ልዩ ልዩ ሐሳብ ለመወያየት መማር አለብን:: (3) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን የእነርሱ ገንዘብ እንዳልሆነችና መግዛት



(በቤተ ክርስቲያን ላይ ባለሥልጣን መሆን) እንደሌለባቸው ይነገራቸው ዘንድ ይገባል::

የቤተ ክርስቲያን አንድነት ለኢየሱስ እጅግ አስፈላጊ ነበር:: አንድነት ለፍሬያማ ተልእኮና ቸርነት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ከዚህ ቀደም አይተናል:: ኢየሱስ ስለ አንድነት ሦስት ተጨማሪ ምክንያቶችን ይሰጣል፤ (1) ክብር - አንድነት የተመሠረተው ለኢየሱስ አካል በተሰጠው ክብር ላይ ነው (ቍ. 22):: በኢየሱስ ክብር አማካየነት እርስ በርሳችን አንድ መሆናችን ብቻ ሳይሆን፣ የመለኮት ባሕርይ ተካፋዮችም እንሆናለን (2ቆሮ 3÷18፤ ዕብ 12÷10፤ 1ዮሐ 3÷2፤ 2ጴጥ 1÷4):: ስለዚህ መለያየቶች የሚከሰቱት ኢየሱስን በትክክል ማየት ሲሳነን ነው ተብሎ ሐሳብ ሊሰነዘር ይቻላል:: በተጨማሪም አንድነታችን ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጣል:: ዓለም የተከፋፈለ አካልን ሲያይ ዕብድ ነው በማለት ራስ በሆነው ላይ ያላግጣሉ:: (2) ይቅርታ - የቤተ ክርስቲያን አንድነት ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑን ለዓለም እንደሚያረጋግጥ ጌታ ኢየሱስ ተናግሮአል (ቍ. 23፤ ከዮሐ 3÷17:34፤ 5÷36-37፤ 8÷18:27-:29፤ 9÷7):: (3) ፍቅር - አንድ በሆነች ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚወድ ዓለም ያስተውላል (ቍ. 23):: ለክርስቶስ ሲባልና ለአብ ክብር ሲባል ቤተ ክርስቲያን አንድ መሆን አለባት::

ዮሐ 17÷24-26

24«አባት ሆይ፤ እነዚህ የሰጠኸኝ እኔ ባለሁበት
እንዲሆኑ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝንም
ክብሬን እንዲያዩ እፈልጋለሁ::
25«ጻድቅ አባት ሆይ፤ ዓለም ባያውቅህም፣ እኔ ዐውቅሃለሁ፤ እነዚህም
አንተ እንደ ላከኸኝ ያውቃሉ:: 26ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነርሱ እንዲሆን እኔም በእነርሱ
እንድሆን አንተን እንዲያውቁ አደርጌአለሁ፤ እንዲያውቁህም አደርጋለሁ::

[a]26 በግሪኩ ስምህን እንዲያውቁ ደባል

ይህ ተወዳጅ መደምደሚያ የጸሎቱን ዐበይት ሐሳቦች አካቶ ይዟል፡- የእግዚአብሔር ክብርና መገለጥ፣ ወደ ሐዋርያት ያስተላለፈው እግዚአብሔር ለኢየሱስ ያለው ፍቅር፣ የኢየሱስ ወደ አባቱ መመለስ::

**§ 152**
**ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ያደረገው ጸሎት**
**(ማቴ 26÷30[57] :36-40፤ ማር 14÷26:32-42፤ ሉቃ 22÷39-46፤ ዮሐ 18÷1)**

ይህ የኢየሱስ ወሳኝ ሰዓት ነው:: እዚህ ላይ የመጨረሻ ውሳኔውን ያደርጋል:: ወደ መስቀል ይሄዳል ወይስ አይሄድም? ምን እንደሚያደርግ እናውቃለን፤ ምንጊዜም አባቱን ይታዘዛል:: ይህ ግን ጉዳዩን ቅንጣት ያህል ቀላል አያደርገውም:: በምድረ በዳ ከከፋው ጋር በብርቱ ከታገለበት ጊዜ ጀምሮ ጉዳዩ ቀላል አልነበረም:: ቢሆንም ከዚያ ወቅት አንስቶ ብቻውን አይደለም::[58] በምድረ በዳ እንደ ሆነው ሁሉ በብርቱ ሥቃይ ውስጥ ሳለ ያገለግለው ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሰስ መልአኩን ላከለት (ሉቃ 27÷43):: ኢየሱስ በምድረ በዳ እንዳደረገው ተልእኮውን ለመፈጸም ይወስናል:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወደፊት ማወላወል አይኖርም፤ ጥያቄዎች አይኖሩም፤ ወደ ኋላ መመለስ አይኖርም::

[57] ስለ ጴጥሮስ ክሕደት ሁለት ትንቢቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ በድጋሚ እናስታውስ ዘንድ ይህ ሆኖአል:: ሉቃስና ዮሐንስ በላይኛው ክፍል የተነገረውን የመጀመሪያ ትንቢት ጽፈዋል:: ማቴዎስና ማርቆስ ደግሞ ወደ ጌቴሴማኒ በሚወስደው መንገድ ላይ የተነገረውን ሁለተኛ ትንቢት ጽፈዋል:: ሆኖም አራቱን ወንጌላውያን ክፍል 147 ውስጥ አንድ ላይ አስቀምጠናል:: ስለዚህ በማቴዎስና በማርቆስ መካከል እዚህ ላይ የ5 ቍጥሮች ክፍተት አለ::

[58] R.S. Barbour, "Gethesemane in the Tradition of the Passion," *NTS* 16 (1969-70): 231-251, በሚለው ላይ ለኢየሱስ የጌቴሴማኒ ተመክሮው እንደ ምድረ በዳው ተመክሮው ነበር በማለት በሚያሳምን ሁኔታ ይከራከራል::



³⁰(ይህን ካለ በኋላ[ማር]) መዝሙር ከዘመሩ በኋላ (የቄድሮንን ሸለቆ ተሻገረ[ዮሐ]) (እንደ ልማዱ[ሉቃ]) ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ወጡ::

***ማቴ 26÷30 ከዮሐ 18÷1 ከሉቃ 22÷39 ጋር***

³⁶ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ (የአትክልት ስፍራ[ዮሐ]) ሄደ:: እነርሱንም[ማ]፣ «ወደዚያ ሄጄ በምጸልይበት ጊዜ እናንተ እዚህ ተቀመጡ» («ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ[ሉቃ]») አላቸው:: ³⁷ከእርሱም[ማ] ጋር ጴጥሮስንና ሁለቱን የዘብዴዎስ ልጆች (ያዕቆብንና ዮሐንስንም[ማር]) ይዞ በመሄድ ይተክዝና ይጨነቅ ጀመር፤ ³⁸ከዚያም፣ «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዝናለች፤ ከእኔ ጋር በመትጋት እዚህ ቆዩ» አላቸው::

***ማቴ 26÷36-38 ከዮሐ 18÷1 ከሉቃ 22÷40 ከማር 14÷33 ጋር***

ከኢየሱስ «ሊቀ ክህነታዊ» ጸሎትና ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ከሀሊሉያ (ከሀላል) መዝሙር ጋር (መዝ 136 ወይም ከሦስተኛ ጽዋ በኋላ መዝ 115-118 ሳይሆን አይቀርም) የፋሲካ ምግብ ይደመደማል:: የኢየሱስ ቡድኖች በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ወደ ኢየሩሳሌም ጎዳናዎች አቀኑ:: ይሁን እንጂ በከተማው ውስጥ ብዙ የሚከናወን ነገር ነበር:: ብዙ ጌቶች ለምግቡ የሚሆኑትን ግብአቶች ያመጡ ዘንድ መልእክተኞችን ላኩ:: ብዙዎቹ ደግሞ ለድኾች ስጦታ ለመስጠት ወጡ:: አንዳንዶችም በሚቀጥለው ቅዱስ ቀን ለሚቀርበው አያሌ መሥዋዕት ለመዘጋጀት በእኩለ ሌሊት ዳግም ወደ ተከፈተው ቤተ መቅደስ ሄዱ:: ኢየሱስ በምሥራቁ የቤተ መቅደስ መግቢያ በኩል ደቀ መዛሙርቱን እየመራ በመውጣት ላይ ነው:: የቄድሮንን ሸለቆም ተሻገሩ::[59] የደብረ ዘይት ተራራን በመውጣት ላይ ሳሉ ዙሪያውን

[59] Brown (vol 1, p. 125) ከዚህ ላይ በኢየሱስና በዳዊት መካከል ያለውን ብርቱ ትስስር ያመለክታል፤ (1) ዳዊት ኢየሩሳሌምን ለቅቆ ሄደ (2ሳሙ 15÷16)፤ የቄድሮንን ሸለቆ ተሻግሮም በደብረ ዘይት ተራራ አለቀሰ (2ሳሙ

ወደታጠረ የጌቴሴማኒ ጫካ (ትርጕሙ የወይን መጭመቂያ ቦታ ማለት ነው) ወደ ተባለ ስፍራ መጡ:: ኢየሱስ አዘውትሮ እንዲመላለስበት የተፈቀደለት ገለልተኛ የሆነ የወይራ ዛፍ ስፍራ ነበር::

አትክልቱ ስፍራ መግቢያ ላይ[60] ስምንቱን ሐዋያት ተዋቸው:: ወደ ፈተና እንዳይገቡ ይጸልዩ ዘንድ ነገራቸው (ሉቃ 22÷40):: ከዚያም እርሱና ሦስቱ የቅርብ ወዳጆቹ (ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ) ወደ ውስጠኛው ጫካ ሄዱ:: ኢየሱስ ከቅርብ ወዳጆቹ ጋር ሆኖ በመምጣት ላይ ያለውን ሕማማቱን ልብ በማለት ሐዘን ገብቶታል:: በማቴዎስና በማርቆስ መካከል የኢየሱስን የውስጥ ሥቃይ[61] የተገለጸባቸው ሦስት የተለዩ ቃላት አሉ:: ሐዘኑ እጅግ ብርቱ በመሆኑ እሞታሁ ብሎ ዐሰበ:: የኢየሱስ ሥቃይ የሚጀምረው በጎልጎታ ሳይሆን በጌቴሴማኒ ነው:: ከሁለት ቀን ቀደም ብሎ ኢየሱስ እጅግ ከባድ ሐዘን እንደገባው ተናገረ (ዮሐ 12÷27-36):: ሆኖም ከዓለም ኀጢአት የተነሣ የበደል ሸክሙና አይቀሬ የሆነው የአባቱ መለየት (2ቆሮ 5÷21) የቱን ያህል ከባድ

---

15÷23:30):: (2) የቅርብ ወዳጁ የነበረው አኪጦፌል ከዳው፤ እርሱም ኋላ ጊዜ ራሱን የሰቀለ ሲሆን (2ሳሙ 17÷23)፣ ከአስቆሮቱ ይሁዳ ሌላ ይህን ድርጊት የፈጸመ ብቸኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገጸ ባሕርይ ነው:: የወይራ ዘይት ጥልቅ ትእምርታዊ ትርጕም ያለው መሆኑም መገለጽ አለበት:: ከዚህ ያላነሰው ደግሞ መሲሓዊው ጦርነት ነው (ዘካ 14):: እዚህ ላይ የሚገኙት ሁኔታዎች ላይ ላዩን ሲታዩ ከሚሰጡት እሳቤ ይልቅ ላቅ ያለ ሐሳብ አላቸው::

60 ከሐዋርያት ሌላ ከኢየሱስ ጋር ጥቂት ደቀ መዛሙርት ነበሩ:: M.L. Soards, "On Understarding Luke 22:39," *BT* 36 (1985): 336-337 ላይ ባመለከተው መሠረት፣ ሉቃስ «ደቀ መዛሙርት» ሲል (23÷39)፣ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የለያቸው ይመስላል:: ይህ መደምደሚያም በአትክልት ስፍራ የነበረውን በስም ያልተመለከተውን ደቀ መዝሙር ማርቆስ መጥቀሱ የተረጋገጠ ይመስላል (ማር 14÷51-52)::

61 *ላይፒኦ* - *Lypeo* «ማዘን» ማለት ነው:: *አደሞኔኦ* - *Ademoneo* ገብቶ የሚገኘ ው ከዚህ ላይና በፊል 2÷26 ላይ ነው:: ነፍስን መከራ ስለሚያበላ ሥቃይ ?ናገራል:: *ኤክታምቢኦ* - *ekthambeo* ማለት «ወደ አስገራሚ ሁኔታ ወይም ?ደ ሽብር መወርወር» ማለት ነው:: ምናልባት እነዚህን ቃሎች በመዝ 42÷5-6 ወይም 43÷5 ላይ ያለውን ቋንቋ እንዲያንጸባርቁ ታስበው ይሆናል::



መሆኑን የተገነዘበው ከዚህ ላይ ነው:: እነዚህ እንግዳ ስሜቶች ናቸው:: ከዘላለም አንሥቶ ኢየሱስ የበደልም ሆነ የመተው ስሜት ተሰምቶት አያውቅም:: ሦስቱ የቅርብ ወዳጆቹ ነቅተው እንዲጠብቁ ነገራቸው:: ጠላት ሲመጣ ኢየሱስን የሚያስጠነቅቁት ወታደራዊ ዘቦች አይደሉም (ኤፌ 6÷17-18):: ራሳቸውን በመጠበቅና በመንፈሳዊ ውጊያ ላይ ከኢየሱስ ጋር በመተባበር መጠበቅ ነበረባቸው (ሉቃ 22÷40፤ ማቴ 26÷40-41)::

**ማር 14÷35-36**
**ከሉቃ 22÷41፤**
**ከማቴ 26÷39 ጋር**

[35]ጥቂት እልፍ ብሎም (ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ ያህል ርቆ[ሉቃ]) (ተንበርክኮ[ሉቃ]) (በግንባሩ በመደፋት[ማቴ]) በምድር ላይ በመውደቅ ቢቻል ሰዓቱ ከእርሱ እንዲያልፍ ጸለየና፣ [36]አባ[ሪ]፤ አባት ሆይ፤ ሁሉ ነገር ይቻልሃልና ይህን ጽዋ ከእኔ አርቀው፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን» አለ::

*[ሪ]36 በአራማይ ቋንቋ አባት የሚጠራበት ነው::*

**ሉቃ 22÷43-44**

[43]መልአክም ከሰማይ ተገልጦለት አበረታታው:: [44]እጅግ ተጨንቆም በብርቱ ይጸልይ ነበር፤ ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር[ሙ] ይፈስ ነበር::

*[ሙ]44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ቍጥር 43 እና 44 የላቸውም::*

ኢየሱስ ይጸልዩ ዘንድ የሚቀርቡትን ሦስት ሐዋርያት ካሳሰበ በኋላ፣ «የድንጋይ ውርወራ ያህል ርቆ» ሄደ:: ያ ምን ያህል እንደሚርቅ የሚወሰነው እንደ ድንጋዩ መጠንና እንደ ወርዋሪው ጡንቻ ነው:: በጆሮ ሊሰማ ከሚችለው ርቆ ግን ከዐይን ያልራቀ መሆኑ ግልጽ ነው:: በፋሲካ ሙሉ ጨረቃ ወጥታ ሳለ በዚያ ቦታ ኢየሱስ በጕልበቱ ተንበርክኮ (ሉቃ)፣ ከዚያም በግንባሩ ተደፋ (ማቴዎስ):: በሥቃዩ

ውስጥ እያለ አባቱን በፍቅር ጠራው:: «አባት» የሚለው ቃል አይሁድ ቅርርብን በእጅጉ ያመለክታል ብለው የሚያስቡትና እግዚአብሔርን ለመጥራት የማይደፍሩበት ቃል ሲሆን፣ የፍቅር መግለጫ አራማይካዊ ቃል ነው:: ከዚያም አራት ቃሎችን ስሳየ፤ «ይህን ጽዋ ከእኔ አርቀው» በደንብ አስተውሉ! ኢየሱስ ይህን የሥቃይ ጽዋ ባይጠጣ ኖሮ የዘላለም ዕጣ ፈንታችን በአደገኛ ሚዛን ላይ እንደ ተንጠለጠለ ይቀር ነበር:: ደግሞም ኢየሱስ፣ «ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን» በሚለው ቃል ጸሎቱን ባይጨርስ ኖሮ፣ እኛ የቱን ያህል አሳዛኝ ዕድል ባጋጠመን ነበር:: ኢየሱስ ሞት የሚገባው አልነበረም፤ በሞት ይቀጣ ዘንድ የሚያስገድድ ግብረገባዊ ግዴታ አልነበረበትም:: ከዚህም በላይ ይሞት ዘንድ የሚያስገድደው ምድራዊ ኀይል አልነበረም (ዮሐ 10÷18):: የሚሞተው በራሱ ምርጫ ነው::

ኢየሱስ ስቅለት እንዲደቀርለት ለምን ለመነ፧ ይህ ፊታቸውን ሳያጨማድዱ በጽናት ወደመገደያቸው ስፍራ ከሚራመዱት ሰማዕታት ያነሰ ደካማ ሰው አያደርገውምን፧ ይህ ጥያቄ አንዳንዳችን ኢየሱስ ይናገር የነበረው ጽዋ ስለ መሰቀል ሳይሆን በጌቴሴማኒ ጊዜው ሳይደርስ ሊጸም ስለሚችለው ሞት ነበር:: እንደሚታወቀው፣ «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዝናለች» ያለ ሰው ነው (ማቴ 26÷38):: ከዚህም በላይ ሥቃዩ የደም ላብ አስከትሎበታል (ሉቃ 22÷44)፤ ይህም ከሞት ሊያደርስ የሚችል ነበር:: ስለዚህ እግዚአብሔር ለዐሥራ አምስት ሰዓታት ወይም ለዚህን ያህል ጊዜ ሕይወቱን እንዲያቆዩለት ጸለየ የሚል ሐሳብ ቀርቦአል::[62]

[62] H.R. Cowles, "'This cup': What Did Jesus Mean," *AL* 128 (Apr 1993:6ff., በሚለው ላይ ሁለተኛ ሐሳብ ይሰነዝራል:: ኢየሱስ የጠየቀው በሞት ብቻውን እንዳይተው ሳይሆን፣ ከሞት እንዲነሣ ነው በማለት ይከራከራል:: እነዚህ ሁለቱም መፍትሄዎች «ተርበትብቶ» ከመስቀል እንዲገላገል አለመጠየቁን ያመለክታሉ:: ይሁን እንጂ ለሁለተኛው አጋማሽ ጸሎት፣



ከዚህ የተሻለ ገለጻ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የአመክንዮ መሥመር የሚከተል ይመስላል:- በመጀመሪያ ነገር ሞት እንዳይደርስ መፈለግ ወይም ሌላ መውጫ መንገድ መሻት ፈሪነት አይደለም:: ደፋርነት ወይም ጀግንነት የሚለካው በአንድ ሰው ውስጣዊ ስሜት ሳይሆን፣ በሰውየው ተግባር (ድርጊት) ነው:: ሁለተኛ የኢየሱስን ሞት ከሰማዕትነት ጋር ማነጻጸር ተገቢ አይደለም:: ሰማዕታት የሚሞቱት ለውሱን ዐላማ ነው፤ ኢየሱስ የሞተው ግን ለዓለም ኀጢአት ነው:: በመስቀል ላይ እያለ ኀጢአት ሆነ (2ቆሮ 5÷21)፤ በራሱ አካልም የዓለምን ኀጢአት ተሸከመ (1ጴጥ 2÷24):: ኢየሱስን ያስጨነቀው የሰማዕትነት አካላዊ ሥቃይ ሳይሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰውን ዘር በደል በመቅመሱና ከአብ መለየትን በመቀበሉ ሰው የሆነው አምላክ የደረሰበት መንፈሳዊ ሥቃይ ነበር:: ኢየሱስ ይህን ይፈጽም ዘንድ የቱን ያህል ዝቅ እንዳለ የምንረዳበት መንገድ የለም:: ከዚህም የተነሣ መንፈሳዊ ሥቃዩ የቱን ያህል እንደ ነበር የመመዘን ዐቅም የለንም:: ካርሰን (ገጽ 543)፣ እንዲህ ይላል፤ «ምንባቡ መታየት ያለበት ከማቴ 1÷21 እና 20÷28 አኳያ ነው:: የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የኢየሱስን

«ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን» ለሚለው አጥጋቢ ገለጻ የላቸውም፤ አንዳቸውም ቢሆኑ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የተሠቃየውን ሥቃይ በሚገባ አላጤኑትም:: ሦስተኛው ገለጻ የሚከተለው ነው፤ በብሉይ ኪዳን «ጽዋ» የእግዚአብሔርን ቊጣ የሚያመለክት ዘይቤ ነው፤ ስለዚህ ኢየሱስ የሚጸልየው በግሉ በእርሱ ላይ እግዚአብሔር ያሳረፈበትን ቊጣ እንዲያነሣለት ነው (C.E.B. Cranfield, "The Cup Metaphor in Mark 14:36 and Parallels," *ExPT* 59 [1947-48]: 137-138). C.A. Blaising, "Gethsemane: A Prayer of Faith," *JETS* 22 (1979): 333-343 በሚለው ላይ እነዚህን ሁለት አተያየቶች በማቀናጀት ኢየሱስ ጽዋውን ያስወግድለት ዘንድ አብን በጠየቀ ጊዜ መስቀል እንዳያጋጥመው እየተከላከለ አልነበረም፤ የእግዚአብሔር የቊጣ ጽዋ በእርሱ ላይ እንዳረፈበት ሳይቀር፣ እግዚአብሔር ከሞት እንዲያስነሣው ይለምን ነበር እንጂ:: ነገር ግን ይህ እንዳለ ሆኖ የጽዋ ዘይቤ፣ «የእኔ ድርሻ» የሚለውንም ያመለክታል:: ደግሞም ማርቆስ 10÷39 ውስጥ ኢየሱስ ዕጣ ፈንታው የሥቃይና የሰማዕትነት መሆኑን ለመግለጽ ይህን የጽዋ ዘይቤ ይጠቀማል:: እንዲሁም ዮሐ 18÷11 ውስጥ ይህንኑ ዘይቤ ይጠቀምበታል:: ስለዚህ ከዚህ ላይ የምንይዘው ግንዛቤ ይህንኑ ነው::

ልዩና ቤዛዊ ሞት በእጅጉ መግለጻቸው ተገቢ ነው (ሮሜ 3÷21-26፤ 4÷25፤ 5÷6:9፤ 1ቆሮ 1÷23፤ 2ቆሮ 5÷21፤ ዕብ 2÷18፤ 4÷15፤ 5÷7-9፤ 1ጴጥ 2÷24)::» ከዚህም በላይ «ጽዋው» እንዲሁ ተራ ሥቃይ አልነበረም:: የእግዚአብሔርን ቊጣ የሚያመለክት የተለመደ ብሉይ ኪዳናዊ ትእምርት (ምልክት) ነበር (መዝ 75÷8፤ ኢሳ 51÷22፤ ኤር 25÷15-16፤ ሰቆ 4÷21፤ ዕን 2÷16):: ኢየሱስ ወደ ማቴዎስ 20÷22-23 ዘወር ብሎ በመመልከት ላይ አልነበረም፤ እግዚአብሔር በኀጢአት ላይ ያለው ቊጣ በእርሱ ላይ በኀይል ወደሚያርፍበት ወደ ማቴዎስ 27÷46 ወደፊት ይመለከት ነበር እንጂ:: በመጨረሻም ኢየሱስ በሕማማት ውስጥ እንደ ታጋሽ መንፈሳዊ ሰው ቢኖዝ ኖሮ አዳማዊ ድካማችንን ይረዳል የሚለው ተስፋችን መንማና በሆነ ነበር:: ወደ መለኮታዊ ባሕርዩው የሚስበን እንደ እኛ ሰው የመሆኑ እውነታ በመሆኑ ይህ ሌላ ሳይሆን አይአወ (የማይሆን የሚመስል ነገር) ነው:: የዕብራውያን ጸሐፊ የዚህ ጸሎት ሽክም የቱን ያህል ውጤታማ እንደ ሆነ ለማሳየት ወደ ኢየሱስ ያመለክታል (ዕብ 5÷7)::[63]

ሁለተኛው ጥያቄ የሚነሣው ከኢየሱስ ጸሎት ላይ ነው:- «ሌላ መንገድ ነበርን?» ኢየሱስ ማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የሚገኝን ቅድመ ሁኔታዊ ቃልን ይጠቀማል፤ «ቢቻል ...» ይህ ሌላው ቢቀር በኢየሱስ ሐሳብ (አእምሮ) እውናዊ የሆነ አማራጭ ያለ መሆኑን ይናገራል (ከማቴ 26÷42 ጋር መነጻጸር ያለበት ቢሆንም እንኳ):: ማርቆስ ወንጌል ውስጥ እንዲያውም ይበልጥ ብርቱ ነው «ሁሉ ነገር ይቻልሃልና::» በትወራ (ትረካ) ደረጃ ሲታይ፣ ያለ ምትክ ሞት የሰው ዘር የሚድንበት ሌላ መንገድ ይኖር ይሆናል:: ይህ ግን እንዲሁ ግምት ነው:: የእግዚአብሔር ሉዐላዊ ፈቃድ የገዛ ልጁ ለዓለም ኀጢአት እንደሚሞት

---

[63] R.E. Brown (1:229-233) ዕብ 5÷7 እና ዮሐንስ 17 እንዲሁም የጌቴሴማኒ ጸሎት የቱን ያህል እንደሚመሳሰል ያመለክታል:: እንዲህ ያለው አዝልቆት ደግሞ ታሪካዊነትን በእርግጥ ያመለክታል::



ወስኖአል:: እውነቱ ሲታይ ሌላ አማራጭ አልነበረም:: ውጤቱ የቱንም ያህል ዘግናኝ ወይም ሥቃይ ያለበት ቢሆን ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ቈርጦ ተነሥቶ ነበር::

መልአኩን ወይም የኢየሱስን አካላዊ ሁኔታ (የደም ላብ) ማውሳት የሉቃስ የተለመደ ባሕርይ ቢሆንም፣ የሉቃስ 22÷43-44 ምንባብ አሳማኝ የሆነ ጽሑፋዊ ድጋፍ የለውም:: በሌላ አባባል በጥንት ቅጆች ውስጥ አይገኝም:: ይህ መረጃ እንዲሁ ከሚቀር ተብሎ በኋላ የተጨመረ ቢሆንም፣ በሉቃስ ሳይጻፍ አሳማኝ ትውፊትን መሠረት በማድረግ በኋላ የታከለ (የተጨመረ) ነው ብለን እንደመድማለን::[64] ስለዚህ እውነት ነው ብለን እንቀበላለን፤ ነገር ግን የመጀመሪያው ቅጅ አካል አድርገን አይደለም:: ኢየሱስ ሲሰቃይ ሳለ መልአክ መጥቶ እንዳገለገለው ተገልጿል:: ከሦስት ዓመት በፊት በምድረ በዳ ከተፈተነ ወዲህ ይህ የመጀመሪያ ነው (ማር 4÷11):: ከሥቃዩ የተነሣ «ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ» በማለት ሉቃስ የገለጸው መከራ በኢየሱስ ላይ ደረሰበት:: የዚህ ሕክምናዊ ገለጻ ደም ማውጣት ነው:: ከጭንቀት የተነሣ[65] የግንባር የደም ሥሮች የሚፈነዱበት ሁኔታ ይኖራል:: በርግጥም ይህ የኢየሱስን ሁኔታ በትክክል ይገልጻል::

---

[64] B.D. Ehrman and M.A. Plunkett, "The Angel and the Agony: The Textual Problem of Luke 22:43-44," *CBQ* 45 (1983): 401-416 በሚለው ላይ ይህን የጽሑፍ ልዩነት በዝርዝር ይተነትናሉ:: ከዚህ ድምዳሜም ላይ ደርሰዋል:- «በግምት ከ200-300 ዓመት የተተወ ነገር እንዳለና ከ160 ዓ.ም. በፊት ደግሞ ጣልቃ ገብነት» መኖሩን (ገጽ 403) ያመለክታሉ:: ጣልቃ ገብነት ስለ መሆኑ ይስማማሉ፤ ይሁን እንጂ እጅግ ቀደም ብሎ መሆኑን ያመለክታሉ:: ይህም ታሪካዊ ተቀባይነቱን ከፍ ያደርገዋል:: T. Baarda, "Luke 22:42-47a: The Emperor Julian as Witness to the Text of Luke," *NovT* 30/4 (1998): 289-296 በሚለው ጽሑፍ ላይ የንጉሥ ዮልያንን «የከሐዲው ተቃውሞ»ና (በግምት 331-63) የቴዎዶር ምፕሱዌስቲያን ምላሽ (በግምት 350-428) ይዘረዝራል:: ክርክራቸው ምንም ይሁን ምን፣ ይህ ምንባብ በሰፊው ተቀባይነት ስለ ማግኘቱ እነርሱ የመጀመሪያ ምስክሮች ሆነዋል::

[65] ከ W.D. Edwards, W.J. Gabel, & F.E. Hosmer, "On the Physical Death of Jesus Christ," *JAMA* 255/11 (March 21,1986): 1455-1463 ጋር ያነጻጽሩ::

ማቴ 26÷40-46
ከሉቃ 22÷45-46፤
ከማር 14÷40-41
ጋር

40ከዚያም (ከጸሎትም ተነሥቶ[ሉቃ]) ተመልሶ
ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሲመጣ (ከሐዘን የተነሣ[ሉቃ])
ተኝተው አገኛቸው፤ («ስለምን ትተኛላችሁ?»[ሉቃ])፤
ጴጥሮስንም እንዲህ አለው፤ «እናንተ ሰዎች፤ ከእኔ ጋር
ለአንድ ሰዓት እንኳ መትጋት አቃታችሁን? 41ወደ ፈተና
እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ:: መንፈስ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን
ደካማ ነው::»

42እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ሄደ፤ «አባት ሆይ፤ ይህ ሳልጠጣው የማያልፍ ጽዋ
ከሆነ ፈቃድህ ይፈጸም» ብሎ ጸለየ::

43እንደገናም በመጣ ጊዜ ዐይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ስለ ነበር
ተኝተው አገኛቸው:: (የሚመልሱትንም አያውቁም ነበር[ማር])::

44ትቶአቸውም እንደገና በመሄድ ለሦስተኛ ጊዜ ቀድሞ ብሎ የጸለየውን
ጸሎት ደገመ::

45ከዚያም (ሦስተኛ ጊዜ[ማር]) ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ እንዲህ
አላቸው፤ «አሁንም ዐርፋችሁ ተኝታችኋል? (ይበቃል![ማር]) እነሆ፣ ሰዓቱ ቀርቦአል፤
የሰው ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ዐልፎ ይሰጣል፤ 46ተነሡ! እንሂድ፤ አሳልፎ
የሚሰጠኝም እየመጣ ነው::»

ሦስት ጊዜ ሙሉ ኢየሱስ፣ «አባቴ ሆይ፤ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ» በማት ጸለየ:: ሦስት ጊዜ ሙሉ እግዚአብሔር «አይሆንም» በማለት መለሰ:: በዚህ ሰዓት እግዚአብሔር መልአክ ሊልክለት ይችል ነበር፤ የትንሣኤን ተስፋ ሊሰጠውም ይችል ነበር፤ ወደ ሰማያዊው ዙፋን መልሶ ሊያመጣውም ይችል ነበር:: ይሁን እንጂ ከዚህ ሁኔታ ኢየሱስን መገላገል ፈቃዱ አልነበረም:: እግዚአብሔር ለጥያቄአችን «አይሆም» የሚል መልስ ስለ ሰጠ ጸሎታችንም ሆነ እምነታችን ደካማ ነው ማለት አይደለም:: ይህ ምንባብ በቀጥታ ስለ



ጸሎት ባይሆም እንኳ፣ ብዙ እንማርበታለን::[66] እንደ ኢየሱስ እንጸልይ ዘንድ ተጠርተናል፤ ይሁን እንጂ እንደ ጴጥሮስ በመጸለይ እንደመድማለን::

ኢየሱስ ሦስት ጊዜ የቅርቡ ወደ ሆኑት ሦስቱ ተመላለሰ፤ ሦስት ጊዜም ተኝተው አገኛቸው:: ጴጥሮስን ለይቶም «ከእኔ ጋር ለአንድ ሰዓት እንኳ መትጋት አቃታችሁን?» በማለት ጠየቀው (አንድ ሰዓት በትክክል ሥልሳ ደቂቃ ባይሆም፣ የኢየሱስ የመጀመሪያው ጸሎት ምን ያህል ሰዓት እንደ ወሰደ ይነግረናል):: ጴጥሮስን ለይቶ የተናገረበት ምክንያት ከጥቂት ሰዓታት በፊት ከእርሱ ጋር እንደሚሞት ጉራ በመንዛቱ ሳይሆን አይቀርም:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደግሞ ሰይፉን መዞ በማልኮስ ላይ ያሳርፋል:: መደምደሚያው በዐይን በሚታይ ሰይፍ ለኢየሱስ ለመዋጋት ፈቃደኛ መሆኑ ነው:: በመንፈሳዊ የጦር ሰይፍ ለመዋጋት ግን በእንቅልፍ ተጠምዶ ነበር::

የቱንም ያህል ጥረት ቢያደርጉ ነቅተው ለመጠባበቅ አልቻሉም! በሐዘን ተዳክመዋል:: ታላቅ የውስጣዊ ስሜት ተራራና ሸለቆ የበዛበት ሳምንት ነበር:: እሑድ ዕለት ሆሣዕና፣ ሰኞ ቤተ መቅደሱ የነጻበት ዕለት ነበር:: ማክሰኞ ከእስራኤል ታላላቅ አለቆች ጋር ውይይትና ክርክር የተደረገበት ታላቅ ቀን ነበር:: በእያንዳንዱም ምሽት አያሌ ምዕራፎችን በመንዝ፣ ይኖሩበት ወደ ነበረው ወደ ቢታንያ ይመለሳሉ፤ ረቡዕና ሐሙስ ያለፉት ለፋሲካ በዓል በመዘጋጀት ነበር:: ኢየሱስ

66 ስለ ጸሎት ከዚህ ምንባብ ውስጥ የምንማራቸው አንዳንድ ትምህርቶች የሚከተሉት ናቸው:- (1) የኅብረት ጸሎት ኀይል አለው፤ ኢየሱስ እንኳ ለእርሱ የቅርብ የሆኑት ሦስቱ ከእርሱ ጋር ወይም ለእርሱ እንዲጸልዩ ጠራቸው (ማቴ 26÷38:40):: (2) እግዚአብሔር ለጸሎትህ መልስ ባይሰጥ የእምነት ሰው አይደለህም ማለት አይደለም:: እንዲያውም በዚህ ጊዜ አንተ በእግዚአብሔር ፈቃድ ማእከል ውስጥ ያለህ መሆንህን ያሳይ ይሆናል፤ እናም ያንቀሳቅስህ ዘንድ አልፈለገም:: (3) ብዙ ጊዜ ለሥጋዊ ፍላጎት ስንል (እንደ እንቅልፍ) ጸሎትን ችላ እንላለን:: መንፈስ ተግባራችንን እንዲመራ ከማድረግ ይልቅ ሥጋችን እንዲመራን ማድረጋችን ስሕተት ነው:: (4) ጸሎት ለፈተና እንዳንሸነፍ የሚያደርገንን ኀይል ይሰጠናል::

«ትቻችሁ እሄዳለሁ»፣ «ትሰደዳላችሁ»፣ «ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል፤ ሁላችሁም በእኔ ተሰናክላችሁ ትሄዳላችሁ» እና የመሳሰሉትን ተናገረ:: በዚህ ሁሉ ጊዜ በክብር መቀመጫና የጴጥሮስንም ፋክራ በማውሳት ይከራከሩ ነበር:: የባሰውን ደግሞ ትክክል የሆነውን ጥያቄ ሳይሆን (ዮሐ 16፥5) ትክክል ያልሆነውን ጥያቄ በመጠየቃቸው ኢየሱስ ገሠጻቸው (ዮሐ 14፥7፡9):: ከጨዋታ ውጭ ሆነዋል:: አሁን ግን ጸሎት በእጅጉ የሚያስፈልጋቸው ወቅት ነው:: ኢየሱስን የመተውን ፈተና ለመቋቋም የሚያስችል ኀይል ያገኙ ዘንድ ጸሎት ያስፈልጋቸዋል:: ኢየሱስ ትክክል ነው:: መንፈሳቸው ፈቃደኛ ነው፤ ሥጋቸው ግን ደካማ ነው:: ቀጥሎ ያለው ትራኬ እንደሚያሳየው ስሕተት የሆነውን ምርጫ መረጡ:: የመንፈሳቸውን አነሣሽነት ከመከተል ይልቅ የሥጋቸውን አነሣሽነት ተከተሉ::

ለሁለተኛ ጊዜ ኢየሱስ ወደ አብ ጸለየ፤ ጥያቄውንም በመጠኑ ለወጠው፤ «ይህ ሳልጠጣው የማያልፍ ከሆነ» አለ፤ ከፊቱ ተደቅኖ ለሚገኘው ተግባር ራሱን አሳልፎ የሰጠ ይመስላል:: አሁንም ሦስቱን ተኝተው አገኛቸው፤ አሁንም የሚሉት አልነበራቸውም፤ ተደርሶባቸዋል፤ ኀፍረትም ገብቶአቸዋል:: ለሦስተኛ ጊዜ ተኝተው ሲያገኛቸው «በቃ!» አለ:: ቃሉ «አንድን ሥራ ከመሥራት ማቆም ወይም መታቀብ» ማለት ነው (ከሐሥ 15፥29 ጋር ያነ):: አንዳንዶች ይህን፣ «ጸሎቴን ጨርሻለሁ፤ ጉዳዬን ፈጽሜያለሁ፤ እንሂድ» በማለት ይተረጉሙታል:: «ብዙ ተኝታችኋል፤ እንሂድ» ማለትም ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ ወደ መስቀሉ ከሚደረገው ጉዞ ቀጥሎ ወዳለው ደረጃ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው:: ኢየሱስ ዝግጅቱን እንደ ጨረሰ ሁሉ ይሁዳም የግሉን ዝግጅት አጠናቆአል:: ሁለቱ ወደ አትክልት ስፍራ መግቢያው ላይ ይገናኛሉ::



**§ 153**
**መካድና መያዝ በጌቴሴማኒ**
**(ማቴ 26፥47-56 ማር 14፥43-52 ሉቃ 22፥47-53 ዮሐ 18፥1-12**

[(ዮሐ 18)1]ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሆኖ የቄድሮንን ሸለቆ ተሻገረ፤ ማዶ ወደ ነበረውም የአትክልት ስፍራ ገቡ::

[2]ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በዚያ ስለሚገናኝ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም በታውን ያውቅ ነበር:: [3](በመናገር ላይ እያለ[ማቴማርሉቃ]) (ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ[ማቴማርሉቃ]) ይሁዳም ወታደሮችን ከካህናት አለቆችና (ከጸሐፍትና) (ከሕዝቡ ሽማግሌዎች[ማቴማር]) ከፈሪሳውያን የተላኩ ሎሌዎችን እየመራ ወደ አትክልቱ ስፍራ መጣ:: እነርሱም ችቦ፣ ፋኖስና የጦር መሣሪያ (ሰይፍና ዱላ[ማቴማር]) ይዘው ነበር::

[4]ኢየሱስም የሚደርስበትን ሁሉ ዐውቆ ወጣና «የምትፈልጉት ማንን ነው?» አላቸው::

[5]እነርሱም፣ «የናዝሬቱን ኢየሱስን» አሉት::

ኢየሱስም፣ «እርሱ እኔ ነኝ» አላቸው:: አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር:: [6]ኢየሱስም፣ «እርሱ እኔ ነኝ» ባለ ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው መሬት ላይ ወደቁ::

[7]እንደ ገናም የምትፈልጉት ማንን ነው» ሲል ጠየቃቸው

እነርሱም፣ «የናዝሬቱ ኢየሱስን» አሉት::

[8]ኢየሱስም መልሶ፣ «*እርሱ እኔ ነኝ* ብያችኋለሁ እኮ፤ እኔን የምትፈልጉ ከሆነ፣ እነዚህ፣ ይሁዱ ተዉአቸው» አለ፤ [9]ይህ የሆነው፣ «ከሰጠኸኝ ከእነዚህ አንድም አልጠፋብኝም» ብሎ የተናገረው ቃል እንዲፈጸም ነው::

ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ጌቴሴማኒ ወደገቡበት ጊዜ መልሶ ይወስደናል:: ሁለት ሰዓት ሙሉ[67] የወሰደውንና ኢየሱስ በአትክልት ስፍራ የጸለየውን ጸሎት አለመጻፍን ይመርጣል:: በዚህ ፈንታ ከኢየሱስ ጸሎት በኋላ ወደ ተከሠተው ወደ ይሁዳ ክሕደት በቀጥታ

[67] ዮሐንስ በ95 ዓ.ም. አካባቢ ሲጽፍ ተመሳሳይ ወንጌላቱ በዝርዝር የተናገሩትን፣ በተለይ ደግሞ ምዕራፍ 17 ውስጥ የኢየሱስን ጸሎት ከጻፈ በኋላ መድገሙ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም::

ይጓዛል:: ይሁዳ ያን ቡድን ወደ ላይኛው ክፍል ይዞት ሄዶ ሊሆን ይችላል፤ ይህ ቦታ ምግብ እስከሚጀመር ድረስ በምሥጢር የተያዘ ስፍራ ነበር:: ኢየሱስን ለመያዝ ይህ አመች ስፍራ ይሆንላቸዋል:: ገለል ያለ ቦታ ስለሆነ ረብሻ አይነሣም:: ዙሪያውን የታጠረ በመሆኑም ኢየሱስ ለማምለጥ ቢፈልግ አስቸጋሪ ይሆንበታል:: ያ ቦታ ባዶ መሆኑን ሲገነዘቡ ኢየሱስ ከሚያዘወትራቸው ቦታዎች አንዱ በሆነው በጌቴሴማኒ እንደሚገኝ (ሉቃ 22÷39) ይሁዳ ያውቃል:: በአትክልት ስፍራው መግቢያ ላይ ይሁዳን ለማግኘት ኢየሱስ ከተራራው ወረደ:: ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ምንም ማለት አልቻሉም:: ምን እንደሚመጣ የሚያውቁት ይሁዳና ኢየሱስ ብቻ ናቸው::

ይሁዳን ወደ ጌቴሴማኒ የተከተሉት ሕዝብ ምን ያህል እንደ ነበሩ አንዳንድ ክርክር ነበር:: አንዳንዶች ወታደሮቹ የአይሁድ ቤተ መቅደስ ዘቦች ናቸው በማለት ይከራከራሉ:: ይሁን እንጂ ዮሐንስ ቡድን ነበር (አመት «ብዙ ሰዎችም» ይላል):: ይህም ስድስት መቶ ሰዎችን ያካተተ ሰራዊት ነው:: አይሁዳውያን ያን ያህል የቤተ መቅደስ ሰራዊት መያዛቸው ያጠቃይቃል:: አንዳንዶች እነዚህ ከዚህም ከዚያም የተሰባሰቡና ተወዳጅ አለቆቻቸውን ይከተሉ የነበሩ ብሔራዊ ፍቅር ያላቸው ቡድኖች ናቸው በማለት ደምድመዋል:: በተመሳሳዩ ወንጌላት ውስጥ «ብዙ ሰዎች» (ማቴ 26÷47፤ማር 14÷43) የሚለው ይህን ድምዳሜ የሚደግፍ ይመስላል:: ይበልጥኑ ሊሆን የሚችለው ሐሳብ ግን በራሱ በጲላጦስ የተላኩ የሮም ወታደሮች መሆናቸው ነው:: ጲላጦስ በዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ለምን እጁን አስገባ፧ ሊነሣ የሚችለውን ዐመፅ ጸጥ ለማደረግ ነው:: እሑድ የሆሣዕና ዕለትና ሰኞ ቤተ መቅደሱ እየጸዳ ሳለ ኢየሱስ በመጠኑም ቢሆን የሕዝቡን ስሜት ቀስቅሶአል:: በዚህ ታላቅና የተቀደሰ በዓል ዓመፅ እንዳይቀሰቀስ በመሥጋት ሮማውያን በተጠንቀቅ ላይ ናቸው:: ሊቃነ ካህናቱ ኢየሱስን ያለምንም



ረብሻ እንደሚወሰዱት ለጲላጦስ ቃል ቢገቡ ኖሮ ግራ ቀኙ ቡድኖች ዕረፍት ያገኙ ነበር:: ኢየሱስ እንደሚያዝ ጲላጦስ ቢያውቅ ኖሮ፣ ገና በጧቱ ኢየሱስን ወደ እርሰ ለምን ለማምጣት እንደቻሉና የአይሁድ የፈርድ ሸንጎ አባላትም በኢየሱስ ላይ ተገቢ የሆነ ክስ ለመመሥረት ሌሊቱን ሙሉ ለምን ሲሠሩ እንዳደሩ (ሕግን በመጣስ) ግልጽ ያደርግ ነበር:: ከዚህም በላይ እነዚህ ሁኔታዎች ሲካሄዱ ሳለ የጲላጦስ ሚስት ለምን መጥፎ ሕልም እንዳየች ግልጽ ያደርጋል::

አትክልት ስፍራው መግቢያ ላይ ኢየሱስ ማንን እንደሚፈልጉ በመጠየቅ በመጀመሪያ ጉዳዩን አነሣ:: «የናዝሬቱ ኢየሱስን» በማለት መለሱ:: ኢየሱስ፣ «እርሱ እኔ ነኝ» ባለ ጊዜ የይሁዳን ሤራ አከሸፈው:: ይህ ከሆነ አሁን ኢየሱስን መሳም አያስፈልግም:: ተሰብስበው የነበሩት ሁሉ መሬት ላይ ተደፉ:: ከኢየሱስ የአፍንጫ ቀዳዳዎች ውስጥ በወጣ ታምራዊና ተጋራፊ ነፋስ ተደፉን? እንዲህ ላይሆን ይችላል:: ሊቀርብ የሚችለው ገለጻ ይሁዳ ከመደንገጡ የተነሣ ሐናንና ቀያፋን እየረገጠ ወደ ኋላ አፈገፈገ፤ እነዚያ በበኩላቸው ደግሞ ሽማግሌዎችን በረጋገጡት በሊቃነ ካህናቱ ላይ እየተረማመዱ ወደ ኋላ አፈገፈጉ:: ከዚያም ሁኔታው እንደ ተንከባላይ ነገር ወደ ፈሪሳውያን፣ ወደ ሮም ወታደሮች፣ ወደ አዛዦችና ወደ ወታደሮች ተዛመተ:: ምንም ይሁን ምን በፍጥነት ተነሡ፤ ትቢያቸውን አራገፉ፤ ተረጋጉም:: ነገር ግን እንደበታቸው ታስሮ ነበር:: አሁን ምን ማድረግ አለባቸው፧ ኢየሱስ «የምትፈልጉት ማንን ነው?» ብሎ ጥያቄውን በመድገም ዝምታውን ሰበረ:: መልሳቸው አልተቀየረም:: ስለዚህ ኢየሱስ፣ «እኔን የምትፈልጉ ከሆነ፣ እነዚህ ይሂዱ ተዉአቸው» አለ:: በዚህ ፈታኝ ሰዓት እነርሱ እንደሚክዱት እያወቀ እንኳ፣ ኢየሱስ የራሱ ስለሆኑት ሰዎች መጨነቁ የሚገርም ነው:: ይህ ሁኔታ ኢየሱስ ለዐሥራ አንዱ ያለውን ርኅራኄ ብቻ ሳይሆን፣ ለእነርሱ የገባላቸውንም ተስፋ ፍጻሜ ላይ አድርሶታል (ዮሐ 6÷39፤ 17÷12)::

ማቴ 14÷44-45
ከማቴ 26÷49 ጋር

[44]አሳልፎ የሚሰጠውም፣ «እኔ የምስመው እርሱ ነውና ያዙት፤ ተጠንቀቃችሁም ውሰዱት» በማለት አስቀድሞ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር:: [45]እንደ ደረሰም ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ «መምህር ሆይ (ሰላም ለአንተ ይሁን[ማቴ]) ብሎ ሳመው::

ማቴ 26÷50
ከሉቃ 22÷48 ጋር

[50]ኢየሱስም፣ (ይሁዳ ሆይ፤ የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጣለህን»[ማር]) «ወዳጄ ሆይ፤ የመጣህበትን ፈጽም»* አለው::

በዚህ ጊዜ ሰዎቹ ቀርበው ኢየሱስን ያዙት፤ አሰሩትም::

**50 ወይም «ወዳጄ ሆይ፤ ለምን መጣህ?»*

ሉቃ 22÷49

[49]በኢየሱስ ዙሪያ የነበሩ ሰዎችም ሁኔታውን ተመልክተው «ጌታ ሆይ፤ በሰይፍ እንምታቸውን?» አሉት::

ማቴ 26÷51-54
ከዮሐ 18÷10-11
ከሉቃ 22÷51 ጋር

[51]ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ (ስምዖን ጴጥሮስም[ዮሐ]) ሰይፉን መዝዞ በመሰንዘር የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮውን ቈረጠው:: (የአገልጋዩም ስም ማልኮስ ይባል ነበር[ዮሐ])

«(ተው![ሉቃ]) [52]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «ሰይፍህን ወደ ሰገባው መልስ፤ ሰይፍን የሚመዙ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ:: («አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣምን?» አለው::) [53]ካስፈለገ አባቴን ብጠይቀው ከዐሥራ ሁለት ክፍለ ሰራዊት የሚበልጡ መላእክት የማይሰድልኝ ይመስልሃል? [54]ይህ ቢሆን ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት ይሆናል ያሉት ነገር እንዴት ይፈጸማል?» (የሰውየውንም ጆሮ ዳሰ ፈወሰው[ሉቃ]::)



ይሁዳ ኢየሱስን በመሳም አሳልፎ ለመስጠት አዘጋጅቶአል፤ ይህ መሳም አንድ ደቀ መዝሙር ለመምህሩ የሚያቀርበውና የተለመደ የሰላምታ አገላለጽ ሥርዐት ነው:: ነገር ግን ኢየሱስ ራሱን ስለ ገለጠ ይሁዳ መሳም የለበትም:: ሆኖም ይህንኑ ፈጸመ:: ይህ ሐቅ ሙሉ በሙሉ በሰይጣን ቍጥጥር ሥር ያለውን ልብ አሳልፎ ይሰጣል:: ለኢየሱስ በአክብሮት ሰላምታ ያቀረባል:: ነገር ግን በፍቅር አይደለም:: ኢየሱስ «ወዳጄ በማለት መለሰ:: ይህ ከዚህ ቀደም ለማስጠንቀቅ ወይም ለተግሣጽ የዋለ ቃል ነው (ማቴ 20÷13፤ 22÷12):: ከዚያም፣ «ይህን በእውነት ልትፈጽም ነውን?) በማለት ይሁዳን ጠየቀው፤ «እንግዲያውስ የመጣህበትን ፈጽም» አለው:: ይሁዳም ፈጸመ:: እንዲያውም ማቴዎስና ማርቆስ ብዙ ጊዜ ጒንጮቹን በመደጋገም ወይም ኢየሱስን ጥብቅ አድርጎ በመያዝ ከልክ በላይ መሳሙን ያሳያሉ:: ይህ የግብዝነትና የክሕደት ቁንጮ ነው:: ይህ በብዙ ረገድ የሰው ዘር ኢየሱስን የካደ መሆኑን በምሳሌነት ያሳያል:: በአስመሳይ የቸርነት ምልክት ራሳችንን ከእርሱ በማራቅ::

በዚህ ጊዜ ወታደሮቹ ቦታቸውን ያዙ:: ኢየሱስን በመያዝ እንደ ተራ ወንጀለኛ አሰሩት:: ደቀ መዛሙርቱ ለመዋጋት ዝግጁዎች ናቸው:: የእነርሱ የተቃራኒ ወገን ቍጥር ከልክ በላይ የተራራቀ ነው (ሥልሳ ወታደር ለአንድ ሰው):: ሆኖም ኢየሱስ ማዕበልን ጸጥ ሲያደርግና ቤተ መቅደሱን ሲያጸዳ አይተዋል:: እርሱ እነርሱን ተዋግቶ ሊያሸነፍ ይችላል:: ነገር ግን ሰይፋቸውን ይምዘዙ ወይም አይምዘዙ ኢየሱስ ጥያቄያቸውን ከመመለሱ በፊት ጴጥሮስ የፋሲካን በግ የሚሠዋበትን ሰይፍ[68] መዞ በሊቀ ካህናቱ አገልጋይ በማልኮስ ላይ አሳረፈ:: ማልኮስ የሊቀ ካህናቱ ዋና አገልጋይ ነው:: ጴጥሮስ ሰይፉን አወዛወዘ፤ ማልኮስም ዘወር አለ:: ጴጥሮስ ጆሮውን ያዘ፤ ዓላማው

[68] ምናልባት ቀደም ያለውን የኢየሱስን ትእዛዝ በቁሙ (ቃል በቃል) ሳይረዳው አልቀረም (ከሉቃ 22÷36 ጋር ያነ)::

ትከሻው ላይ ያረፈውን ጠጕር ለመቍረጥ ነበር:: የባሰ ጕዳት[69] ከመድረሱ በፊት ኢየሱስ ገታው:: ጴጥሮስ ያኔ አልተያዘም ነበር፤ ምክንያቱም (1) ሁኔታው ከመባባሱ በፊት ኢየሱስ አበረደው፤ (2) ኢየሱስ የማልኮስን ጆሮ እንደ ነበረ ስላደረገ የክሱ ማረጋገጫ ነገር የላቸውም፤ (3) ሽብር የገባቸውንና ቍጡ የሆኑ ዐሥራ ሦስት እስረኞችን ከመያዝ ይልቅ አንድ ረጋ ያ እስረኛን መያዝ ይቀላል::

ኢየሱስ ጴጥሮስ ሰይፉን እንዲያስወግድ ነገረው፤ ምክንያቱም የእርሱ መንግሥት የሚዋጋው በዚህ ዐይነቱ መንገድ አይደለም:: እርግጥ ነው ኢየሱስ 72,000 መላእክትን ለማምጣት ይችል ነበር (እያንዳንዱ መልአክም 185,000 ሰዎችን መሰየፍ ይችላል፤ ከኢሳ 37÷36 ጋር ያነ):: የተለመደው የፊት ለፊት ግብግብ ቢመጣ ኖሮ ግጥሚያ አይኖርም፤ ኢየሱስ ያለጥርጥር ያሸንፍ ነበር:: ነገር ግን ይህ የኢየሱስ መንግሥት ባሕርይ አይደለም:: ይገባናል የሚሉትን ነገር በዐመፅ የሚወስዱ መንግሥታትና ግለሰቦች ሁሉ በተመሳሳይ ዐመፅ ይጠፋሉ:: ከዚህ ባሻገር ግን ለኢየሱስ የእግዚአብሔር ፈቃድ በትንቢት እንደ ተነገረው (ኢሳ 53) ለዓለም ኀጢአት መሞት ነበር:: Tenney (ገጽ 170) ዮሐንስ «ጽዋ»ን ማውሳቱ (18÷11) የመያዝን ሁኔታ ኢየሱስ በአትክልት ስፍራ ካደረገው ጸሎት ጋር ያያይዘዋል ይላል (ማቴ 26÷42፤ ማር 14÷36፤ ሉቃ 22÷42):: በአይአወ (ተጻራሪ በሚመስል) መልክ የሚቀጥሉት ዐሥራ ሁለት ሰዓታት በሰው ዘር ማስመሰልና በመለኮት ዕጣ ፈንታ ይነዳሉ::

[52]ከዚያም ኢየሱስ ሊይዙት የመጡትን የካህናት አለቆች፣ የቤተ መቅደስ ሹሞችና ሽማግሌዎችን እንዲህ አላቸው፤ «ወንበዴ እንደሚይዝ ሰው፣ ሰይፍና ቈመጥ

ሉቃ 22÷52
ከማቴ 26÷55፤
ከማር 14÷49 ጋር

---

[69] «በቃ» (አመት)፣ «ይህን ፍቀዱልኝ» ማለት ሊሆን ይችላል:: የማልኮስን ጆሮ ያነሣ ዘንድ ወታደሮቹ እንዲለቁት የቀረበ ጥያቄ ሊሆን ይችላል::



ይዛችሁ (ልትይዙኝ[ማቴ]) መጣችሁን? [53]በየዕለቱ በቤተ መቅደስ (ሳስተምር[ማቴማር]) ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ እጃችሁን አላነሣችሁብኝም፤ ይህ ግን ጨለማ የነገሠበት ጊዜያችሁ ነው::

[56]«ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነው ነቢያት በቅዱሳት መጻሕፍት የተናገሩት ይፈጸም ዘንድ ነው::» በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርት ሁሉ ጥለውት ሸሹ::

ማቴ 26÷56

[51]ዕርቃኑን ለመሸፈን በፍታ ያገለደመ አንድ ወጣት ኢየሱስን ይከተል ነበር:: ሰዎቹም ይህን ወጣት በያዙት ጊዜ፣ [52]ግልድሙን ጥሎ ዕራቍቱን ሸሸ::

ማር 14÷51-52

ዮሐ 18÷12-13ሀ

[12]ወታደሮቹም ከአዛዣቸውና ከአይሁድ ሎሌዎች ጋር በመሆን ኢየሱስን ያዙት፤ አስረውም [13]በመጀመሪያ የቀያፋ አማት ወደ ነበረው ወደ ሐና አመጡት::

ምን እየተካሄደ እንደ ሆነ በትክክል የሚያውቅ መሆኑን ኢየሱስ ለአስቆሮቱ ይሁዳ አሳየው:: ከዚያም ምን እየተካሄደ እንደ ነበር በትክክል እንመዲያውቅና ይህም በቍጥጥር ሥር እንደ ሆነ ለዐሥራ አንዱ ግልጽ አደረገላቸው:: ከዚያም ወደ አይሁድ አለቆች ዘወር ብሎ በድጋሚ፣ «በዚህ ምን እንደሚካሄድ ዐውቃለሁ፤ የምትሠሩት በጨለማው ገዥ ቁጥጥር ሥር ሆናችሁ ነው» አላቸው:: በቤተ መቅደስ ኢየሱስን ለመያዝ ብዙ ዕድል ነበራቸው:: ነገር ግን ድርጊቱን ለመፈጸም ድፍረቱም ሆነ (ዮሐ 7÷32:42-47 ጋር ያነ) በቂ ድጋፍ አልነበራቸውም:: ይህ የሆነው ኢየሱስ ክፉና ዐመፀኛ ስለነበረ አይደለም፤ እውነትን ስለ ያዘ እንጂ:: በመሆኑም የፍርድ ሸንጎው በሁኔታዎች በመነዳትና በትንቢት በመያዝ በጨለማ ሽፋን መሥራት አለበት::

ደቀ መዛሙርቱ ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ የኢየሱስ መንግሥት በጋሻና በጐራዴ የማይመሠረት መንፈሳዊ መንግሥት

መሆኑን ሲገነዘቡ ሸሹ:: በኢየሱስ ስላፈሩ ወይም ለእርሱ ለመሞት ስለ ፈሩ አይደለም:: መንፈሳዊ ጦርነትን እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው ስለማያውቁ ነው:: ኢየሱስ ሰይፋቸውን ከወሰደባቸው የሚዋጉበት ሌላ ነገር የላቸውም፤ ስለዚህ ሮጡ::

ማርቆስ እንግዳ ነገር ጽፎአል:: ከሸሹት ሰዎች መካከል «በፍታ ያገለደመ» ወጣት ይገኛል:: «ብዙ ጊዜ ወንዶች ቺቶን የተባለውን የውስጥ ልብስ ይለብሳሉ:: ይህ ወጣት ሲንደን የተባለ የላይ ልብስ ለብሶአል:: ብዙ ጊዜ ይህ ልብስ የሚሠራው ከሱፍ ነው:: የእርሱ የተሠራው ግን ከተልባ እግር ሲሆን ልብሱ በሀብታሞች ብቻ የሚለበስና ውድ ነው» (Wessel pp. 766-767):: ሁሉም ሲበታተኑ ከዘቦቹ አንዱ የወጣቱን ልብስ ያዘበት፣ እርሱም ልብሱን ትቶ ራቁቱን ወደ ቤቱ ሸሸ:: አያሌ ሊቃውንት ወጣቱ የወንጌሉ ጸሐፊ ዮሐንስ ማርቆስ ነው ብለው ይገምታሉ:: ከሁኔታው ጋር የሚገጣጠም ነው:: ከዚህም በላይ በራስህ ላይ እስካልደረሰ ድረስ ይህን ያህል ፋይዳ ያለው ዝርዝር ጉዳይ አይደለም! የመጨረሻው እራት በዮሐንስ ማርቆስ ቤት ሳይሆን አልቀረም:: ይሁዳ ኢየሱስን ለማስያዝ በመጣ ጊዜ ወጣቱ ኢየሱስን ለማስጠንቀቅ ወይም ምን እንደሚሆን ለማየት ከአልጋው ተነሥቶ ወደ አትክልት ስፍራ ሮጠ:: እዚያም በአሳፋሪ ሁኔታ ተያዘ::

እንዲህ ያለ ታሪክ ወንጌላቱ ውስጥ ለምን ታከለ≅ ከሱሪ ቁልፎችና ዚፖች መሠራት በፊት ልብስን ማጣት የተለመደ ክሥተት ሲሆን ሥነ ጽሑፋዊ ጭብጥ አለው::[70] በመሠረቱ የፍርሃት ሩጫን በአጽንዖት ያመለክታል:: ይህ ወጣት ኢየሱስን ለማገዝ ወጣ፤ ነገር ግን ራቁቱን በመሮጥና በፍርሀት በመያዝ የተነሣበትን ጉዳይ ሳያሳካው ቀረ:: ኢየሱስ ብቻውን ከጠላቶቹ ጋር ቀረ:: እንደ ወንጀለኛ ተያዘ፣ ፍርዱም ተጀመረ::

[70] H. Jackson, "Why the Youth Shed His Cloak and Fled Naked: The Meaning and Purpose of Mk. 14:51-52," *JBL* 116/2 (1997): 273-289.



# ምድብ ዐሥራ ሁለት
# የክርስቶስ ሞት

## ለፍርድ መቅረቡ

ኢየሱስ ስድስት ጊዜ ለፍርድ ቀርቧል:: የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ በአይሁድ ፊት ሲሆን እነርሱም፣ ሐና፣ ቀያፋና ሸንጐው ናቸው:: ሁለተኛዎቹ ሦስቱ፣ ሕዝባዊ ሲሆኑ በጲላጦስ፣ በሄሮድስና እንደገና ወደ ጲላጦስ መመለሱን የሚመለከቱ ናቸው:: እነዚህን ፍርድ ብሎ መጥራት አግባብ አይሆንም፣ በአይሁድ ሕግ[1] ማላገጥ እንጂ ፍርድ ሊባሉ የሚችሉ አልነበሩም:: አይሁድ የሚያስተላልፉት ፍርድ ቀድሞውኑ የተወሰነ ነበር፤ ፍርዱ እውነትን ወይም ፍትሕን ሳይሆን ቅንዓትና ፍርደ ገምድልነትን መሠረት ያደረገ ነው:: የሮማውያንን ፍርድ በተመለከተም ቢሆን፣ ኢየሱስ በማንኛውም በደል ተጠያቂ ሆኖ አልተገኘም:: ይልቁንም ከአይሁድ መሪዎች ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥን ለመሸሽ ሲል ጲላጦስ ለእነርሱ አሳልፎታል፤ እንደዚያ ባያደርግ፣ ፖለቲካዊ ሥልጣኑ ያከትም ነበር::

[1] የአይሁድ መሪዎች ሚሻኒክ ሕጐችን በግልጽ ተላልፈዋል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሸንጐው እንዴት መሥራት እንዳለበት መመሪያ የሚሰጡ ከኢየሱስ 100 ዓመታት በኋላ የመጡ ፈሪሳዊ አስተሳሰቦች ናቸው:: እንዲህ ከሆነ፣ እንደ አጣዳፊ ሁኔታ የሚታየው በፍርዱ ሂደት ዙሪያ ካሉ እንግዳ ሁኔታዎች አንጻር ይህ ራሱ ለብዙ ግምታዊ ሐሳቦች መነሣት ምክንያት ይሆናል:: ያም ሆኖ የተዘረዘሩት ሕገ ወጥ አሠራሮች፣ እንዲሁም ስለ ሐሰት ምስክሮቹ ማቴዎስና ማርቆስ ባቀረቡት ዘገባ ግልጽ የሆነ የፍትሕ መዛባት መኖሩን ለማየት ይቻላል:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ የጲላጦስ አሠራር ሕገ ወጥ ቢሆንም፣ R.L. Overstreet, "Roman Law and Trial of Christ," *BibSac* 135 (1978): 323-332 እንደሚያመለክተው በእርሱ ዳኝነት ውስጥ የተፈጸመ ነበር::